ከጨለማ ወደ ብርሃን

የአዲስ ኪዳን መጥምቃዊት ቤተ ክርስቲያን
ጅማሬ

በሎራሊ ሊንድሆም ተጻፈ::

መጀመሪያ በ2000 ዓ.ም. ታተመ::

አዲስ አበባ 2000 ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved
2000


ማውጫ

ምስጋና .....
ካርታዎች .....
የጸሓፊዋ መግቢያ 6
ጥሪ 12
ኦርቶዶክስ 17
ምልክት 21
የእግርን ትቢያ ማራገፍ 27
ታላቅ ጉጉት 31
የጸሎት ኃይል 36
የጥንቆላ መጽሐፎች መቃጠላቸው 41
ዐመፅን ማነሣሣት 45
ድንኳኖችን መሥራት 49
መነቃቃት 56
ስደት 65
ክስ 67
ብርታት 74
ጠላት 81
የማሰናከያ ዐለት 89
መብዛት 95
ማህበራዊ መገለል 102
በበለጠ መጠንከር 112
ጥበቃ 118
ምስክሮች 126
የእሳቱ መቀጣጠል 131
እስከ ምድር ዳርቻ 139
እስራት 148
ለአገልግሎት መለየት 154
መደምደሚያ 162
ደብዳቤዎች 164
የቃላት ፍቺ 166

ምስጋና

ይህ መጽሐፍ ታላቅ አስተዋፅኦ ላደረጉና የዚህ ታሪክ ባለቤት ለሆኑት ለማ.ከተሉት ሁሉ ከምስጋና ጋር የተበረከተ መጽሐፍ ነው፡-

- በተለያዩ ቦታዎች ላሉና ለእኛ በመንዝ ለነበረው እንቅስቃሴ መሳካት በታማኝነት ለጸለዩልን፣
- ለአገልግሎት ስንሄድ የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ላቀረቡልን አብያተ ክርስቲያናት ወንጌል በራሳቸው ቋንቋ በቴፕ ክር ላሠራጩት ኢትዮጵውያን ሰባኪዎችና መዘምራን፣
- ከእኛ በፊት በብዙ ድካም የወንጌልን ዘር ዘርተው በጥቂቱም ቢሆን የወንጌልን ፍሬ ላዩ ሚሲዮናውያን፣
- የእግዚአብሔርን መልእክት በአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍና እንዲሁም በትናንሽ ጽሑፎች ላሳተሙልን ጸሓፊዎች፣
- በፈቃደኝነት ልጆችን ለተንከባከቡልንና ላስተማሩልን በጉድ ሼፐርድ ት/ቤት ለሚገኙ ወላጆችና አስተማሪዎች፣
- እኛን ላጓጓዙን ለሚሲዮናውያን አየር ማመላለሻ ጎብረት ፓይለቶችና እነሱን በሬድዮ ለሚከታተሏቸው ሚስቶቻቸው፣
- በገጠር እንኖርና እንሠራ ዘንድ ለተንከባከቡን፣ አስፈላጊውን ትብብር ላደረጉልን በአዲስ አበባ ለሚገኙ የሚሲዮን ጣቢያዎች፣
- እኛ ለእግዚአብሔር ጥሪ ተገቢውን መልስ ስንሰጥ ልጅና የልጅ ልጆቻቸውን ለተዉት ወላጆቻችን፣
- በእንግዳ አገርና በሕዝቦቹ ውስጥ ሳለን አብሮን /አብራን ለነበረ/ች ልጃችን፣
- በቴፕ ስብከት ሥርጭታቸው ላስተማሩንና ላነቃቁን ሰባኪዎች።


Our area of work in Munz
N
Hannah Church
Cliff edges
Digimsha Church
Agarcha Church
Bridge
Connotik house
Air Strip
Addis
Clinic
Handicraft School
Air Strip
KAYA
Girmay house
Tudobear Church
Aloe Church
Maullah Maryam Church
Wuhau Church
Shai River
Addis Ababa
180 air miles
(45 min.)
Approx. scale in miles

የጸሐፊዋ መግቢያ

«ወዴትም መሄድ አትችሉም። ወደ ሚሽን ግቢ ተመለሱ፤ ከዚያም አትውጡ። እኛ ሁል ጊዜ ክትትል እናደርግባችኋለን።»

ሚሲዮናውያኑ እንደዚህ ዐይነቱ አጋጣሚ ሊመጣ እንደሚችል ቀደም ሲል ራሳቸውን አሳምነውና የአእምሮ ዝግጅት አድርገው የነበረ ቢሆንም፥ መንግሥታዊው ትእዛዝ አስደንጋጭ ሆኖባቸው ነበር። ይሁን እንጂ ከሚሲዮናውያኑ መካከል አራቱ የእንሰሳት ሀኪም የነበረው ዶ/ር ጀሪ ቤድሶል፥ የእርሻ ባለሙያ የነበረው ዶ/ር ዳሌ ቢግሌ፥ ሲይን ግሮስ እና ከእነርሱ ጋር ዐብሮ ይሠራ የነበረው ኢትዮጵያዊው ዶ/ር ሙኮ አክሬ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ዕቅዳቸው ከአዲስ አበባ ዐሥራ ስድስት ማይል ወደሚርቀው ፀሐይ ሲና ወደሚገኘው ቤታቸው መሄድ ነበር። ነገር ግን የተጓዙት የመንዝ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ወደ መሃል ሜዳ ነበር። ለረጅም ጊዜ በሠሩበትና በኖሩበት በዚያ አካባቢ ባደረጉት የመጨረሻ ጉብኝት ሁሉም ታላቅ ተስፋና ጉጉት ዐድሮባቸው ነበር።

ከብዙ ሳምንታት በፊት ሚሲዮናውያኑ እየተባባሰ ባለው የመንዝ ጦርነት ባለማወቅ እንዳይጐዱ በማሰብ የመንዝ ባለሥልጣናት ከአካባቢው ለቀው እንዲወጡ አዘዋቸው ነበር። ከዚህ የተነሣ በፍጥነት ስለ ወጡ የረሷቸው ዕቃዎች ነበሩ። ተገቢ ስንብት የሚያደርጉበት ጊዜ እንኳ አልነበራቸውም። አንድ መኪና ሙሉ ለሕዝቡ የሚታደል የእንሰሳት መድኀኒትና መጽሐፍ ቅዱስ ነበራቸው።

በቤት ውስጥ እስራት የተነሣ ጥረታቸው ሁሉ ከንቱ መስሎ መታየቱ ግልጽ ሆነ። ሚሲዮናውያኑ ከእስራት ቶሎ መለቀቅ አለመቻላቸው ደግሞ ከሁሉም የከፋ ነው። ከጓደኞቻቸው አንዱ የነበሩ የሥራ ባልደረባቸው ዶ/ር ካናታ በአዲስ አበባ ከተማ ዐሥራ ስድስት ቀን ታስረው ከተለቀቁ ገና አራት ቀናቸው ነበር።

ተስፋ በመቁረጥ ስሜት ወደ ቤታቸው እያመሩ ሳሉ ስለ ጉዞው የነበራቸውን ዕቅድ መልሰው መላልሰው ይቃኙት ነበር። ስለዚህም ጉዞ ስልት እየጸለዩ ብዙ ጊዜ ቈይተዋል። ሚሲዮናውያኑና ሚስቶቻቸውም ጭምር አካባቢውን ለቀው መውጣታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ ከስምምነት ላይ ደረሱ። የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ማረጋገጣቸው መጠነኛ የሆነ መረጋጋትን አሳደረባቸው። ነገር ግን በቤቱ ዙሪያ አንድ የጦር መሣሪያ የታጠቀ ዘበኛ ሲቃኝ ተመለከቱ።

ከዚያን ቀን አስቀድሞ መንግሥት በየአካባቢው የሚገኙትን መሪዎች ለስብሰባ ወደ መሐል ሜዳ ጠርቶአቸው ነበር። ቁስ ግርማ የቀያ ዋና ተወካይ እንደ መሆናቸው መጠን በስብሰባው ላይ የመገኘት ግዴታ ነበረባቸው። ሦስቱ የቅርብ ጓደኞቻቸው ታጠቅ፥ ግርማና አስቻለው አብረዋቸው ወጥተው ነበር።

ስብሰባው ሊያበቃ ሲቃረብ፥ ረጅሙን የሰባት ሰዓት ጉዞ ጨለማው ሳይመጣ ቶሎ ቶሎ ሂደው መጨረስ እንዳለባቸው በሰማዩ ላይ ካዩት የተለምዶ ምልክት ተገነዘቡ። ስለዚህ ጊዜው ከመጨለሙ በፊት ፈጠን ብለው ጉዟቸውን ወደ ቀያ ቀጠሉ። ልክ ከከተማው ወጥተው ከግርጌ ወዳለው ሸለቆ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት የአፈ ወንዝን ቀጭልቀለት ሲያያዙት ደካማ የመኪና ድምፅ ሰሙ። የመኪናዋን መቃረብ መመልከት ጀመሩ። በዚያ ሁኔታ እንዳሉም ሚሲዮናውያኑ ተመልሰው እየመጡ ሳይሆን እንዳልቀረ ዐሰቡ። ምንም እንኳ መንደሩ መኪናዋን ቢከልላቸውም፥ ከመኪናው ጎማ ሥር የሚነሣው አቧራ ያለምንም ስሕተት ወደ ሚሽን ግቢ መራቸው።

ምንም ዐይነት ውይይት አላስፈለገም ነበር። ወዲያውኑ የሄዱበትን ዱካ በመከተል ሚሲዮናውያን ወዳጆቻቸውን ለማግኘት ሮጡ፤ ተገናኙና ተሳሰሙ። ይህንን ስብሰባ እግዚአብሔር ያዘጋጀው እንደ ሆነ ድምዳሜ ላይ ከመድረስ ውጭ ሌላ ምንም ነገር ማድረግ አልቻሉም። ምንም እንኳ ሚሲዮናውያኑ ከቤት መውጣት የተከለከሉ ቢሆንም፥ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጓደኞቻቸው ከእነርሱ ጋር እንዲያድሩ ተፈቅዶላቸው ነበር። በዚያ ምሽት መታሰራቸውን ማወቃቸው እንኳ ዐብሮ በመጸለይና በማምለክ ያገኙትን ደስታ አላጠፋባቸውም።

የመንዝ ወጣቶች በቅርብ ሳምንታት ውስጥ ጌታ የሠራውን ሥራና ርካታ ለማግኘት ጥረት እያደረጉበት ያለውንና እያደገ የሚታየውን ለእግዚአብሔር ቃል የመጠማት ጉዳይ ለመናገር ይጓጉ ነበር። በዚያ ጊዜ የነበረው የሚሲዮናውያን ሁኔታ ሲታይ፥ መንዝ ለመሥራት ተመልሰው መምጣታቸው ፈጽሞ የሚሆን አይመስልም ነበር። እነዚያ ወጣቶች የእነርሱ ተራ እንደ ደረሰ አስተዋሉ። ከሚሲዮናውያኑ ጋር እየተነጋገሩ በነበረበት ጊዜ ችቦው ተላልፎ ተሰጠ።

«አስከ አሁን ድረስ መጽሐፍ ቅዱስን ስታስተምሩንና ክርስቶስንም ከእኛ ጋር ስትካፈሉ ቈይታችኋል። መሄድ እንዳለባችሁ ይገባናል፥ ነገር ግን እናንተ እንዳደረጋችሁት ወንጌልን አርስ በርሳችን መማማርና መከፋፈል አንዳለብን እግዚአብሔር አሳይቶናል። ከእናንተ መልካም ምስክርነት የተነሣ በጌታ ጸንተን እንደምንቆም ርግጠኞች መሆን ትችላላችሁ።» ወጣቶቹ በእነዚህ ቃላት ሚሲዮናውያኑን ተሰናበቷቸው።

ከመሄዳቸው በፊት ግን እነዚህ አራት የቀያ ሰዎች መሸከም የሚችሉትን መጽሐፍ ቅዱስና መድኀኒት ለመውሰድ መሰናዶና ዝግጅት ተደረገ። የቀረውን ደግሞ ተመልሰው መጥተው መውሰድ ነበረባቸው። በአስቸኳይ ወደ አዲስ አበባ ይመለሳሉ በሚል ቅድመ ሁኔታ ሚሲዮናውያኑ በሚቀጥለው ቀን ከዚያ ቦታ ለቆ ለመሄድ ተፈቀ ደላቸው። ከስድስት ሳምንት በኋላ ሰኔ 1969 የሳውዘርን ባፕቲስት

ሚሲዮናውያን ሁሉ ኢትዮጵያን ለቀው ወጡ። በዚያ ቦታ በትክክል ዐሥር ዓመት ረናል።

በመጀመሪያ ከኮረብታ በስተጀርባ ባለ አገር በመንዝ ዙሪያ ለመሥራት ማሰባችንን ሰዎች ሲያውቁ በጥርጥርና በሥጋት ተሞልተ ው ነበር። ማንም የውጪ ዜጋ በዚያ ስፍራ ኖሮ አያውቅም፥ ወደዚያ ቦታ የሄደም በፈቃዱ ተመልሶ አያውቅም። እጅግ በጣም ታላቅ ተስፋ ካደረባቸው መካከል አንዱ፥ ሰዎች በሥራችን እኛን ለማመንና ጓደኛም ለማድረግ ቢያንስ ዐሥር ዓመት ሊፈጅባቸው እንደሚችል ተናግሯል።

ነገር ግን በኢትዮጵያ በተለይም በመንዝ ለመሥራት ፈቃድ በማግኘት ረገድ የነበረው ሁኔታ የነበረብንን ጥርጣሬ ሁሉ አስወግዶልናል። በዚህ ጉዳይ ላይ የጌታ ምሪት ግልጽ ስለነበር፥ የመመለስን ነገር ፈጽሞ አላሰብነውም። የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ዓመታት አማርኛ ቋንቋን በመማር፥ ቤት በመገንባትና እንደዚሁም የጎብረተ ሰቡን ልምድና ባህል በመለማመድ አሳለፍን።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለሳውዘርን ባፕቲስት ሚሲዮን ፈቃድ የሰጠው የማጎበረ ሰብ ልማት በአብዛኛው ባልተስፋፋበት አካባቢ በተለይ በመንዝ እንድናስፋፋ ነበር። እኛም ሚሲዮናውያን እንደ መሆናችን መጠን አንዳንድ አዳዲስ ፕሮግራሞችን ጀመርን፤ ሥጋጃ ሥራ፥ ድልድይ ግንባታ፥ በክፍታ ስፍራ የሚዘሩ ሰብሎች ምርምር፥ ተንቀሳቃሽ የሰውና የእንስሳት ህክምና ክሊኒኮችን ማቋቋም ዋና ዋናዎቹ የልማት ፕሮግራሞቻችን ነበሩ።

በተመሳሳይ ጊዜ በጥንቱ የክርስቲያን ግዛት ውስጥ ካለችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ራሳችንን ማስታዋወቅ ጀመርን። በየእሑዱ ሚት ቅዳሴ ስናስቀድስ የሚታዩ ማራኪ ነገሮች፥ የሚሰሙ ድምፆችና ልዩ ልዩ መዐዛዎች ቀልባችንን ሳቡን። ሃይማኖታውያን ክብረ በዓሎች በተለይ ደማቅና አስደሳች ነበሩ። ስለ ሕዝቡ የበለጠ እያወቅን ስንሄድ፥ ለረጅም ዘመን ተገልለው ለኖሩትና ጊዜ ለዘነጋቸው ሁሉ ያለን ፍቅርና ሐሳብ አደገ።

ከባህር ወለል በላይ 1000 ጫማ ከፍታ ያለው የመንዝ ዐምባ ምድር በዐጫጭር የማይል ርቀት ላይ በሚገኙ ትላልቅ ሸለቆዎች የተከፈለ በመሆኑ፥ ዓለም ዐልፎት ሄዷል። እንደ ዕድል ሆኖ አካባቢው ከዘመናት በፊት እንደ ነበረ እንዲሁ ሳይለወጥ አሁንም አለ። ሕዝቡ ዝቅተኛ ኑሮን ይራል። በአብዛኛው ነዋሪዎቹ የአንድ አዝመራ ወቅት ቢስት ለረኃብ የሚጋለጡ ናቸው። ከዚህ የባሰው አስከፊ ነገር ደግሞ ብዙ ጊዜ በመሬት ጭቅጭቅ ወይም በስርቆት ሳቢያ የሚፈጠረው ቤተ ሰባዊ ጠብ የሚያስከትለው የመገዳደል አደጋ ነው።

መንዜዎች ማንኛውንም ሊታረስ የሚችል መሬት እያረሱ በአብዛኛው ራቅ ራቅ ብለው በገደልና በኮረብታዎች ጥግ ጥግ ይራሉ። ዐፈሩ ከዉስጥ ጉጥረ ነገሩ ያሉቀበትና ድንጋያማ ነው። ገበሬዎች

ለእርሻ የሚገለገሉባቸው እንስሳት በሬዎች ሲሆኑ፥ የእርሻ መሣሪያቸው ባህላዊ ማረሻ ነው። ከገብስ፥ ሽንብራና ከምስር በቀር ሌሎች የሰብል ዐይነቶች ከፍ ባለ ቦታ ላይ እምብዛም አይመረቱም። ምግባቸውም በጣም ቀላል ምግብ ነው። ዋና ምግባቸው በኮመጠጠ እርሾ ተለውሶ ምጣድ ላይ የሚጋገር ቀጭን ጠፍጣፋ እንጀራ ነው። እንጀራ ሁልጊዜ የሚበላው በወጥ ነው። ወጥ ከበርበሬ፥ ከሽሮና ከምስር ይሠራል። ገበሬዎቹ ዶሮ፥ በግ፥ ላም ያረባሉ። ዐልፎ ዐልፎም ሥጋ፥ ዕንቁላልና እርጎ ይመገባሉ። ከገብስ የሚጠመቀው ጠላ ብዙ ጊዜ የሚጠጡት መጠጥ ነው።

የቤታቸው ግድግዳ የተሠራው ከጭቃ ግንብ ሲሆን ጣራው በሳር የተከደነ ነው። የውስጡ ግድግዳ፥ ወለሉና መቀመጫ መደቦች ከገለባ ወይም ከጭድ ጋር ዐብሮ በተቦካ የከብቶች እበት ይለቀለቃል። የከብቱን እበት ጠፍጥፈው በማድረቅ ለማገዶነትም ይጠቀመበታል። ምግብ የማብሰል ሥራ የሚሠራው በክፍሉ መካከል ላይ በተዘጋጀ ምድጃ ላይ ነው። ብርድ እንዳይገባ በማሰብ አብዛኞቹ ቤቶች በቂ የሆነ መስኮት ስለሌላቸው፥ የቤቶች ግድግዳና ጣሪያ በጢስ ጠቀሮ ይስተዋላል። ምግብ የማብሰል ሥራ ሲሠራም ቤቶቹ የሚታዩት ጢሳማ ሆነው ነው። ቤተ ሰቡ ሀብታም ከሆነ፥ በከብቶቻቸው ማደሪያ ክፍል ላይ አንድ ፎቅ ክፍል በባሕር ዛፍ ዕንጨት ላይ የከበት ቄዳ ጠፍር ተወጥሮ ከተሠራበት ዐልጋ ጋር ሊገኝ ይችላል። ለሙቀት ሲባል ብዙ የቤተ ሰብ አባላት በያንዳንዱ ዐልጋ ላይ በአንድነት ስብስብ ብለው ይተኛሉ።

የኤሌክትሪክ መብራት በገጠሩ ክፍል የለም። ለመብራት የሚጠቀሙት ጥሙር ጋዝ በኩራዝ ውስጥ በመጨመር ነው። የሚጠጣ ውሀ በእንስራ ከምንጭ ይቀዳሉ። ለቤተ ሰቡ ውሃ የሚቀዱት እናቶችና ሴቶች ልጆች ናቸው። ለተለያዩ ግልጋሎቶች ማለት ለመጠጥ፥ ለምግብ ማዘጋጃ፥ ለመተጣጠቢያ ወዘተ. የሚውለውን ውሃ ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ከምንጭ ወደ ቤት ያግዛሉ። ውሀውን የሚጠቀሙበት እንዳሻቸው ሳይሆን በጥንቃቄና በቀጠባ መልክ ነው። መጸዳጃ ቤቶች ወይም የቁሻሻ መተላለፊያ ቱቦዎች የሉም።

በአብዛኛው እያንዳንዱ የመንዝ ቤተ ሰብ መሥራት የሚፈልገውን ለመሥራት በራሱ ብቁ ነው። ራሳቸው መሥራት የሚይችሏቸውን በየሳምንቱ ወደሚቆሙት የአካባቢ ገበያዎች በመሄድ ገዝተው ያመጣሉ። ለምሳሌ ጎማ ጫማ መርፌ ቀጭልና፣ ጨውና ጠመንጃ የመሳሰሉት ሸቀጦች ነጋዴዎች ገበያ ላይ ይዘዋቸው የሚታዩ ናቸው። እነዚህ ሸቀጦች በጎብረተ ሰቡ ዘንድ በጣም ተፈላጊ ከሚባሉት ሸቀጦች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። ነዋሪዎቹ ከአንድ በላይ መቀየሪያ ልብስ የሚራቸው ዐልፎ ዐልፎ ነው። ማታ ማታና እንዲሁም ብርድ በሆነ ቀን ነዋሪዎቹ ጋቢ ይለብሳሉ። ጋቢ የሚሠራው እዚያው ሰፊር ውስጥ በሚሩ ሸማኔዎች ነው። ጉልማሶችና ወጣት ወንዶች ልጆች

ዱላ ከእጃቸው አይለያቸውም። የዚህም ጥቅም ለምርኩዝነትና ራስን ለመከላከል ነው። በወጣገባው መልክአ ምድር ላይ ሁሉም የሚጓዘው በባዶ እግሩ ነው። አብዛኛው መንዜ ከውጩ ዓለም ጋር ግንኙነት የለውም።

ሕዝቡን ብዙ እየተለማመድነው ስንመጣ፣ በአጠቃላይ ስለ ነበረው ጥርጣሬና በመንዝ የምናከናውነውን ሚሲዮናዊ ተግባር ተገቢነትና ትክክለኛነት ስላለመቀበሉ የሰጠውን አስተያየት የበለጠ እያደነቅን ሄድን። ነገር ግን እግዚአብሔር በእኛ አለማወቅ ውስጥ ጥበቡን ይገልጥ ነበር። እግዚአብሔር በዐሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ እኛ በረጅም ዘመን ይሆናሉ ብለን ካሰብናቸው የሚበልጡ ታላላቅ ተግባራትን አከናውኗል።

ስድስት ዓመት የወንጌል ዘር ዘራን። ነገር ግን ምንም ፍሬ አላየንበትም። ቢሆንም የእግዚአብሔር ቃል የሚሻውን ሳይፈጽምና ፍሬ ሳያፈራ በከንቱ እንደማይመለስ በኢሳያስ 55÷11 ላይ የተገለጠውን የተስፋ ቃል መሠረት በማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት መዝራት ቀጠልን። ከዚያም የመጀመሪያዎቹ ፍሬዎች ታዩ፤ ውጊያውም ተጀመረ። የአብዛኛው አዝመራችን የመከር ጊዜ እየደረሰ ሲመጣ፣ ውጊያው ይበልጥ እየተባባሰና እየከፋ ሄደ። በየጊዜው ጠላት የመውጊያ ፍላፃውን ይወረውር ነበር፤ እግዚአብሔርም ለራሱ ሕዝብ ተአምራዊ በሆነ መንገድ ጥንቃቄ ያደርግ ነበር። ከእያንዳንዱ ድል ጋር ፍሬው እየተበራከተ ሄደ። ጎብረታችንም መጠነኛ ጥንካሬ አሳየ።

በእንደዚህ ዐይነቱ መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ እያለን በተደጋጋሚ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለውን የሐዋርያት ዘመንና ሕይወት እናስብ ነበር። ነገሮች የጨለሙ በመሰለን ጊዜ ተስፋ ሳንቆርጥ ጠላታችንን እንድንቋቋመው ጎይል የሆነን፣ የሐዋርያት በዚያ መከራ ውስጥ የማለፍ ምስክርነትና የእግዚአብሔር ታማኝነት ነው።

እግዚአብሔር ሕያው ነው! ሰይጣንን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል አድርጎታል። እግዚአብሔር ዛሬም ከሁለት ሺ ዓመት በፊት ይሠራ እንደ ነበረው ይሠራል። ይህም መጽሐፍ በጣም ትንሽ በሆነው የዓለም ክፍል በመንዝ፣ የእግዚአብሔር እጅ ሕዝቡን ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማምጣት እየተንቀሳቀሰች እንደ ሆነ የሚያሳይ ምስክር ነው።

አሁንም እንደገና እግዚአብሔር በማቴ 4÷16 ላይ፣ «በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፤ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው» ተብሎ የተነገረውን የተስፋ ቃሉን ፈጸመው።

ይህ መጽሐፍ ዛሬ ስደትና መከራ የሚደርስባቸውን አማኞች ያጽናናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በክርስትና ሕይወት ጉዞአቸው የዛሉትንና የደከሙትንም እንደሚያበረታታቸው እምነቴ ነው። ከሁሉም በላይ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያለውን የእግዚአብሔር ፍቅርና

ይቅርታ ያልተለማመዱ ሁሉ በዚህ አስደናቂ ታሪክ ውስጥ አበክረው እንዲያገኙት እጸልያለሁ።

ራእይም ለጳውሎስ በሌሊት ታየው፤ አንድ የመቄዶንያ ሰው፡- ወደ መቄዶንያ ተሻገርና ርዳን እያለ ቆሞ ሲለምነው ነበር። ራእዩንም ካየ በኋላ ወዲያው ወደ መቄዶንያ ልንወጣ ፈለግን፤ ወንጌልን እንድንሰብክላቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ጠራን መስሎናልና።

የሐዋርያት ሥራ 16÷9-10

ጥሪ

«ቀጥሎስ ምን እናድርግ?» በ1969 ዓ.ም የመክር ወራት የእግዚአብሔርን ምሪት እየጠበቅን ሳለን ይህን ጥያቄ ራሳችንን በመደጋገም ጠየቅነው። እኔና ሬይ በሁለተኛው ኢትዮጵያ ጉብኝታችን የሚኖረን አገልግሎት ለየት ያለ አቅጣጫ እንደሚይዝ ዐሰብን። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ሬይ በሚሲዮኑ የእጅ ሥራ ት/ቤት ውስጥ ስጋጃ ሥራ ያስተምር ነበር፤ እኔ ደግሞ ሦስቱን ልጆቻችንን ዩሐንስን፣ ጁሊንና ስቴፈንን አስተምር ነበር። እናም ባተሌዎች ነበርን። ከዚህ ሁሉ ጋር እኛም መማር ነበረብን፤ እጆቻችንም በሥራ ተጠምደው ነበር። በዚህ ምክንያት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ቶሎ ዐለፉ።

የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ በጣም አስፈላጊ ስለ ነበረ የዕረፍት ጊዜ ፈቃዳችንን ጨርሰን፣ የአራት ወር የአማርኛ ቋንቋ የማጠናከሪያ ትምህርት መማር እንዳለብን ዐሰብን። ለተማርንባቸው አሰልቺ ሰዓቶች የሚያስገልገውን ገንዘብ ሁሉ ከፈልን። ከተራ ንግግር ላቅ ወዳለ የውስጥ ሐሳብን ወደ መግለጽ ችሎታ ስለ ተሸጋገርን ተሸለምን።

በዚያን ጊዜ ልጆቻችን በጉድ ሼፐርድ ዐዳሪ ትምህርት ቤት ይማሩ ነበር። በሦስቱም መንፈቀ ትምህርቶች እዚያው ነበር የሚቈዩት። ከእያንዳንዱ መንፈቀ ትምህርት በኋላ በዕረፍት ጊዜያቸው ወደ መንዝ ይመጡ ነበር። የመጀመሪያው እንቅስቃሴያችን ሰዎች ወደ እኛ እየመጡ ሳይሆን እኛ ወደ እነርሱ እየሄድን በማገልገል ላይ የሚያተኵር ሆነ። የሰውና የእንሰሳት ህክምና ጣቢዎች ለእንደዚህ ዐይነቱ የአገልግሎት ስልት ተስማሚ ናቸው፤ የእጅ ሥራን ማስተማሩም ሌላው ጉዳይ ነበር። አንድ ዐዲስ የሆነ ክሂሎትን አስተምሮ ለማስጨበጥ ረዘም ያለ ጊዜ ይጠይቃል። ሰዎችም ዘወትር መማር አለባቸው። ስለሆነም ለእጅ ሥራ ትምህርት እምብዛም ትኵረት አልሰጠንም ነበር።

ከዚያም እየተዘዋወሩ መሥራት የሚለውን ሐሳብ ማብላላት ጀመርን። አንድ ትልቅ ድንኳን ነበረን። በአእምሯችን ውስጥ ሠርያ የነበረው አማራጭ አስቀድሜ እንደ ገለጽሁት እየተንቀሳቀሱ መሥራት የሚሰው ነበርና ሥራውን የት መጀመር እንዳለብን ዐሰብን። የምንሠራበትንም ቦታ እንዲያሳየን እግዚአብሔርን ጠየቅነው። መልሱ እኛ ከጠበቅነው ፈጥኖ ከጳውሎስ የመቄዶንያ ጥሪ መልስ በማያንስ

ግልጽነት መጣልን። በጥቂት ጊዜ ውስጥ አንድ ወጣት ወደ ቤታችን መጣና ስሙ አሰፋ እንደሚባል ራሱን አስተዋወቀን። ለመንግሥት ሀኪም ቤት ዘበኝነት ሥራ ለመቀጠር ፈተና ከወሰደበት ከመሀል ሜዳ ከተማ የመጣ መሆኑን ነገረን። የነገሮች ከተገመተው በላይ መዘግየት የተለመደ ነው። ስለዚህ ይህ ወጣት የፈተና ውጤቱን ለማወቅ ለብዙ ወራት መሐል ሜዳ ውስጥ እየጠበቀ መቈየት ነበረበት።

እስከዚያው ድረስ ጊዜውን ማሳለፍ እንዲችል በዶ/ር ካናታ ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጀመረ። አሰፋ ከፍተኛ ፍላጎት ስለ ነበረው አንድም ቀን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቀርቶ አያውቅም ነበር። ብዙም ሳይቈይ ፈተናውን እንዳለፈና ሥራም እንዳገኘ ዐወቀ፤ ጌታ ኢየሱስንም ዐውቆ ዐዲስ ሰው ሆነ። ስላገኘውም ዐዲስ ደስታ ለእኛ በሚነግረን ጊዜ ዕጥፍ ድርብ የደስታ ስሜት ይታይበት ነበር።

አሰፋ የሰማውን ወንጌል ወደ ትውልድ ቦታው ወደ ቀያ ሄደን ለጎረቤቶቹ እንድንነግራቸው ፈለገ። ጎረቤቶቹ ወንጌልን በራሳቸው ቋንቋ ከሰሙ ልክ እንደ እርሱ ኢየሱስን ወደ ማወቅ እንደሚመጡ ርግጠኛ ነበር። እኛ ግን ለጊዜውም ቢሆን ትንሽ ጥርጣሬ ገባን። ከመሐል ሜዳ 32 ኪ.ሜ. ርቆ ወደሚገኘው ወደ ቀያ ባንሄድም እንኳ በዚያ ቦታ ለአራት ዓመት ያህል ወንጌልን ስንሰብክ ቈይተናል። በዚያ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት ምን እንደ ሆነ በእውነት የተረዳ አንድ ሰው እንኳ አልነበረም። ነገሩን ካረጋገጥን በኋላ ልንጸልይበት ወሰንን። አሰፋም ወደ ቤቱ ተመልሶ ሄደ።

እነከናታ ሳምንታዊውን የጎሙስ ዕለት ህክምና ሊሰጡ ሲመጡ ስለ ዐዲሱ አማኝ ሊነግሩን በጣም ጓጉተው ነበር። የዐዲሱ አማኝ ስም አሰፋ ይሆንን ብለን ስንጠይቃቸው፣ እነሱም በተራቸው ተደነቁ። በቀያ ስለምንጀምረው ሥራ የጌታ ምሪት እንዲረን ከመሄዳቸው በፊት ዐብረን ጸለይን።

ከሁለት ቀን በኋላ አሰፋ እንደገና መጣ። በዚህ ጊዜ አንድ ረጅም ሙሉ በሙሉ የተጻፈበት ወረቀት ይዞ ነበር። የጽሑፉ ምንነት ሲጣራም ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በአማርኛ ቋንቋ ጽፈው የፈረሙበት ወረቀት ነበር። ወረቀቱ ለመማር የሚፈልጉ ሰዎችን ስም ዝርዝር ይዞ ነበር። ሰዎች ለመማር ፈቃደኛ መሆናቸውን ለእኛ የሚያሳይበት የተሻለ መንገድ ብሎ አሰፋ የተጠቀመበት ዘዴ በእያንዳንዳቸው ቤት እየሄደ በመንገር እንዲሰበሰቡ ማድረግ ነበር። የያዘው ስም ዝርዝር እምነቱን በግልጽ ያስረዳ ነበር።

በዚህ ጊዜ እኛ ምንም አልተጠራጠርንም። የመጀመሪያው ቅዳሜ ትምህርት የምንጀምርበት ቀን እንዲሆን ወዲውኑ ወሰንን። አሰፋም የጥሪ መልእክት ለሰዎቹ እንዲያስተላልፍ አደረግን። ትምህርት ለማስተማር በየቀኑ የ64 ኪ.ሜ. ደርሶ መልስ ጉዞ እናደርግ ነበር። ነገር ግን መኪና መንገዱ ብዙም አመቺ አልነበረም። ከዚህም የተነሣ መንገድ ላይ የተለየ ችግር ካልገጠመን በቀር ቀያ ለመውረድ አንድ

ሰዓት ይወስድብናል። ነዳጅ በጣም ውድ ስለ ነበረ ከአዲስ አበባ ማምጣት ነበረብን። አጠቃቀማችን ጥንቃቄና ቁጠባ የተሞላበት ነበር። ከመንገዱ ወጣገባነት የተነሣ በጣም ስለሚደክመን ትንሽ ብርታት ለማግኘት ለተወሰነ ጊዜ ማረፍ ተገቢ ነበር።

ይህን ሁሉ ማድረግ ያነሰን ይመስል፣ ልናደርገው የሚገባን አንድ ሌላ ነገር ነበር። የቀያን ሕዝብ በደንብ ለማወቅ ብቸኛው መንገድ ዐብሮ መኖር መሆኑን ተገነዘብን። ከዚያም የመጠለያ ድንኳናችንን፣ ለሳምንት የሚስፈልገንን ምግብና ሌሎች ነገሮችን እንዲሁም የእጅ ሥራ ማስተማሪያ መሣሪያዎቻችንን በላንድሮቨር መኪናችን ላይ ጭነን ወደ ቀያ ተጓዝን።

ቀያ እንደ ደረስን በተባለው ቦታ ሰዎች ተሰብስበው ሲጠብቁን አገኘናቸው። ሁሉም በሚችሉት መንገድ ሁሉ እኛን ለመርዳት ፈቃደኞች ነበሩ። ድንኳኑን ለመትከል ተሸካሚ የሚሆኑ ሁለት የባሕር ዛፍ አጣናዎችን ቈረጡ። የጣሪያውን ሸራ በመሬት ላይ ዘረጋነው፤ ካስማዎችንም በዙሪያው ተከልን።

በመጨረሻ ሰዎች በሁለት ወገን ሆነው የተቈረጡትን አጣናዎች በሸራው ላይ በሚገኙት የብረት ቆቦች (ቀደዳዎች) ውስጥ አስገቡ። ከዚያም አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ብለው ከቈጠሩ በኋላ ዙሪ ያውን ገፍተው ሲይዙት ድንኳኑ ቆመ።

በየቀኑ የነበረን የትምህርት ክፍለ ጊዜ በርከት ያሉ ሰዎችን ያካተተ ነበር። በአካባቢው ከነበረው ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ የተነሣ ሁሉም ሰዎች ለመጻፍ፣ ለማንበብና እንደዚሁም የሂሳብ ስሌቶችን ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። መሠረታዊ የሆነውን ለማስተማር ይረዳን ዘንድ የመንዝ ተወላጅ የነበረውን ሞልቶትን ለአስተማሪነት ቀጠርነው። ይህ ሰው ቀደም ሲል በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግል ዲያቆን ነበር። ቄይቶ ግን ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ ሄደ። ከዚያም እያለ ለኑሮ የሚሆነውን ሥራ አገኘ።

ሞልቶት የተማረው እስከ ፭ኛ ክፍል ቢሆንም፣ ይህ የትምህርት ደረጃ ለመሠረተ ትምህርት አስተማሪነት በቂ ነበር። ይህንኑ ሥራ እየሠራ ነበር ከእኛም ጋር የተገናኘው። ለዚህ ወጣት ምቹ የሆነውን የአዲስ አበባን ኑሮ ትቶ መምጣት ቀላል ባይሆንም፣ ወደ ትውልድ ቦታው ተመልሶ ለሕዝቡ ትምህርት ለመስጠትና ለመመስከር ደስተኛ ነበር።

የእጅ ሥራ ትምህርት ማስተማርም ሌላው የየቀኑ ተግባራችን ነበር። ሁሉም የመንዝ ሴቶች ጥጥና የበግ ፀጉር በእንዝርት የመፍተል ችሎታ አላቸው። በመጀመሪያ ፀጉሩን በእጃቸው ይፈቱታል። ይህ ደግሞ በጣም አሰልቺና ብዙ ጊዜ የሚፈጅ ተግባር ነው።

ሬይ በአሜሪካ ያሉ መንደፊያ ሚዶዎች የምንላቸው በኢትዮጵያም እንደሚገኙ ዐሰበ። ከዚህም በመነሣት የእጅ መፍቻ

መሥራት እንደሚችል ተረዳ። ሁለት ትናንሽ አራት ማእዘን ጠፍጣፋ ጥርብ ዕንጨቶች ወሰደ፣ በእነሱም ላይ ጫፋቸው ቂልመም ያሉ ሽቦዎችን ሰካባቸው። በእዚህ የእጅ መፍቻ በሰዓት የሚሠራው ሥራ በደቂቃ ውስጥ መሥራት ተቻለ።

መቼም ባልለመደ ሕዝብ ዘንድ ለውጥ በጣም አስደንጋጭ ነው። ስለዚህ ነገሮችን በዝግታ ያዝናቸው። ሴቶች ወደ እኛ እየቀረቡ በእጅ መፍቻው ከፈቱ በኋላ ይፈትሉ ነበር። እኛም ትምህርቱን ስንጨርስ አንዳንድ መፍቻ ሰጠናቸው።

በየሁለት ሳምንቱ ዶ/ር ጀሪና ሳም የሕክምና ሥራ ለመሥራት ይመጡ ነበር። ጀሪ በመስክ ላይ ለእንስሳት ሕክምና ሲሰጥ፣ ሳም ደግሞ በድንኳኑ ውስጥ ሰዎችን ያክም ነበር። ምንም እንኳ ሳም የሚይዘው መድኀኒት በአንድ ሻንጣ ውስጥ ያለና መጠነኛ ቢሆንም፣ ሁሉንም ሰው እንደ ምንም ብሎ ለመርዳት ይችል ነበር። በዚህ ሕክምና መገልገል የማይችለው ከ20 ሰዎች አንድ ቢሆን ነው።

የዓለም ጤና ድርጅት ፈንጣጣን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥፋት ባደረገው ዘመቻ እኛም የበኩላችንን ርዳታ አድርገናል። የመሬቱ መልከአ ምድር ወጣ ገባ ከመሆኑ የተነሣና መንዜዎች ለመጤዎች ካላቸው የጠላትነትና ያለማመን ተፈጥቶአዊ ባህርይ አኳያ ችግሮችን ለመፍታተ በጣም ያዳግታቸው ነበር። ክትባት በመስጠትና ስለ በሽታው መስፋፋት ሪፖርት በማድረግ እንረዳቸው ነበር።

ከሕዝቡ ጋር እየኖርን ሳለን በዚያ አካበቢ ብዙ የታመሙ ሰ ዎች መኖራቸውን ተመልክተናል። ከበሽተኞች ውስጥ ብዙዎቹ ሥር የሰደደ በሽታ ያለባቸው ናቸው። ሰዎቹ ከችግሩ ጋር ለመኖር ራሳቸውን አሳምነውታል። በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ያሉትን ልንረዳቸው በመቻላችን በጣም ደስተኞች ነበርን። ይህ በርግጥ እኛ ለነርሱ ያለንን በጎ ሐሳብ ማሳያ ትክክለኛ መንገድ ነበር።

ሊን ግሮስም ሁል ጊዜ ለገበሬዎች የሚታደል ዘርና እንደዚሁም የሚሸጡ የእርባታ በጎችና ዶሮዎች እየያዘ ይመጣ ነበር። የዶሮዎችና የበጎች ዋጋ ተመጣጣኝ ስለ ነበረ ገበሬዎች ገዝተው ለማርባት ዐቅሙ ነበራቸው። ለመብላት ግን ዋጋው ውድ ሆባቸው ነበር።

ለእኛ ትልቁ አጋጣሚያችን በየቀኑ የምናሳየው ፊልም ነበር። አንድ ትንሽ በመኪና ባትሪ የሚሠራ ፊልም ማሳያ መሣሪያ ነበረን። እሱን በመጠቀም ቀለል ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ማታ ማታ ለሰዎቹ እናሳያቸው ነበር። ምንም እንኳ መንዜዎች ሁሉ ኦርቶዶክስ ክርስቲያች ቢሆኑም፣ በጣም የታወቁት ብሉያውያት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እንኳ ለእነርሱ ዐዲስ ነበሩ። ሲኒማውን ሲመለከቱ ረጃጅም ካባ የለበሱና በባዶ እግራቸው ልክ እነርሱ ዘወትር የሚሠሩትን ሥራ ሲሠሩ ሲያዩ፣ ለካስ ሲኒማ ወደ መንዝ የመጣው በመጨረሻ ነው አሉ። የነበራቸውን የአመለካከት ብዥታ ልናጠፋ አልሞክርንም።

ፀሓይ ስትጠልቅ ሁሉም የቀኑን ሥራቸውን ያቆማሉ። ወደ ትልቁ ድንኳን ይመጣሉ። እረኞች በጎቻቸውን ወደ ቤት አስገብተው ይዘጉና ይመጣሉ። አንዳንዶች ከድንኳኑ ውጭ እንዲጣጡ ይተዉአቸዋል።

ወጣቶችም ሆኑ ሽማግሌዎች ሲኒማውን ተማርከውበትና ወደውት ነበር። የምሽቱን ታሪክ በሚመለከት ዘግይተው ለሚመጡና ታሪኩ ላልገባቸው ፊልሙ ይደገምላቸው ነበር። በዚህን ጊዜ መልእክቱን በደንብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በመሀል በመሀል እያቋረጥን ጥያቄዎችን እንጠይቃቸው ነበር። በመጨረሻ ላይ በደንብ እንዲያጤኑት ለማነሣሣት በፊልም ያዩትን ከአነርሱ ሕይወት ጋር እያዛመድን እናብራራላቸዋለን። ከዚያም ቀኑ በጣም ከመጨለሙ በፊት ወደየመጡበት እንዲሄዱ እናደርጋለን። ሰዎቹ ከማንኛውም የሌሊቱ አደጋ ለመከላከል የውጪ በራቸውን አጠባብቀው ወደ ቤታቸው ይገባሉ።

ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነርሱ ገባ፣ ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር፤ ሲተረጕምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያስረዳ፡- ይህ እኔ የምሰብክላቸው ኢየሱስ አርሱ ክርስቶስ ነው ይል ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 17÷2-3

ኦርቶዶክስ

በድንኳን ውስጥ ፕሮግራማችን በድፍረት የወሰድነው እርምጃ ለቀሳውስትና ለዲያቆናት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መርሐ ግብርን መጀመር ነበር። ጥናቱ ሁልጊዜ እሑድ እሑድ ጠዋት ከቅዳሴ በኋላ እንዲካሄድ ታቀደ። ምንም እንኳ ብዙዎቹ የስጋጃ ሥራ ተማሪዎቻችን ቀሳውስትና ዲያቆናት፣ ከቀሩትም መካከል በርከት ያሉት ወዳጆቻችን ቢሆኑም፣ ከአሁን በፊት ምንም ዐይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራም አላመቻቸንላቸውም። ፕሮግራሙን ሳናሳውቃቸው በማለት የተዳፈርን መሰለን። ማን ይመጣ ይሆን? እያልን በውስጣችን እንገረም ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እየመራን እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር አልነበረንም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያች መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ በሚነዱ ሰዎች እንደ ተጻፈ ይናገራሉ። ነገር ግን አብዛኞቹ ያላቸውን መጽሐፍ በግእዝ ቋንቋ ማንበብ እንጂ ትርጕሙን አያውቁትም በመንዝ ውስጥ ያሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ አላቸው። ነገር ግን ይዘቱን አይረዱትም። ከዚህም የተነሣ በሕይወታቸው ላይ ምንም ለውጥ አላመጣም።

ሚሲዮናዊው ድርጅታችን በመንዝ ውስጥ ሥራ ከጀመረ በኋላ ቀጥሎ በነበረው የክረምት ወቅት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለቀሳውስትና ለዲያቆናት የክረምት መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መስጠት ጀመረች። እኛም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶችን ለሥልጠናው እናቀርብላቸው ነበር። ከሠልጣኞቹ መካከል አብዛኞቹ ከዚያ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ በዐይናቸው አይተው አያውቁም ነበር። ከዚህ የተነሣ ደስተኞች ነበሩ። በማንኛውም ዐዲስ ነገር ላይ የጥርጣሬ መንፈስ ያደረባቸው ጥቂት ሰዎችም ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱሱ የፈረንጆች መጽሐፍ ቅዱስ ነው፤ ከእኛ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር አንድ አይደለም የሚል ወሬ በፍጥነት ተሠራጨ።

በዚያን ጊዜ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሪ የነበረው አንድ ወጣት መምህር አዲስ አበባ ሆኖ ይህን ወሬ ሰምቶ ለማስተባበል የተቻለውን ሙከራ ሁሉ አደረገ። ነገር ግን ነገሩ ቀደም ብሎ ተበላሽቶ ነበር። አንድ ቀን ይህ ሰው በመንፈስ ተነሣሥቶ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ እያየው ሰተት ብሎ በአቅራቢያው ወደምትገኘዋ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅድስተ ቅዱሳን ገባ። ቅድስተ ቅዱሳን ታቦት የሚቀመጥበት የተቀደሰ

ስፍራ ነው። በዚያ ስፍራ መምህሩ በግእዝ ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ አግኝቶ ለሕዝቡ አሳያቸው። አማርኛውንና የግእዙን መጽሐፍ ቅዱሶች ጐን ለጐን አስቀምጦ ተራ በተራ ከሁለቱም ለሰዎቹ አነበበላቸው። ከተነበበላቸው በኋላ በተለይ የግእዝ ቋንቋ የሚያውቁት የሁለቱም መጽሐፎች ትርጒም አንድ እንደ ሆነ ተረዱ። በመጨረሻም በማስረጃነት በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ገጽ ላይ ያለውን የአፄ ኃይለ ሥላሴን ፎቶግራፍና ያጸድቁበትን ፊርማ አሳያቸው።

በዚህም መሠረት ሕዝቡ መጽሐፍ ቅዱሱን እያወቀው መጣ። ለአብዛኞቹ የማወቅ ፍላጎት እንዲያድርባቸው በክረምት ወራት ጥናት ጊዜያቸው ያጠኑት ብቻ በቂ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ዕውቀት ለመቅሰም ከሌሎች በተለየ ሁኔታ የማወቅ ጕጕት ያደረባቸው ተማሪዎች ዐሥራ ሁለት ያህሉ ነበሩ። ለምን እንደ ሆነ ባናውቅም ሁሉም ቀያ ውስጥ የሚሩ ናቸው። ለቀሳውስትና ለዲያቆናት በተዘጋጀው በመጀመሪያው አሐድ ጠዋት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማን ማን ይመጣ ይሆን በማለት እየጠበቅን ሳለ፣ እግዚአብሔር ያመቻቻቸው ሁኔታዎች መንገዳችንን ያፋጥኑት ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች መሠረታውያንና በመጀመሪያ በጣም ቀለል ያሉ ነበሩ። በዚህም ባልተለመደ መጽሐፍ ውስጥ ትክክለኛውን የንባብ ሥፍራ ማግኘት እንዲቻል እያንዳንዱን ተሳታፊ ለመርዳት የተወሰነ ጊዜ በመውሰድ፣ ለአንዱ ትምህርት በተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ብቻ አተኩርን።

ተሳታፊዎች ብዙ ጥያቄዎችን ጠይቀዋል። የውጪ ሰዎችና የቤተ ክርስቲያን አባላት ስላልነበሩ፣ ማንኛውንም ነገር ሳይፈሩ ይጠይቁ ነበር። ሁላቸውም የዕውቀት ዕጥረት ያለባቸው እነርሱ ብቻ እንዳልሆኑ ተገነዘቡ። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና እውነቶችን ከዚህ በፊት ፈጽሞ ተምረው አያውቁም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ የሚያበቃው ስድስት ሰዓት ላይ ነበር። የከሰዓት በኋላው አገልግሎት እስከ ዘጠኝ ሰዓት አይጀምርም። ነገር ግን አብዛኞቹ እዚያው አካባቢ ይቈያሉ። እኛም እነርሱን በደንብ ልናውቃቸውና ልንቀርባቸው የቻልነው ያንኑ ጊዜ በመጠቀም ነበር።

ዐልፎ ዐልፎ ቆም ብለን ቁሶችንና ዲያቆናትን መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር ብቁ ነን ወይ? የሚል ጥያቄ ራሳችንን እንጠይቅ ነበር። ሬይ በባዮሎጂ ኤም ኤ ዲግሪ ነበረው፣ እኔ ደግሞ በሶሾሎጂ ቢ.ኤ ዲግሪ ነበረኝ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ መረጃዎች ለተጀመረው አገልግሎት ምንም ዐይነት ጥቅም እንደሌላቸው እናውቅ ነበር። ከዚህም በላይ ለሥነ መለኮት ጥናት ወደ ጎልደንጌት ሄደን ነበር። ነገር ግን አብዛኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ያገኘነው በክርስቲያን ቤተ ሰብ አባላት መካከል ስናድግ በየቀኑና በየሳምንቱ በሚካሄዱት ጥናቶች ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ሁልጊዜ እናነብ ነበር፤ በቤተ ክርስቲያን ከሚዘጋጁ የተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞችም ብዙ ጥቅም አግኝተናል።

ሁልጊዜ በቀላሉ የምንመልሰውን ጥያቄ እንኳ ስንጠየቅ ለመመለስ እንፈራና እንደነግጥ ነበር። ነገሩን አውጥተን አውርደን ማስተዋል ስንችል ግን አንድ አስተማሪ ያወቀውንና ሊመልሰው የሚችለውን ያህል እኛም እንዳደረግን ይሰማን ነበር። ስለዚህ ከእንዲህ ሁለቴ እነርሱን ማስተማራችን ትክክል እንደሆነ ርግጠኞች ሆንን።

የጌታ ደቀ መዛሙርት የትም ቢሆኑ ወደ አይሁድ ምኵራብ ሁልጊዜ በየሰንበቱ እንደሚሄዱ ሁሉ፣ እኛም እሑድ እሑድ ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንሄድ ነበር። ከእነርሱ የተለየ ላለመሆን እነርሱንም ነጻነት እንዲሰማቸው ለማድረግ በምንችለው ሁሉ የእነርሱን ባህል ለመከተል ሞክረናል።

በመንገዝ ያሉ አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ከጭቃና ከድንጋይ የተሠሩ ክብ ግንቦች ሲሆኑ፣ ጣሪያቸው በሳር የተከደነ ነው። በግንቡ መካከል ላይ ያለው ቀሳውስትና ዲያቆናት ብቻ መግባት የሚችሉበት ቅድስተ ቅዱሳን ነው። ዙሪያውን ያለው ክብ ክፍል ደግሞ ቄሶች ቅዳሴ የሚቀድሱበት፣ ዕጣን የሚያጥኑበት፣ ሌሎች ንዋያተ ቅዱሳትን የሚይዙበትና ቡራኬ የሚሰጡበት ክፍል ነው። ቅዳሴ የሚያስቀድስ ሰው ሁሉ ከግንቡ ሥር ይቆማል።

ሴቶች ፀጕራቸውን ሸፍነው፣ በቀኝ በኩል ባለው በር ሲገቡ፣ ወንዶች ደግሞ ጫማቸውን አውልቀውና (ካላቸው) ከበር ውጭ አስቀምጠው በግራ በር ይገባሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንዶችና ሴቶች በስስ መጋረጃ ተለይተው ይቆማሉ። ረጅሙ የቅዳሴው ሰዓት እስከሚያልቅ ድረስ ሁሉም መቋሚያቸውን ተመርኵዘው ይቆማሉ። መቋሚያው እንደ አስፈላጊነቱ ሊነሣም ሊቀመጥም ይችላል። ምንም ዐይነት መቀመጫ ወንበር የለም።

በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠባቂ ቅዱሳን እንዳሉ ሕዝቡ ያምናል። ቅዱሳኑ በሚውሉበት በየወሩ ዕለት ለእነርሱ ክብር ሲባል ምንም ዐይነት ሥራ አይሠራም። በዓመት አንድ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ከሩቅ ስፍራ እየመጣ የጠባቂውን ቅዱስ ዐመታዊ ክብረ በዓል ያከብራል። ይህ በዓል ሕዝቡ ሁሉ ዐዲስ ልብስ እየለበሰ የሚያከብረው ለየት ያለና ታላቅ በዓል ነው። አንዳንድ ጊዜ በእነዚህ ክብረ በዓላት ወቅት ከረጅሙ የቅዳሴ ጊዜ በኋላ በዓሉን ሊያከብሩ የመጡ ባለሥልጣናት ካሉ፣ ስብከት ወይም የምክር ንግግር ይደረጋል።

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለብዙ ዓመታት ከተከታተልን በኋላ ሕዝቡ ስለ እኛ የተገነዘቡት አንድ እንግዳ የሆነ ነገር እንዳለ ተናገሩ። በየሳምንቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሄድ ነበር። ሌሎች ሳይሆኑ በጣም ያረጁት ሰዎችና ከክህናት ጥቂቶቹ የእኛን ያለማቋረጥ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ በንቃት ይከታተሉት ነበር። ቁስም እንኳ ቢሆን የቅዳሴ ተረኛ ካልሆነ አብዛኛውን ጊዜ ይቀራል።

መጀመሪያውኑ ተልእኮአችን በቤታችን፣ በእጅ ሥራ ት/ቤትና በክሊኒኮች የሚካሄዱ ቀለል ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ወይም ስብከቶች ነበሩት። ቀደም ሲል ቤተ ክርስቲያን እየተከታተልን ሳለ

ከቅዳሴ በኋላ ከቤተ ክርስቲያናቸው ውጪ እንድንሰብክ ጥያቄ ቀርቦልን ነበር። የመጀመሪያው የአማርኛ ስብከት በጣም አስቸጋሪ ነበር። እንዳንዶችም እኛ የምንናገረው በሌላ ባዕድ ቋንቋ እንደ ሆነ በማሰብ ለመስማት ጥረት ማድረጋቸውን አቁመው ትከሻቸውን ይነቀንቁ ነበር። እኛ ግን መስበካችንን አላቆምንም።

ሁልጊዜ ከቅዳሴና ከስብከት በኋላ የሰባት፣ የአርባ፣ የዓመት ወይም ደግሞ የሰባት ዓመት መታሰቢያ ተዝካር አለ። የሟቹ ቤተ ሰቦች ወይም የቅርብ ዘመዶች ዳቦና ጠላ ይዘው ይመጣሉ። ጠላውና ዳቦው ለተሰበሰበው ሕዝብ ይታደላል። አያንዳንዱ ሰው «የሟቹን ነፍስ ይማር» ይላል። እኛን የበለጠ እየለመዱን ሲመጡ ከአነርሱ ጋር ተቀምጠን ቢንያስ ጥቂት ዳቦ እንኳ እንድንበላ ይገፋፉን ነበር። አብረናቸው ስንቀመጥ ከሳምንት ወደ ሳምንት ስለ አነርሱ ያለን መረዳት እየጨመረ ሄደ።

በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን በምንም ዐይነት ተቀባይነት አላገኘንም። በአብዛኞቹ ዘንድ የመፍራት ነገር ነበር። አንዳንዶቹ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ያልሆኑ መጨዎች መኖር ቤተ ክርስቲያናቸውን እንደሚያረክስ ያምናሉ። እንዲያውም ወደ ጠይበር ቤተ ክርስቲያን ብንሄድና ብናስቀድስ በድንጋይ ልንወገር እንደምንችል ወሬ ደረሰን። በርግጥ ጥሪ ካልተደረገልንና የቤተ ክርስቲያን ወይም የአካባቢ ጎበረቱ ሰብ መሪዎች ካላጀቡን በስተቀር ወደየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ዝም ብለን አንሄድም ነበር። ስለዚህ የጠይበር ሰዎች በዚህ ጕዳይ ላይ መጨነቅ አልነበረባቸውም።

ቀያ እያለን በቅርብ ወደሚገኙት ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ወደ አቃፌና ወደ ዝግባ እንሄድ ነበር። በመጨረሻው እሑድ ወደ ዝግብ ለመሄድ ዕቅደን ነበር። ነገር ግን ጎመሱ ቀን የአካባቢው ጎብረቱ ሰብና ድንኳናችን የተተከለበት መሬት ባለቤት የነበረው አስተናጋጃችን ከእርሱ ጋር ወደ አቃፌ እንድንሄድ ነገረን። በጕዳዩ ላይ እያሰብን ሳለን፣ ቄስ ግርማ መጥተው ወደ ዝግብ እንድንሄድ ያደረጉልንን ጥሪ እንደ ሰረዙት ነገሩን። እኛም ይህ ሁሉ ምን ምን ትርጕም እንዳለው ለማወቅ ዐሰብን፤ ከሞልቶትም ጋር በጕዳዩ ላይ ጸለይን። ከዚያ በኋላ ወደ የትኛውም ቦታ መሄድ ጥሩ መስሎ ስላልታየን፣ በዚያ ዕለት ጠዋት እቤታችን ቀረን። ቄይቶም ዝግባ ሄደን ቢሆን ኖሮ፣ እኛን ለመደብብ ዕቅድ ተይዞ እንደ ነበር ሰማን።

በቀሳውስት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት የነበረው የየሳምንቱ ክትትል ጥሩ ነበረ። ከስድስት ሳምንት በኋላ ጥናቱን ሳያቋርጡ ለተከታተሉት ሁሉ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱስ በመስጠት ደስ አሰኝናቸው። አብዛኞቹ ይህ መጽሐፍ ሲሰጣቸውና በእጃቸው ሲገባ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ስለ ነበር፣ በክብርና በደስታ ተቀበሉን። እንግዲህ የመጀመሪያዎቹ ዘሮች በዚህ መንገድ ተዘሩ ማለት ነው። እኛም እነዚህ ዘሮች ፍሬ ያፈሩ ዘንድ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል እንደ ሰጠን አረጋገጥን።

ምልክት

ከቀሳውስቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ያገኘነው ውጤት ከጠበቅነው በላይ ነበር። ከዚህም የተነሣ ያለንን ራእይ ማስፋት ጀመርን። በሕዝቡ ዘንድ እውነተኛ ተቀባይነትን ለማግኘት ዐሥር ዓመት መጠበቅ እንዳለብን ከመጀመሪያው ራሳችንን ያዘጋጀን ቢሆንም፣ ሚሲዮናዊው ቡድናችን ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ ገና ከስድስት ዓመት ትንሽ ጊዜ እንዳለፈው ነበር። በዚያ ጊዜ ሌላ ነገር መጠበቅ አልነበረብንም። ጌታ በልባችን ውስጥ ተስፋን ማቀጣጠል ጀምሮ ነበር።

በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረን አሠራር ያልተለመደ ስለ ነበር በርካታ ሰዎች በቅርብ ይከታተሉን ነበር። አንዳንዶቹ እንደዚህ ዐይነቱ አካሄድ እንደማያሠራ እርግጠኞች ነበሩ፣ ለእኛም ይህንኑ ለመንገር አልተጠራጠሩም ነበር። ሌሎች ደግሞ ምንም እንኳ ጥርጣሬ ቢያድርባቸውም መልካሙን ሁሉ ይመኙልን ነበር። የወደፊቱን ተስፋ ከወዲሁ በማየት የተደሰቱና እኛንም በብዙ መንገዶች የሚያበረታቱን ሌሎች ሰዎችም ነበሩ።

መጽሐፍ ቅዱስን የማወቅ ፍላጎት በቀያ እያደገ ሲመጣ እግዚአብሔር ለምልክት እንድንጸልይ ራእይን ሰጠን። ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር በምንሠራው ሥራ እግዚአብሔር እየሠራ እንደ ሆነ የሚያረጋግጥ ማኅተም ይሆነን ዘንድ አንዱን የቤተ ክርስቲያን መሪ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አደርጎ ለመቀበል እንዲገፋፋው እግዚአብሔርን ጠየቅነው። ይህን ጥያቄ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ስንችልም በብሩህ ተስፋ ተሞልተን ነበር።

ከጥቂት ቀናት በኋላ አንድ ቀን ቄስ ግርማ ወደ እኛ መጡ። እኒህ ሰው በራሳቸው ላይ የጠመጠሙት ነጭ ሻሽ ቄስ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ነበር። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ከእኛ ጋር ለመወያየት ብቻ ፈልጎ ሰው ወደ እኛ የመጣበት ያ ቀን የመጀመሪያ ቀን ነው። ቄስ ግርማ ምንም እንኳ የሃያ ስምንት ዓመት ወጣት ቢሆኑም የቤተ ክርስቲያን ዋና መሪ እንደሆኑ ተረዳን። ከእርሳቸው በፊት የነበሩት ቄስ ስለ ሞቱና ሌላው ደግሞ የሕግ ሚስታቸው ስለ ሞቶች ቄስ ግርማ (መምሬ ግርማ) የመሪነቱን ሥልጣን ያገኙት ከዐምስት ዓመት በፊት ነበር። በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሥርዐት መሠረት አንድ ቄስ የሕግ ሚስት ልትኖረው ይገባል። የሕግ ሚስት ከሞቶች በኋላ በቅስና አገልግሎቱ ለመቀጠል ሲፈልግ ይመከሩሳል።

ከዚያም ቄስ ግርማ አንድ የሚያስገርም ታሪክ ነገሩን። እኛም ረቂቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሥራ እንደገና ለማየት ቻልን።

በሕጋዊ መንገድ ቅስና ለመቀበልና ማዕረግ በአቡኑ (በጳጳሱ) ለመቀባት ቁስ ግርማ ወደ አዲስ አበባ መሄድ ነበረባቸው። በዚያ ቀን ከመሳ ኢትዮጵያ መጥተው ቤተ ክርስቲያንን በቅስና የማገልገል ሥልጣን ከጳጳሱ ከተቀበሉት ብዙ ቀሳውስት መካከል ቁስ ግርማ አንዱ ነበሩ። የቅስና ማዕረጉ የአሰጣጥ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ፣ ጳጳሱ እያንዳንዱ ቁስ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲገዛና እንዲሄድ አሳሰቡ። አብዛኞቹ የመጡት ከገጠር ስለ ነበረ መጽሐፉን ከዚያ ጊዜ በፊት በራሳቸው ቋንቋ ታትሞ በፍጹም አላዩትም ነበር።

መጽሐፉ የሚሸጠው 1.25 ዶላር ነበር። ዓመታዊ አማካይ ገቢ 100 ዶላር በሆነበት ሀገር ያ ዋጋ ውድ ነበር። ቁስ ግርማ ግን ለምን እንደ ሆነ ባይታወቅም አንድ መጽሐፍ ገዙ። የአቡኑን (ጳጳሱን) ማሳሰቢያ ሰምቶ በተግባር ላይ ያዋለ ሌላ ሰው ስለ መኖሩ ቁስ ግርማ አያወቁም ነበር። መጽሐፉን ወደ ቤታቸው ይዘው ከመጡ በኋላ የመጀመሪያውን ገጽ ማንበብ ጀመሩ። ሊገነዘቧቸው ያልቻሉ ጥቂት ነገሮችን ሲያነቡ ተመለከቱ። በርግጥ የበለጠ እያነበቡ ሲሄዱ ብዙ ጥያቄዎች እየተፈጠሩባቸው ሄዱ። ቁስ ግርማ ሊጠይቁትና ሊረዳቸው የሚችል ሰው ማንም አልነበረም። ከዚህም የተነሣ በመጨረሻ ንባቡን ለማቋረጥ ተገደዱ፤ ይኸውም እኛ ወደዚያ ቦታ እስከ ደረስንበት ጊዜ ማለት ነው።

ሁለቱንም ማለት መልሶቻችንንና ያሳየናቸውን መጻሕፍት በጥንቃቄ በመመርመር ማብራሪያ ለማግኘት ቁስ ግርማ ወደ እኛ መጡ። በየቀኑ ከባድ ከባድ ጥያቄዎችን ይዘው ተመልሰው ይመጡ ነበር። በመጨረሻም አንድ ቀን በጣም ተጨንቀው እንደ ነበረ ተገነዘቡ። ሁኔታውን በሥዕላዊ መንገድ በመግለጽም፣ «በግማሽ ራሱ ላይ ረጅም ጠጉር ያለውን፣ ግማሽ ራሱን ደግሞ የተላጨ ሰውን እንደምመስል ይሰማኛል» በማለት ተናገሩ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ቁስ ግርማ ከረጅም ጊዜ ልማድና በልባቸው ውስጥ መሥራት ከጀመረው የእግዚአብሔር መንፈስ የተነሣ በሁለት አቅጣጫ ተከፍሰው እንደ ነበር ነው።

«በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ሳምን የኖርሁት መዳን በጥምቀት የሚገኝ መሆኑን ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ልጆች ሁሉ ተጠምቀዋል፤ የሚጠመቁትም ወንዶች ልጆች በአርባ ቀናቸው፣ ሴቶች ደግሞ በሰማንያ ቀናቸው ነው። ይህም ማለት መንዜው ሁሉ ክርስቲያን ሆኗል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ሳነብ ግን አንድም ስፍራ ላይ ይህን ሐሳብ የሚናገር አላገኘሁም። በዚህ ፈንታ መጽሐፍ ቅዱስ መዳን የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው ይላል» በማለት ምሥጢራቸውን አካፈሉን። በመቀጠልም የሚከተለውን ነገሩን፤ ለመዳን ጎጢአትን መናዘዝ አስፈላጊ እንደ ሆነ አንብቤአለሁ፤ ስለ ጎጢአትም አንዳንድ ዐዳዲስ ነገሮችን ዐውቄአለሁ። ኦርቶዶክስ ክርስቲያን እንደ መሆኔ ጸምና ሃይማኖታውያን በዓላትን ማክበር ሕግን የምንጠብቅባቸው ሁለት ዋና ዋና መንገዶች እንደሆኑ ዐስብ ነበር። ከፋሲካ በፊት ሁለት ወር፣

ዐርብንና ረቡዕንም እንደምንጾም ታውቃላችሁ። ማንም ሰው ሥጋንና የእንሰሳት ተዋፅኦዎችን ማለት እንደ ወተት፣ ዓይብ፣ ቅቤና ዕንቁላል የመሳሰሉት በእነዚያ ቀኖች አይበላም። እኛ ቀሳውስትና ዲያቆናት በጾም ቀናት እስከ ከሰዓት በኋላ ድረስ ምንም አንበላም። በአንዳንድ የበዓል ቀናት ደግሞ ፈጽሞ አንበላም። የአመጋገብ ሕግጋትን በመጠበቅም ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጌአለሁ። ጎሊናዬም በዚያ ጉዳይ ላይ ንጹሕ ነው። ከዚያም በተጨማሪ ሃይማኖታውያን በዓላት አሉ። በወር ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ቀን አንድ የታወቀ ቅዱስን ለማክበር የተሰየመ ዕለት ነው። የተወሰኑትን በዓላት ማለት እንደ ቅድስት ማርያም ያሉትን ሁሉም ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ያከብሯቸዋል። ሌሎቹን በዓላት የሚያከብሯቸው ግን በቤተ ክርስቲያኑ አቀራቢያ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው።»

«ለእነዚህ የበዓል ቀናት የተደነገጉ ሁሉም ሰው በልቡ የሚያውቃቸው ሊደረጉና ላይደረጉ የሚገባቸው ሕግጋት አሉ። ከእያንዳንዱ ወር ውስጥ በግማሽ ቀኖች ከተወሰኑ ሥራዎች በስተቀር ሌላ ነገር ማከናወን ክልክል ነው። በእነዚህ ቀናት መሥራት የሌለብኝን ሥራ ሠርቼ ሕጉን እንዳልተላለፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጌያለሁ። ቁስ ስለ ሆንሁ ሰዎች በአትኩሮት እንደሚመለከቱኝ ዐውቃለሁ።»

መጽሐፍ ቅዱሴን ማንበብ ስጀምር ግን ዐዲስ ነገር አገኘሁ። በአሪት ዘፀአት ላይ የሚገኙት ዐሠርቱ ትእዛዛት ነበሩ። ምንም እንኳ እኛ ኦርቶዶክሳውያን ብዙ የአሪት ሕግጋትን ማለት ምን ዐይነት ሥጋ መብላት እንዳለብንና እንስሳትን እንዴት ማረድ እንደሚገባን ብናውቅም፣ ስለ እነዚህ ዐሥር ትእዛዛት የሚናገር ማንም ሰው የለም።»

«አንዳንዶች ትእዛዛት ይኸውም «አትግደልን» የመሳሰሉት ሚዛናውያን ናቸው። የቀሩት ማለት «በውሸት አትናገር» እንደሚለው ያሉት ግን አስገርመውኛል።»

«መንዝ ውስጥ መዋሸት አለብህ አለበለዚያ ትታሰላለህ። ሁልጊዜ አንድ ሰው ጥያቄ ሲጠይቅ ለመደራደር መጀመሪያ ይዋሻል። ከብዙ ንግግር በኋላ እውነቱ በጣም አስፈላጊ ከሆነ፣ የምትናገረው እውነት ለመሆኑ በመሐላ ማረጋገጥ ይኖርብሃል። በርግጥ መሐላውም ቢሆን ታማኝነትን የሚያረጋግጥ አይደለም።»

«ሌላው ደግሞ የዝሙት ጉዳይ ነው። ዝሙት በመንዝ የተለመደ ነው። ሴት እንደ ጥሩ ሚስት የምትቈጠረው፣ ልጆች መውለድ የምትችል ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህም የትዳር ጥሩና ዘላቂ ዋስትናው ሴቲቱ ከጋብቻው በፊት መውለድ እንደምትችል ማረጋገጥ ነው። መንዝ በጣም ቀዝቃዛ አገር ነው። የመንዝ ወንዶችም ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋዋሪዎች ናቸው፤ ስለሆነም ጥሩ እንግዳ ተቀባይ ለእንግዳው ሁልጊዜ ጥሩ የመኝታ ጓደኛ እንዲያዘጋጅለት ይጠበቃል።»

«ዐሥርቱ ትእዛዛት በቂ እንዳልነበሩ ሁሉ፣ ጌታ ኢየሱስ ክፉ ነገርን ማሰብም እንኳ ኀጢአት መሆኑን ተናግሯል። ኀጢአት ምን

እንደ ሆነ እስካሁን ድረስ አላውቅም ነበር ለካ የሚል ሐሳብ ወደ ውስጤ ይመጣ ጀመር። እስካሁን የማምነው አንድ ሰው ከመሞቱ በፊት ቅዱስ ቊርባን ከወሰደ፣ ከኀጢአቱ ሁሉ እንደሚነጻ ነበር። እኔም ቂስ እንደ መሆኔ፣ ትልቁ ሥራዬ ሊሞት ለተቃረበ ሰው በቶሎ ደርሼ ቅዱስ ቊርባንን ለመጨረሻ ጊዜ መስጠት ነው።»

«አሁን ግን ከዚያም በላይ እንደሚያስፈልግ ተረድቻለሁ። ኀጢአትን መናዘዝ ብቻ ሳይሆን፣ በእውነት ክልብ ተጸጽቶ ንሰሐ መግባት አስፈላጊ ነው፤ ይኸውም አሁን እንደ ተገነዘብሁት ኀጢአትን መሥራት ማቆም ማለት ነው። ኀጢአትን ይቅር ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነውና። ኀጢአታችንን ይቅር እንዲለን ለመለመን እስክንሞት ድረስ የሚጠብቀን አይመስለኝም።»

ቂስ ግርማ ምን ማድረግ እንዳለበትና የልብ ዕረፍትን ይሰጠው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር በአንድነት እንድንጸልይ ጠየቀን። በሁለት መንገዶች ላይ እየተጓዝ እንደ ሆነ ስለ ተረዳ አንዱን መምረጥ ነበረበት። በቀያ የነበረን ጊዜ እንዳበቃ ወዲያውኑ በፀሓይ ሲና ወደሚገኘው መኖሪያ ቤታችን ተመለስን። ወደዚያ ከመሄዳችን በፊት ከምንሰጠው የተልእኮ ኮርስ ውስጥ «የደኅንነት መንገድ» የሚለውን አንደኛውን መጽሐፍ ለቂስ ግርማ ሰጠነው።

ከሁለት ሳምንት በኋላ በከሰዓት በኋላው ጊዜ ቂስ ግርማ ወደ እኛ አቋርጦ ሲመጣ ስንመለከት በጣም ተገረምን። ከቀያ ፀሐይ ሲና ቢያንስ የሦስት ሰዓት እግር መንገድ ያስኬድ ነበር። ይህንን አድካሚ ጉዞ ያደረገው ምን ያህል አስፈላጊ ነገር ቢኖር ነው ብለን ዐሰብን። ያጠናቀቀውን የጥናት ኮርስ በእጁ ጥብቅ አድርጎ ይዞት ነበር፤ ነገር ግን ወደ እኛ መምጣቱ ከዚያም በላይ ለሆነ ምክንያት እንደ ሆነ ጠረጠርን።

በአእምሮአችን የነበረውን ጥያቄ ወዲያውኑ መለሰልን። ቂስ ግርማ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ እዛፍ ሥር ሲጸልይ ላለ ሕይወቱን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ አሳልፎ ለመስጠት ወሰነ። ኀጢአተኛ እንደ ሆነ በመገንዘብ ልቡን ለእግዚአብሔር አስረከበ። የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅር ባይነት እየተለማመደ ሲመጣ፣ ደስታ ውስጡን ያጥለቀልቀው ነበር። ባገኘው ዐዲስ እምነት የተጐናጸፈውን ደስታ ዐብረን በመካፈላችን በጣም ደስተኞች ነበርን። ከብዙ ሰዓታት በኋላ ተሰነባብተን ቂስ ግርማ ወደ ቤቱ ተመለሰ። እግዚአብሔር የሁለታችንንም ጸሎት መለሰልን። ቂስ ግርማ ዐዲስ ሕይወትን አገኘ፤ እኛም ምልክታችንን አየን።

ወዲያውኑ የተለያዩ ለውጦችን በሕይወቱ መመልከት ጀመርን። እሑድ ከቅዳሴ በኋላ ቂስ ግርማ ዐጭር ስብከት ሰበከ። አንዳንዶች ተአምረ ማርያምን ባለማንበቡ ቢቃወሙትም እርሱ አይከራከርም ነበር። ከተለመደው የጥንት መጽሐፍ እየጠቀሰ ሕዝቡን እንዲህ ይላቸው ነበር፤ «ማርያም ማን እንደ ነበረች ሁላችሁም

ታውቃላችሁ። ለተለየ ሥራ በእግዚአብሔር የተመረጠች ወጣት ሴት ነበረች። የተመረጠችበት የተለየ ሥራ ልጅ መውለድ ነበረ። የተወለደው ልጅ ማን እንደ ነበር ታውቃላችሁ? የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ነበር።» ቂስ ግርማ ይህን እንደ መግቢያ ተጠቅሞ መዲን በክርስቶስ እንደ ሆነ አስረድቶ ስብከቱን ጨረሰ።

የተቃወሙት የተወሰኑ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን እርሱ ለተቃውሞ ዐዲስ አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስን ከዐምስት ዓመታት በፊት ማንበብ ሲጀምር ሁለት ትንሽ ልጆቹን ዳንኤልና ዮናስ ብሎ እንደሚጠራቸው ወስኖ ነበር። እንዲህ ዐይነት ነገር በመንዝ የተለመደ አልነበረምና ዘመዶቹ በጣም ዐዘኑበት። እነዚህ የመጠሪያ ስሞች ቤተ ሰብ ለልጆቹ ያለውን ተስፋ የሚያሳዩ ሲሆኑ፣ ኩራትንና የበላይነትን ስሜት የሚያሳዩ ሌሎች ስሞች ማለት እንደ «ግዛቸው»፣ «ንጉሤ» እና ድፋባቸው የመሰሰሉት የተለመዱ ናቸው። ነገር ግን ዳንኤልና ዮናስ እግዚአብሔር በቂስ ግርማ ላይ ያሳረፈውን እጅ የሚያረጋግጡ ሕያዋን ምስክሮች ሆነው ቀሩ።

ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ከተቀበለ ብዙም ሳይቈይ ከእኛ ጋር በኅብረት ለመጸለይና ለመጫወት በድጋሚ መጣ። ዐዲስ ሽክም ነበረበት። ቂስ ግርማ ባለቤቱና ልጆቹ ክርስቶስን እንዴት ማወቅ እንዳለባቸው አሳስቦት ነበር። ምንም እንኳ በየሳምንቱ ቢቀድስም፣ ለሚናገረውና ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ዐዲስ ትኵረት ይሰጥ ነበር። የቅዳሴው ሥርዐት በራሱ ጥሩ ነበር፤ ይሁን እንጂ በግእዝ ቋንቋ ይፈጸም ስለ ነበር ለማንም አይገባውም። ከዚህም በላይ ከባህሉ ጋር አብረው ያደጉ ጥሩ ያልሆኑ ልማዶች ነበሩ።

ቂስ ግርማ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ከተቀበለበትና ለእርሱ መኖር ከጀመረበት ቀን አንሥቶ ብዙ ሰዎች ጀርባቸውን ሰጥተውታል። አንዳንዶቹ እንዲያውም መጤ የሆነ አካሄዱን ካላረመ በእርሱና በቤተ ሰቡ ላይ ጉዳት እንደሚደርስባቸው ያስፈራሩት ነበር። ከአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚደርስበት ተቃውሞም ግን ከበድ ያለ ነበር።

ከዚህም የተነሣ ቂስ ግርማ አሳዛኝ ውሳኔ ላይ ደረሰ። በመንዝ በክርስቶስ እንደገና መወለድ የማይታሰብ ነገር ነው። የነበረው ብቸኛ መፍትሔ ንብረቱን፣ ዘመዶቹንና ጓደኞቹን ትቶ ባለቤቱንና ልጆቹን የሃይማኖት ነጻነት ወዳለበት ስፍራ ይዞ መሄድ ነበር።

ከዚያም እኛ ሚሲዮናውያን በእነዚያ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ዓመታት አንድ ላይ ሆነን እንድንጓዝ ያደረገንን ዐላማ ነገርነው። መንዝ ጨለማ የሰፈነበት አገር እንደ ነበር በተረዳን ጊዜ እግዚአብሔር ብርሃንን ይልክልን ዘንድ እንጸልይ ነበር። እንዲያውም እግዚአብሔር ከኦርቶዶክሳውያን ጋር የነበረውን ሥራችንን እንደ ወደደው እንዲያረጋግጥልን ዳግም የተወለደ አማኝ እንዲያሳየን ጸልየን ነበር። እግዚአብሔር በጨለማ ውስጥ ትንሽ ወገግታ በማሳየት ጸሎታችንን መለሰልን።

ያች ትንሽ ብርሃን እንዴት ያለ ታላቅ ለውጥን አመጣች! አሁን ፈጽሞ ጨለማ ያለ አይመስልም። እግዚአብሔር አንድ ትንሽ ነበልባልን ማቀጣጠል ከቻለ፣ ለበለጠ ነገር ልናምነው አንችልምን? ዐላማችን ቂስ ግርማን እየሳበውና እያጽናናው እንደ ሆነ ስንመለከት፣ ተስፋችን መታደስ መጀመሩን መገንዘብ ቻልን። ልክ እንደ ቂስ ግርማ ሁሉ የብዙ ሰዎች ዐይን ለእውነት የተከፈተ እንዲሆን በአንድነት ጸለይን።

አይሁድ ግን የሚያመልኩትን የከበሩትንም ሴቶችና የከተማውን መኳንንት አወኩ፣ በጳውሎስና በበርናባስም ላይ ስደትን አስነሥተው ከአገራቸው አወጡአቸው። እነርሱ ግን የእግራቸውን ትቢያ አራግፈውባቸው ወደ ኢቆንዮን መጡ።

የሐዋርያት ሥራ 13÷50-51

የእግርን ትቢያ ማራገፍ

በድንኳን በምናገለግልባቸው በእነዚያ የመጀመርያዎቹ ወራት ሞልቶት ቀኝ እጃችን ነበር። እርሱ ነገሮችን በሁለቱም ገጽታ ማየት ይችላል። ዐሥር ዓመት እስኪሞላው ድረስ ለዲያቆንነት እየተማረ በመንዝ ይኖር ነበር። ከዚያም አዲስ አበባ ለትምህርት ሄዶ ክርስቶስን አገኘ። ምንም እንኳ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር ባይችልም፣ ያልተረዳነው ነገር ካለ ባለን የተወሰነ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ተጠቅሞ ለማስረዳት ጥረት ያደርግ ነበር። ከሁሉም በላይ ባህሉን እንድናውቀው ረድቶናል። በተለይ ከተከናወኑ ነገሮች በስተጀርባ ያለውን ነገር እየተረዳን ስንሄድ የበለጠ ትርጉም ይሰጠን ጀመር።

የሞልቶት ወደ መንዝ መምጣት የጸሎታችን ቀጥተኛ ምላሽ ነበር። ከዓመት ፈቃድ ተመልሰን አዲስ አበባ የአማርኛ ቋንቋ እየተማርን ሳለ፣ በመንዝ አንድ ክርስቲያን የሆነ ረዳት ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔርን እንጠይቀው ነበር። በአዲስ አበባ የነበሩትን ጓደኞቻችንን የሚያውቁት ሰው እንዳለ ጠየቅናቸው። ጥያቄው ትልቅ ጥያቄ ነበር ምክንያቱም የከተማን ኑሮ ለምዶ በፈቃደኝነት ወደ ገጠር ተመልሶ ለመኖር የሚፈልግ ሰው አጋጥሞን አያውቅም። በመንዝ የመንግሥት ትምህርት ቤቶችና ጤና ጣቢያዎች እንዲሠሩ የተመደቡ ምሩቃን ከዚያ ቦታ ወደ ሠለጠኑበት ቦታ የሚያመልጡበትን ጊዜ በጉጉት ይጠባበቁ ነበር።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አንድ ጓደኞችን ሞልቶትን ወደ እኛ አመጣው። አባቱ በቅርብ ጊዜ በሞት የተለየው ሲሆን፣ እናቱ ደግሞ በመንዝ ብቻዋን ቀርታ ነበር። ሞልቶት እናቱን ሄዶ መርዳት እንዳለበት ተሰማው። በተጨማሪም ክርስቲያናዊ እምነቱን በመንዝ ለመመስከር ጓጉቶ ነበር።

ምንም እንኳ እስከ ስድስተኛ ክፍል ብቻ የተማረ ቢሆንም፣ ቋንቋ የማስተማር ጥሩ ችሎታ እንዳለው ዐወቅን። በተጨማሪም ዐዲስ ያልጠበቅነው ነገር አገኘንበት፣ ሞልቶት የተሰጠ ሰባኪ ነበር። ዐብሮን በተገዘበት ቦታ ሁሉ በተደጋጋሚ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዲያካፍል ይጠየቅ ነበር። በምንም ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ቢገኝም፣ ሁልጊዜ የተናገረው ጠቃሚ ነገር አለው። ማንኛችንም ስንናገር ሰዎች ካልተረዱን፣ ሞልቶት ነገሮችን ግልጽ ያደርግ ነበር። እግዚአብሔር እንደ ላከው ምንም ጥርጥር አልነበረንም።

እግዚአብሔር በመንዝ በሕይወታችን ስለሚሠራው ሥራ ሦስታችን አንድ ላይ በየቀኑ ስንጸለይ በጣም መቀራረብ ጀመርን። ወደ መንዝ ከተመለስ ጀምሮ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ለመምራት በልቡ የሚቀጣጠል እሳት እንዳለ አንድ ቀን ተናገረ። ሞልቶት ምን ለማለት እንደ ፈለገ ገባን።

እንዳቀድነው በቀያ ለስድስት ሳምንት ቈየን። ሁሉም በየቤታቸው ያለውን ሥራ ትተው ለመማር እንደ መጡና አሁን ወደ ተለመደው የቤት ውስጥ ሥራ ወደ ዕርሻቸው የመመለሻ ጊዜ እንደ ደረሰ ተረዳን። ድንኳኖቻችንን አጣጥፈን ወደ ፀሐይ ሲና ተመለስን። የቤታችንን ምቾት እንደገና ማግኘት ጥሩ ነበር፤ ነገር ግን በዚያ ለመቈየት ብዙም አልጓጓንም። በቀያ የእግዚአብሔርን ሥራ ማየት ጀምረን ነበርና የትልቅ ነገር ጅማሬ ይሆናል ብለን ዐሰብን። ቀጥሎ የት መሄድ እንዳለብን እንዲያሳየን እግዚአብሔርን ጠየቅነው።

ከጥቂት ቀናት በኋላ የውኽይ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ዋና ቄስ ቤታችን መጣ። እርሱ ወዳለበት ስፍራ ሄደን እንድናስተምር ይለምነን ነበር። ወንዙን አቋርጦ ወደ ውኽይ ለመሄድ ከፀሐይ ሲና ዐምስት ማይል ይርቅ ነበር። ጀሪ ቤድሶል እሑድ እሑድ ቅርብ በሚገኘው በሙሽላህ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ያስተምር ነበር ነገር ግን ወደ ውኽይ የሄደ ሰው አልነበረም። በሚቀጥለው ቅዳሜ ተስማምተን ብዙ ዕቃ ሳንጭን ለአርባ ዐምስት ደቂቃ በወንዝ ውስጥ አቋርጠን በጣም በታረሱት ሜዳዎች ላይ ተጉዘን በተባለው ቦታ ላይ ደረስን።

በተባለው ቦታ ላይ ስንደርስ ማንም አልነበረም። የሆነ ሆኖ ከዚህ በፊት በቋንቋ አስተማሪነት ያሠለጠናቸው የተወሰኑ ሴቶች ቦታው ላይ ደረሱ። ሁለት ሳምንት ማስተማር አቋርጠው ስለ ነበር ልንረዳቸው በመምጣታችን ደስተኞች ነበርን።

በትክክለኛው ቦታ ላይ እንደ ደረስን ካረጋገጥን በኋላ ዕቃችንን ማራገፍና ማስተካከል ጀመርን። እንደ ተለመደው መጀመሪያ የራሳችንን ትንሽ ድንኳን ዘረጋን። በመቀጠልም ትልቁን ድንኳን ተከልን። የመጀመሪያው ሥራ እንደ ጣራ የሚያገለግለውን ሽራ መዘርጋት ነበር። በዚህም ጊዜ ብዙ ሰዎች ምን እየተካሄደ እንደ ሆነ ለማየት መጡ። በጥንቃቄ ቋሚዎቹንና ማሠሪያ ገመዶቹን በየቦታቸው በማድረግ ሥራችንን ቀጠልን። በመጨረሻም ድንኳኑን አቆምነው።

ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብን እያሰብን ሳለ የተወሰኑ ቄሶችና ዲያቆኖች በኰረብታው ላይ ወደ እኛ ሲመጡ ተመለከትን። ከሩቅ እነማን እንደ ሆኑ ዐወቅን ምክንያቱም ማዕረጋቸውን የሚያሳየውን ነጭ ሻሽ በራሳቸው ላይ ጠምጥመው ነበር። በመጨረሻ በድንኳን ተ ከላው ሥራ እያገዙን መቀጠል እንደምንችል በማሰብ ወደ እኛ በመምጣታቸው ተደሰትን።

ወደ ውኽይ እንድንሄድ የጋበዘንን ቄስ በዐይናችን ፈለግነውና ከቄሶቹ ኋላ ስናየው ተረጋጋን። ነገሩን እንደሚያስተካክለውም

ርግጠኞች ነበርን። ነገር ግን በጥንቃቄ ስንመለከታቸውና ስናዳምጣቸው እውነቱ ተገለጠልን፤ ሁሉም ሰክረው ነበር።

በኋላም ከጠዋት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ተዝካር እንደ ነበረ ተረዳን። ተዝካር ለሞተ ሰው ክብር እንደ መታሰቢያ የሚዘጋጅ ዓመታዊ ድግስ ነበር። ሟቹ ሀብታምና ሥልፍ ሰው ከነበረ ብዙ ምግብና መጠጥ ይቀርብ ነበርና ሁሉም ማለቅ ነበረበት። አንዳንድ ጊዜ ብዙ ሰዓት ይፈጃል ልክ እንደዚያ እንደ ቅዳሜ ዕለቱ ዐይነት ማለት ነው። ውጤቱ በቀላሉ በግልጽ ይታይ ነበር። ከእነርሱ ምንም ዐይነት ርዳታ እንደማናገኝ እውን ነበር።

ሁኔታውን ራሳችን ለማረጋጋት ወሰንን። ሁሉም በአንድ ጊዜ ከሚጮኹ፣ መናገር የሚፈልጉትን ተቀምጠው በየተራ እንዲናገሩ ጠየቅናቸው። በሚገርም ሁኔታ ማንም አልተቃወመም ነበር።

በመጨረሻ ችግሩ ምን እንደ ነበር ተረዳን። ከጥቂት ዓመታት በፊት ከእኛ ሚሲዮናውያን መካከል አንዱ ዋናውን ቤቱን ከመሥራቱ በፊት ልክ እንደ እኛ ዐይነት ድንኳን ውስጥ ይኖር ነበር። ስለዚህ እነርሱ የኛን ድንኳን ሲመለከቱ የተረዱት ነገር እንደሱው እንደምናደርግ ነበር። ዛሬ ድንኳናችንን ብቻ ዘረጋን። ነገር ግን ይዜ ገና የመጀመሪያው ነበር። በመቀጠል ደግሞ በመሬታቸው ላይ ቤት መገንባት እንጀመራለን። ይህ እንዲሆን ደግሞ በፍጹም አይፈልጉም ነበር።

አሁን የተሳሳቱበትን ቦታ ስለ ተረዳን ሁለንም ነገር እስከሚፈልጉት ድረስ ማስረዳት እንደምንችል ርግጠኞች ነበርን። በትዕግሥት ስለ ድንኳኑ ፕሮግራም ያለንን ዕቅድና በቀያ የሠራነውን ነገርናቸው። ከዚያም በኋላ ብዙዎች ያዩትንና በፀሓይ ሲና ስለሚገኘው መኖሪያ ቤታችን ነገርናቸው። አንድ መኖሪያ ቤት ለእኛ በቂ እንደ ሆነና በመሬታቸው ላይ ሌላ ቤት እንደማንሠራ አረጋገጥንላቸው።

ነገር ግን ከቃላት ይልቅ ተግባር አብልጦ ይናገራል። በተቀመጠበት ቦታ ላይ ሆነው ሌላውን የሚሲዮናውያን መኖሪያ ቤት መመልከት ይችላሉ። በጣም አስፈላጊ ነበር። ቃላችንን እንደምንጠብቅ እንዴት ያውቃሉ? ድንኳኑን ጥለን አንድ እርምጃ እንኳ ከመሄድ መከላከል ይሻል ነበር።

ይህን ጊዜ ከመሀከላቸው አንዱ ብድግ አለና ርምጃ መውሰድ ያለበት አሁን እንደ ሆነ ወሰነ። ሮጦ የሸራውን ጣራ አፈፍ አደረገው። ሌሎቹም ያናደዳቸውን ነገር ለማስወገድ በፍጥነት ተከተሉት። ያረጀውንና ፀሐይ የበላውን ድንኳን በእጃቸው አጥብቀው በመያዝ በየአቅጣጫው ሲጉትቱት መቀደድ ጀመረ። በዚህን ጊዜ ለአስተጣጠፋችን ሳንጨነቅ ዕቃችንን በጥድፊያ ሰበሰብንና ተሳቢው ላይ ወረወርነው። ከተናደዱት ሰዎች ፊት መሄድ ስንጀምር ፀሐይ በኰረብታዎች መካከል መጥለቅ ጀምራ ነበር። በግልጽ ከሚታየው

ሁኔታቸው እንደ ተረዳነው አላስፈላጊ ነገርን ከአካባቢያቸው በማስወገድ የተሳካላቸው ሆኖ ይሰማቸው ነበር።

በዚያን ዕለት ማታ በቀላሉ ልንተኛ አልቻልንም ነበር። ምን ዐይነት ስሕተት እንደ ተፈጸመ ማስላሰል ቀጠልን። በማግስቱ ጠዋት ላይ ያልለከሩና የተጻጻቱ ጥቂት ቁሶች ቀሰቀሱን። እንደገና እንድናስብበትና ወደ ውኽይ እንመለስ ዘንድ ለመኑን። ነገር ግን ባለፈው ቀን የተፈጸመው ነገር ከአእምሮአችን አልጠፋም ነበር። በጕዳዩ ላይ ልንጸልይበት እንደሚገባ ነገርናቸው።

በውኽይ የቀሩት ሰዎች የኛን መመለስ በርግጥ የሚፈልጉት በመሆናቸው ሄደው ማረጋገጥ እንዳለባቸው ሐሳብ አቀረብን። መመለሳችንን የሚፈልጉ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ ተመልሰው ሊያነጋግሩን እንደሚችሉ ገለጽንላቸው። ወደ ውኽይ የመመለሱን ጕዳይ መልሰን ማሰብ ከመጀመራችን በፊት ድንኳን እንድንተክል ይረዱን ዘንድ ሁሉም አንድ ቦታ ላይ መሰብሰብ እንዳለባቸው አጥብቀን ነገርናቸው። ሰዎቹ በዚህ ሐሳብ ሳይስማሙ (ሳይደሰቱ) ወደ መጡበት ተመለሱ።

በሚቀጥለው ሳምንት በሙሉ ስለ መመለሳችን ጌታ በልባችን ሰላምን አላፈሰሰም ነበር። ከዚህም የተነሣ ነገሮች ተዘጋጅተው እየጠበቁን እንደሆነ የሚነግረን ሰው ሳይመጣ ሲቀር፣ ብዙም አልተገረምንም። እግዚአብሔር ከውኽይ ላይ ለጊዜውም ቢሆን ፊቱን እንዳነሣ (በሩን እንደዘጋ) በግልጽ ማየት ይቻል ነበር።

በጥር 1966 ከገና በዓል በኋላ የእኛ ተልእኮ ለአራት ቀን ጸሎት መመለስ ነበረበት። ሁሉም ሚሲዮናውያን ሥራቸውን ትተው በሌላ የሚሲዮን ቡድን በሚመራ የማረፊያ ካምፕ ላይ ተሰበሰብን። መጽሐፍ ቅዱስ እያጠናን ልባችንን ለመመርመር ጊዜ ወሰድን። መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዳችን ውስጥ ይሠራ ነበር።

ያላስተዋልናቸው ኀጢአቶችና ለጌታ ሙሉ በሙሉ ያላስ ረከብናቸው የሕይወታችን ክፍሎች እንዳሉ ተረዳን። እግዚአብሔር በማያጠያይቅ ሁኔታ በመከከላችን እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አስተዋልን። ኀብረቱ በጣም ጥሩ ነበር። ባሳሰፍናቸው ቀናት እርስ በእርሳችን እንድንያያዝ፣ ወደ ጌታም የበለጠ እንድንቀርብ ረዳን።

ስለ ቁስ ግርማና በመንዝ ስለሚገኙ ጓደኞቻችን ስንጸልይ ምልክት እናይ ዘንድ መጸለያችን ብቻ በቂ እንዳልነበር ተረዳን። እግዚአብሔር አምነታችንን አሳድጎ በመንዝ አርባ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን በተገቢው መንገድ እያወቁ እንዳሉ እንድናምን አደረገን። በሐሳብ ብቻ ከመጠን በላይ ተደሰትን። በርግጥ ይህ እንደሚሆን በልባችን ከእግዚአብሔር የሆነ ጽኑ እምነት ነበረን። ለጸሎት ከሄድንበት ወደ መንዝ የተመለስነው እግዚአብሔር እንዴት ሐሳባችንን እውን እንደሚያደርገው ለማየት እየጓጓን ነበር።

የቤርያ ሰዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች ይልቅ አስተዋዮች ነበሩ፤ ምክንያቱም ነገሩ እንደዚህ ይሆንን? እያሉ መጻሕፍትን በየለቱ በመመርመር ቃሉን በታላቅ ጕጕት ተቀብለዋል።

የሐዋርያት ሥራ 17÷11

ታላቅ ጕጕት

ለጸሎት ከሄድንበት የተመለስነው ልክ የዓመቱ ታላቅ ሃይማኖታዊ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ነበር። ሰዎች የክት ልብሳቸውን ለብሰው ሲወጡ ከፊታቸው ላይ የጕጕት ስሜት ይነበብባቸው ነበር።

የኢየሱስን ጥምቀት ለማስታወስ የሚከበረው የጥምቀት በዓል የሚውለው በጥር ወር መጀመሪያ ላይ ነው። በዚህ ቀን የመንዝ ሕዝብ በሙሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጕርፋል። እኛም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድን። ሥነ ሥርዐቱ በጠዋት ይጀመራል። በመጀመሪያ ጥቂት ቁሶችና ዲያቆናት ይጀምሩታል ነገር ግን ሌሎች ሰዎች ሁሉ ሲመጡና የበዓሉ አከባበር ሥርዐት ሲፈጸም ሲታይ ተመልካቹን አፍዝዞ ያስቀራል። እየተደጋገመ የሚመታው ከበሮ ከጸናጽሉ ጋር ተዳምሮ ለማሕሌቱ ጥሩ ድምቀትን የሚሰጥ ነበር።

የሕዝቡ ድምፅ እየጨመረ ሲመጣ እያንዳንዱ ማሕሌት ለጆሮ ትንሽ እየፈጠነና የበለጠ እየተሰማ ይሄዳል። በመጨረሻም ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ለአንድ ሰው መቆሚያ የሚሆን ቦታ እንኳ ይጠፋል። በዚህ ጊዜ ሴቶች በሐሤት መሞላታቸውን ለማሳየት በእልልታ እየተ ቀባበሉ ያደምቁታል። በአጠቃላይ ሥርዐቱ በጣም ማራኪና አስደሳች ነበር።

በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚዘጋጁት መጕናጸፊያዎችና (ካባዎችና) አክሊላት የሚለበሱት በእንደዚህ ዐይነት ታላላቅ ክብረ በዓላት ላይ ነው። በወርቅ ቅብ የተቆንጠቆጠው ልብስ በሚያብረቀርቁ ጥልፎችና ጌጣ ጌጦች የተሸፈነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ወይም መስቀል በያዘ በእያንዳንዱ ቄስ ላይ ልክ እንደ ለበሰው መጕናጸፊያ በጌጥ የተንቈጠቈጠ ጐጕጥላ ይያዝለታል። ጐጕጥላዎቹ የታላላቅ ክብርና አምልኮት መግለጫዎች ናቸው። በተጨማሪም ቄሶቹ ትላልቅ የነሐስ መስቀሎችንና የዕጣን ማጨሻ ጽና ይይዛሉ።

በጣም አስፈላጊ በሆኑ በዓላት ላይ ታቦቱን ከሚያርፍበት ቅድስተ ቅዱሳን (መቅደስ) ያወጡታል። ዕድሜው ትንሽ ገፋ ባለ ቄስ ጭንቅላት ላይ በጥንቃቄ ያስቀምቱትና የወርቅ ቅብ ልብስ አልብሰው

ጐንጥላ ከላይ ይያዝለታል። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ከአንድ በላይ ታቦት ቢኖራቸውም፣ እያንዳንዱ ታቦት የሚወጣው በተመሳሳይ ሁኔታ ነው።

ታቦቱን የሚሸከሙት ቄሶች ከሰልፉ በመጀመሪያው መሥመር ላይ ሲሄዱ፣ የተቀሩት ቄሶችና ዲያቆናት በፍጥነት በኋላ ይከተላሉ። ከእነርሱ ቀጥሎ ደግሞ እንደ ጠባቂ በትከሻቸው ላይ ጠመንጃ ያነገቱ ያገሩ ወንዶች ይታያሉ። በዚህ ዐይነቱ ሰልፍ የበዓሉ ተሳታፊ ወጣት ሴት መዘምራት ከኋላ እየተከተሉ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ለክብረ በዐሉ የተዘጋጁ መዝሙሮችን ይዘምራሉ።

ታቦቱን የሚሸከሙት ቄሶች በክብር ቀስ እያሉ ከፊት ሆነው ስለሚሄዱ፣ ታቦቱን አጅቦ የመሄድ ሥርዐቱ በጣም ዘገምተኛ ነው። አጋጣሚም ከሆነ ውሃ ባለበት ቦታ ማለት ትንሽ ወንዝ ወይም ምንጭ በሚታይበት ከፍ ያለ ድንጋይ ላይም ለመሄድ ይገደዳሉ። አንዳንድ ጊዜ በተመረጠው ቦታ ላይ ለመድረስ ብዙ ሰዓት ይወስዳል ይሁን እንጂ ይህ ከሚጓጕለት ነገር የሚገኘውን ደስታቸውን አይቀንሰም። ከሕዝቡ የተጨናነቀ እንቅስቃሴ ትንሽ ወጣ ተብሎ ሲቆም፣ ያልተለመደ ነገር ግን የማያስጠላና ቅንብር የጐደለው ድምፅ ይሰማል።

ታቦቱ በጥንቃቄ የሚቀመጥበት ትንሽ ድንኳን ተተክሎ ይጠብቃል። የቀረው ልዩ ልዩ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ ታቦቱ አስቀድሞ በሄደበት አኳኋን ከሕዝቡ ፊት ለፊት ሆኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመለሳል። እንደገና ታቦቱ ወደ ማረፊያው ሲመለስ፣ ሕዝቡ ቢደክምም እንኳ ወደየቤቱ የሚመለሰው በደስታ ስሜት ነው።

በዓሉን ከሚያከብረው ሕዝብ ጋር ስንቀላቀል ቄስ ግርማን የአጎራባቿ ቤተ ክርስቲያን ዋና ቄስ ከነበረው ጓደኛው ጋር አገኘነው። ቄስ ድጋፌ በቀያ ስለ ነበረን መርሐ ግብር ሰምቶ ወዳሰበት ወደ አሎ ሄደን እንድናስተምር ከፍተኛ ጕጕት ነበረው። አሎ ከቀያ በስተደቡብ ያለ ሲሆን፣ ወደዚያ ሄዶ ማስተማር ጥሩ ዕድል እንደ ሆነ ተሰማን። የሥራ መርሐ ግብራችንን ለሕዝቡ እንድናስተዋውቅም በቅርብ ቀን በሚከበረው በአንድ ቅዱስ መታሰቢያ በዓል ላይ አንድንገኝ ጋበዘን።

አሎ ቤተ ክርስቲያን በደረስንበት ሰዓት ላይ ቅዳሴ አልቆ ሰዎች ለመቀመጥና ዐብረው ለመብላት ዝግጁ ነበሩ። የአካባቢው የቤተ ክርስቲያንና የማኅበረ ሰቡ መሪዎች በጥሩ ሁኔታ ተቀበሉን። ለሁለት ሰዓት ያህል ዐብረን ስንመገብና ከእነርሱ ጋር ስናወራ ቈየን። ሁሉም በአንድ ድምፅ ሄደን እንድናስተምር ጥያቄ አቀረቡልን።

ከተመገብን በኋላ ለድንኳን መትከያ ስለሚሆነው ቦታ ተነጋገርን። ብዙዎቹ ሁሉንም ነገር ከሌባ መጠበቅ እንዲችሉ በግቢ ውስጥ እንድንሆን ለመኑን ነገር ግን ያንን ለማድረግ ብዙም ጕጕት አልነበርንም። እያንዳንዱ ግቢ ቢያንስ ቢያንስ አንድ ሌባ ለመጠበቅ የሠለጠነ ውሻ አለው። አንድ ቀን ሁሉም ነገር ደኅና ነው ብዬ ወደ ግቢው ስገባ፣ የሚጮኽ ውሻ ቁርጭምጭሚቴን ነክሶኝ ነበር። ነገር

ግን እንዳጋጣሚ ረጅም ሱሪና ወፍራም ካልሲ አድርጌ ስለ ነበር፣ የውሻው ጥርስ ወደ ቈዳዬ ዘልቆ ባለመግባቱ አልተጐዳሁም። ሆኖም ያ አጋጣሚ ስለ ውሻ ሳስብ እንድጨነቅ አድርጎኛል።

በተጨማሪም በሚሲዮናዊው ጣቢያችን ውስጥ ትልቁ ሥራዬ በውሻ የተነከሱ ሰዎችን ቍስል መስፋት ነበር። ከዚህ የተነሣ ባለቤቱ ራሱ ውሻውን በዱላ አስፈራርቶ አንድን እንግዳ ይዞ ካልገባ በቀር፣ ሰዎች ወደ ሌላ ሰው ግቢ ለመግባት ያመነታሉ።

እኛ ግን ሰዎች በነጻነት እንዲገቡና እንዲወጡ ፈለግን። በቀያ የኖርነው መስክ ላይ ነበርና አንዳንድ ዕቃዎችን በሥርዐቱ ካለማስቀመጣችን የተነሣ ከደረሰብን ጥቃቅን ስርቆት በስተቀር ምንም ችግር አላጋጠመንም ነበር። በመጨረሻም ጌታ እንደሚጠብቀን አሳምነናቸው ሁሉም በመስኩ መካከል ላይ ድንኳኑን እንድንተክል ተስማሙ።

ቦታው ላይ በደረስን ጊዜ በቀያ በጥሩ ሁኔታ የሠራነውን መርሐ ግብር መልሰን አዘጋጀን። እሑድ ዕለት ከሰዓት በኋላ በነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሰዎች ድንኳኑን ሞልተውት ስንመለከት በጣም ደስ አለን። ጥናቱን ልክ ልንጀምር ስንዘጋጅ ይመጣል ብለን ያልጠበቅነው ቡድን መጣ። ባለፈው ከነበርንበት ከቀያ የመጡ ቄሶችና ዲያቆናት ነበሩ። ወደዚያ ለመምጣት የሁለት ሰዓት የእግር ጕዞ ማድረግ እንደ ነበረባቸው ቢያምኑም፣ ይህ ምንም አላሳሰባቸውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ለመሳተፍ እስከቻሉ ድረስ ጕዞው ረጅም ቢሆንም፣ ወደ እኛ መምጣቱን ይፈልጉት ነበር።

የመንዝ አየር ሌሊት ሌሊት በጣም ቀዝቃዛ ነው። አስር ሺ ጫማ ላይ አየሩ ስስ ነው፤ ነፋኑም ያለማቋረጥ ይነፍሳል። ፀሐይ ካልወጣች ብቸኛው ተስማሚ ቦታ ዐልጋ ነው። ከትልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን በኋላ ባለው ጠዋት ስንነቃ በጣም ቀዝቃዛ ነው። ከሞቃቱ ዐልጋችን ወጥተን ቀዝቃዛ ልብሳችንን ለመልበስ የማናፈገፍግ ጥንካሬ እያሰባሰብን ሳለ የመጀመሪያዎቹ የጠዋት የፀሓይ ጨረሮች ወደ ድንኳናችን በዝግታ ተጠጉ።

ወዲያውኑ ከውጪ በኩል ያልተለመዱ ድምፆችን ሰማን። ጕሮሮአቸውን የሚስሉ ሰዎች ይመስላሉ። የሚንኳኩ በሮች ከሌሉ፣ የአንድን ሰው መኖር ለማረጋገጥ የሚደረገው እንደዚህ ነውና እነ ማን እንደ ሆኑና ምን እንደ ፈለጉ ጠየቅናቸው። በእንደዚህ ዐይነት ሰዓት ላይ መጥተው ጥያቄ በማቅረባቸው ይቅርታ ጠየቁን።

ጥያቄያቸው እንደዚህ የሚል ነበር፤ «ለዛሬ ያቀዳችሁት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዳለ እናውቃለን፤ እንደገናም ትላንት ሥራ በዝቶባችሁ እንደ ደከማችሁም ተረድተናል። አሁንስ መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር ትንሽ ጊዜ ይኖራችኋልን?»

ጆሮአችንን ማመን አልቻልንም። ነገር ግን ጥያቄያቸውን እንዲደግሙት አልጠየቅናቸውም ነበር። በፍጥነት ለብሰን ከቀያ የመጡትን ቂሶችና ዲያቆናት ወደ ድንኳኑ እንዲገቡ ጋበዝናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን በጸሎት ጀመርን። እያስተማርን ሳለ ለራሳችን ጥቅም ስንል በተከታታይ የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ከእንግሊዘኛው ትርጉም ጋር እናነጻጽር ነበር። በመጨረሻ ላይ ሰዓታችን ስንመለከት ሳይታወቅ ሁለት ሰዓት ማለፉ በጣም አስገረመን።

የጥናት ተሳታፊዎች የሚሠሩት ነገር ይኖራቸዋል በማለት ልናሰናብታቸው ዐሰብን። መጨረሻችንን ለማሳየት መጽሐፍ ቅዱሳችንን ዘግተን ወደ ኋላ ተደግፈን ተቀመጥን ። ምን ለማለት እንደ ፈለግን ሲረዱ፣ ፊታቸው ላይ ዐዘን ይታይባቸው ነበር። ከመካከላቸው አንዱ ደፍሮ «በቃ ደከማችሁ ማለት ነው?» በማለት ጠየቀን።

በድጋሚ ጆሮአችን የሚጫወትብን መሰለን። ተጨማሪ የጥናት ጊዜ ይፈልጉ ነበር። መጽሐፍ ቅዱሳችንን በድጋሚ ከፍተን ጥናቱ ለተጨማሪ ሁለት ሰዓት ቀጠለ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ይህ ይበቃቸዋል ብለን ዐሰብን። እኛ እያስተማርን ሳለ ሞልቶት በትልቁ ድንኳን ውስጥ ቋንቋ ያስተምር ነበር። ለትምህርቱ የመጡት ትንሽ ሰዎች ስለ ነበሩ በቀላሉ ይከታተላቸው ነበር።

እንደገና ጥናቱን ማቆምና ለተሳታፊዎች የመሄድ ዕድል መስጠት እንዳለብን ተሰማን። ለረጅም ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን እንደዚህ ለማጥናት የሚፈልግ ሰው አጋጥሞን ስለማያውቅ ጥርጣሬ ዐደረብን። ጥናቱን አቁሞ የመውጣት ምርጫ የሌላቸው ተሳታፊዎች አድርገን ቈጠርናቸው። ምን አልባት ከባህላቸው ያልተረዳነው ነገር ለኛር ይችላል ብለን ዐሰብን። እኛን አክብረው ላለመሄድ የፈለጉ መስሎም ታየን።

ከአራት ሰዓት በኋላ ጥናቱን አቆምንና ወደ ቤታቸው ለመመለስ እንደሚችሉ ነገርናቸው። ስሜታችንን ለመረዳት ሲጥሩ ሳለ ከመካከላቸው አንዱ «የምታውቁት ይህን ብቻ ነው?» ብሎ ጠየቀን። ጥናቱን ለማቆማችን ብቸኛ ምክንያት ይህ ብቻ ነበር።

በመጨረሻ ለመማር እንደሚፈልጉ በማመናችን ለሦስተኛ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ገለጥን። የፀሐይ ጨረር በአናት ላይ ሲሆን እንደማኖርባቸው ተረዳን። ምሳቸውን ይበሉ ዘንድ ጥናቱን እንድናቆም ሐሳብ አቀረብን። ጠዋት በችኮላ ከመምጣታቸው በፊት እንደ በሉና ማታ ወደ ቤታቸው ተመልሰው እራት እስኪበሉ ድረስ ምንም

እንደማይፈልጉ አስረዱን። ይህን ልምድ ረጅም ጉዞ ሲሄዱና ከቤታቸው ርቀው ዕርሻ ሲያርሱ ስለሚጠቀሙበት ለእነርሱ አንግዳ አልነበረም።

ከዚያ ሁሉ በኋላ ተሳታፊዎች ሙሉ ቀን መማር ፈልገው እንደነበር ከስሜታቸው ተረዳን። ስለ ዕርሻ ሥራቸው ስንጠይቃቸው፣ ዝናብ እስኪመጣ መሥራት ያለባቸውን ሠርተው እንደጨረሱ ነገሩን። ዘንቦ መሬቱ እስኪረጥብ ድረስ ማረስም መዝራትም አይችሉም። ዝናብ መዝነብ እስኪጀምር ድረስ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እያጠኑ መቈየት ይችሉ እንደሆነ ለማወቅ ፈለጉ።

ይህ በህልማችን ብቻ ተስፋ ማየት የቻልንበት ጉዳይ ነበር። በዚህ ጊዜ በርግጥ እውን እየሆነ ነው። ብዙ ልናስተምራቸው የምንፈልጋቸው ነገሮች ነበሩና ሁሉም አስፈላጊ ሆኖ ታየን። በዚያ ቀን ሰዓቱ ቶሎ ዐለቀ። ሳናውቀው ፀሐይ ጠልቃ ነበር። በየቀኑ የምናካሂደው የቋንቋና የእጅ ሥራ ትምህርት በእሱ ብዙ ባይሳካም ጌታ ግን በጥንቃቄ የራሱን ዕቅድ እያሳካ ነበር።

በኢቆንዮንም ጳውሎስና በርናባስ አብረው ወደ አይሁድ ምኩራብ ገቡ፤ በዚያም በሚገባ ስላስተማሩ፣ ከአይሁድም ከግሪክም እጅግ ብዙ ሰዎች አመኑ። ያላመኑት አይሁድ ግን፣ ከአሕዛብን አነሣሥተው ወንድሞችን እንዲጠሉ አደረጓቸው። ጳውሎስና በርናባስም ስለ ጌታ በድፍረት እየተናገሩ ብዙ ጊዜ አዚያው ቈዩ፤ ጌታም የሚናገሩትን የጸጋውን ቃል በታምራዊ ምልክትና በድንቅ ሥራ እየደገፈ ያረጋግጥላቸው ነበር። የከተማውም ሕዝብ ተከፋፈለ፤ ገሚሱ ከአይሁድ ጋር ገሚሱም ከሐዋርያት ጋር ሆነ።

የሐዋርያት ሥራ 14÷1-4

የጸሎት ኀይል

በአሎ ሳለን በቁስ ድጋፌ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከእርሱ ጋር እናስቀድስ ነበር። የአምልኮ ሥርዐታቸውን በምንም መንገድ ተቃውመን ልናስከፋቸው አልፈለግንም። ባህላቸውን በጥንቃቄ ለማጥናት ጥረት እናደርግ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት ጥቂቶቹ የትኛው መቼ መደረግ እንዳለበት በማሳየት ይረዱንና የወዳጅነት ስሜት ይገልጹልን ነበር። ይሁን እንጂ ተጠራጣሪ የነበሩ ሌሎች ሰዎችም ነበሩ። ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን ለሁለተኛ ጊዜ ከሄድን በኋላ ያልተለመደ ነገር ተፈጸመ። ታቦቱ ተሰረቀ። በፍጥነት ፈረንጆቹ ታቦቱን ሰርቀው ሸጡት የሚል ወሬ ተናፈሰ። ወሬ አንቀበልም ማለት እርባና ቢስ እንደሚሆን ስለተረዳን ዝም አልን። ነገር ግን ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አቆምን።

ከአሎ ከሄድን ከብዙ ሳምንታት በኋላ ታቦቱ ተመለሰ። የእኛን በዚያ መኖር ያልወደደ አንድ የቤተ ክርስቲያኑ ዲያቆን ታቦቱን ለመጠበቅ በራሱ ዋሻ ውስጥ አስቀምጦት ነበር። ቢሆንም ግን የዲያቆኑ ታቦቱን መልሶ ማምጣት ስማችንን የማጥፋት ዘመቻውን ሊያስቆመው አልቻለም። የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ታቦቱን በመጠበቁ በጣም አመሰገኑት። እርሱ ባይሸሸገው ኖሮ ያለ ምንም ጥርጥር ልንሰርቀው እንችል እንደነበር ተናገሩ።

ከዓመት ፈቃድ ተመልሰን ቋንቋ መማር ስንጀምር፣ እግዚአብሔር በሆነ መንገድ በመንዝ ላሉት ሰዎች የጸሎትን ኀይል እንዲያሳይ ጽኑ ፍላጎት ነበረን። ስለ እያንዳንዳችን የሚጨነቅና ጸሎትን የሚመልስ ሕያው አምላክ እንዳለ ሰዎቹ እንዲያውቁ ፈለግን።

በአማርኛ ለመጸለይ የምናደርገው ልምምድ ከየቀኑ ትምህርታችን ትልቁን ስፍራ ይይዝ ነበር። ከሠራናቸው ነገሮች በሙሉ በጣም ከባድ ሆኖ ነው ያገኘነው። ከጓደኞች ጋር ሲነጋገሩ ስሕተት መሥራት ምንም ማለት አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ሆኖ አፍ ቢተሳሰር ጥሩ አይሆንም። ሐሳባችንን ዐዲስና አስቸጋሪ በሆኑ ቃላት ለመግለጥ ስንሞክር በጣም ጥንቃቄ እናደርግ ነበር።

በመጨረሻም ከወራት ልምምድ በኋላ ቋንቋውን እየለመድነው መጣንና ግባችንን መታን። በተለማመድነው አማርኛ ቋንቋ ከእግዚአብሔርና ከኢትዮጵያውን ጓደኞቻችን ጋር ለመነጋገር ቻልን።

በዚህ ጊዜ ወደ መንዝ ከተመለስን ስምንት ወር ሆኖል። ከመቼውም ጊዜ በላይ እግዚአብሔር ያ ጸሎት እውነት እንደ ሆነ ለኢትዮጵያውያን ጓደኞቻችን እንዲያሳያቸው ፈለግን። እነርሱን ለማሳመንና ትኩረታቸውን ለመሳብ ዐዲስና ያልተለመደ ነገር መሆን እንዳለበት ዐሰብን።

በአጠገባችን የነበሩት ብዙዎች ሰዎች ባልተለመዱ ቦታዎች ላይ አዘውትረን እንደምንጸልይ ብዙም ሳይቈዩ ተረዱ። ምግብ በተ መገብን ቊጥር እነርሱ ቤት ውስጥም ሆነ እኛ ቤት ውስጥ ብንሆን ሁልጊዜ እንጸልያለን። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የእጅ ሥራ ትምህርትና ጤና ጣቢያው የሚከፈተው በጸሎት ነው። ሁልጊዜ ችግር ሲያጋጥመን ወይም ውሳኔ መስጠት ሲያስፈልገን፣ በመጀመሪያ ጌታን እናማክረዋለን።

ይህ ያልተለመደ የአማርኛ ጸሎት ሙሉ በሙሉ ለእነርሱ ዐዲስ ነበር። የሚያውቁትና የተለማመዱት የጸሎት ዐይነት የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ነበር። ጸሎቶቹን ማቅረብ የቄሶች የተለየ ኀላፊነት ሲሆን፣ ሁሉም የሚጸልዩት በግእዝ ቋንቋ ነበር። በጥንቃቄና በዝርዝር የሚታወሱ ስለ ሆኑ ያለ ምንም ችግር በቃል ይነበነባሉ።

ዐዳዲስ ሐሳብን እየፈጠሩ መጸለይ ለእነርሱ አዳጋች ነበር። አስበውት አያውቁም ነበር ነገር ግን አሁን እኛ ስናደርገው ሰሙን። ከምንም በላይ ለእነርሱ ልናሳያቸው የፈለግነው ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የመነጋገሪያ መንገድ እንደ ሆነና ጸሎትንም እግዚአብሔር እንደሚመልስ ነው።

በሳምንት አንድ ቀን እኔና ሬይ ለጎሙሱ የሽራብ ክርና የብርድ ልብስ ገበያ በጤና ጣቢያ ቀን ከድንኳኑ ኑሮ ወደ ቤት እንመለሳለን። በተጨማሪም ለውነታችንንም እንታጠባለን እንደገናም ለድንኳኑ ኑሮአችን የሚያስፈልገንን ምግብም እንገዛለን። እዚያ በምንቈይበት ጊዜ መንዝ ከሚኖሩ ከሌሎች ሚስዮናውያን ጋር ለመገናኘትና በሳምንቱ ወስጥ ጌታ ስለ ሠራው ሥራ ለመነጋገርና ለመጸለይ ዕድሉን እናገኛለን።

አድካሚና ሰዓት ገዳይ ስለ ነበር፤ ረቡዕ ረቡዕ ወደ ቤታችን ስንመለስ ትንሹን ድንኳናችንንና ሌሎች ዕቃዎቻችንን አናመጣም ነበር። ጥቂት ሰዎች ዕቃችንን በሌለንበት ጥለን መሄዳችን ዐሳስቧቸው ነበር። ይህ ጕዳይ በተነሣ ቊጥር እግዚአብሔር የሰጠንን ነገር ሁሉ እንደሚጠብቅልን ያለንን ጽኑ እምነት እንገልጽ ነበር። ለጥንቃቄ ሲባል ግን በአካባቢው ባለርስት ተመርጦ የተመደበ ጠባቂ ነበረን።

በየሳምንቱ በጥንቃቄ ዕቃችንን እናስቀምጥና ድንኳኑን አጣጥፈን በዚፕ ከዘጋን በኋላ ሽፋኑን እናስረዋለን። ድንኳኑን መቄለፍ

ግን አይቻልም። ጎሙስ ከሰዓት በኋላ ተመልሰን እንደነበረ ስናገኘው በመረጋጋት እንተነፍስና የምስጋና ጸሎት እንጸልያለን።

ከዕለታት አንድ ቀን ብዙም ዕድለኞች አልነበርንም። በቤት ውስጥ ከነበረን አድካሚ ሥራ ስንመለስ፣ የተለመደው ስብሰብ ከድንኳኑ አጠገብ ይጠብቀን ነበር። ሁልጊዜ ጸጥ ወዳለው የመስክ ላይ ሰፈራችን መመለስ ጥሩ ነበር። ወደ ድንኳኑ እየተቃረብን ስንመጣ በመጀመሪያ ትኩረታችንን የሳበው ነገር የተበጠሰው ዚፕ ነበር። ከውስጥ ሰዎች በተጣደፈ ሁኔታ ሲመለከቱን መጥፎ ነገር እንደ ተፈጸመ አረጋገጠልን። አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር ወደ ውስጥ ገብቶ ነበር።

ሁሉም ነገር ትርምስምስ ያለ ነበር። በፍጥነት ገባንና አየር እንዲገባ መስኮቶቹን ከፈትናቸው። ውጭ የነበሩት ምን እንደ ተፈጸመ ለማየት በክፍተቶቹ በኩል መጡ። የተዝረከረከው ነገር የማይታመን ነበር። ምግባችን፣ መጽሐፎቻችን፣ ልብሶቻችንና የማስተማሪያ ዕቃዎቻችን በየቦታው ተበታትነው ነበር። ከትራሳችን ውስጥ ያለው ጨርቃ ጨርቅ ላይቀር ወጥቶ ከተበታተነው ልዩ ልዩ ዕቃ ጋር ተደባልቋል።

የመጀመሪያው ግምታችን የሚያስደነግጥ ቀልድ ሊሆን ይችላል የሚል ነበረ። ምናልባት ደግሞ አንድ ሰው ድንኳኑን ሲከፍት ውሾች ገብተው ዕቃዎችን ሰባብረው ይሆናል ብለንም ዐሰብን። የመንዝን ልማድ የሚያውቁ ሰዎች ግን በተለየ መንገድ ነበር የጠረጠሩት። ወዲያውኑ ለንዝናቸው ክፍተት እየሰጡ በዜማ ማልቀስ ጀመሩ። ከሰዎች መካከል አንዱ፣ «ይህ እንደሚሆን ገምተን ነበር። እንግዲህ ላትመለሱ ወደ ቤታችሁ ትሄዳላችሁ። ከዚህ በኋላ አታስተምሩንም ማለት ነው» አለ።

ሌላ ሰው ደግሞ ሁሉንም በሚወክል አስተያየት፣ «በሜዳው ላይ መሆን (መኖር) እንደሌለባችሁ ነግረናችሁ ነበር። እናንተ ግን አምላካችሁ እንደሚጠብቃችሁ ተናገራችሁ። ስለዚህ ዝም ብለን እንድንጠብቅና እንድናይ ወሰንን። አሁን ግን ያን ጊዜ መስማማት እንዳልነበረብን ተረዳን» አለ።

የተዘበራረቀውን እያስተካከልን ጥርጣሬአቸውን ልናስወግ ድላቸው ሞከርን። በኾክ የተጻፉ መልእክቶች በየቦታው እንደ ተምነ ጫጨሩ አስተዋልን። ምንም ዐይነት ፍንጭ አልሰጠንም፤ ነገር ግን ወደ ድንኳናችን የገባው ሰው መጻፍ የሚችል እንደ ሆነ ተረዳን። በመጨረሻም ሁሉንም በየቦታው መልሰን አስቀመጥን። በዚያን ጊዜ ብዙ ነገር እንደ ጠፋ ተገነዘብን። በጓደኞቻችን ጉትጉታ ዝርዝሩን መጻፍ ጀመርን።

ኮቶቻችንና የመኝታ ከረጢቶቻችን (sleeping bags) የሉም። አባቴ ገደል ላለባቸው አገር አቋራጭ ጉዞዎች እንድጠቀምበት የላከልኝ ቦት ጫማ ከእነዚህ ዕቃዎች ጋር ዐብሮ ነበር። በጣም ይታወቁ የነበሩት

ፕሮጀክተራችንና የመጽሐፍ ቅዱስ ፊልሞች ከካሜራችንና ከካሴት ማጫወቻችን ጋር ተወስደዋል። ሁሉም መጽሐፍ ቅዱሶችና የጥናት መርጃዎች የትም ሊገኙ አልቻሉም። አብዛኛው ምግባችን ደግሞ ጠፍቷል ወይም ተበልሽቷል። ባትሪዎች፣ ከብር የተሠሩ የገበታ ዕቃዎች፣ መጥበሻዎች፣ ማሰሮዎች፣ ሳሕኖች፣ የቋንቋ መማሪያዎችና የሹራብ ሥራዬ ጠፍተዋል። የጠፋ ዕቃዎች ዝርዝር ከ500 ዶላር በላይ እንደ ከሰርን አሳየ።

ሰዎቹ ግን ለእኛ ምክር ለመለገስ ፈጣን ነበሩ። መሀል ሜዳ ሄደን ጉዳዩን በፍርድ ቤት ማስያዝ እንዳለብን ነገሩን። ይህን ማድረጉ የተለመደ ሥነ ሥርዐት ነበር። ነገሩ በአሰልቺ ሁኔታ የሚጓተት በመሆኑና ጥሩ ነገር አገኛለሁ ተብሎ የሚታሰብ ትንሽ ተስፋ ብዙውን ጊዜ ስለሚገድል እንደ አላስፈላጊ ነገር ይቁጠራል። ወደ ሕግ ቦታ መሄድ አለበት። የሚደረገው እንደዚህ ነው።

መጸለይ እንዳለብን ወሰንን። ጌታ ወደ አሎ እንደ አመጣን ስለ ተሰማን ወደ ፍርድ ቤት ሄዶ ጊዜ ማባከን ጥሩ እንዳልሆነ ሁሉታችንም ውሳኔ ላይ ደረስን። ጉዳዩ በእግዚአብሔር እጅ እንደ ሆነና ማስተማራችንን እንደምንቀጥል ለሰዎቹ ነገርናቸው።

ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ሰዎች ከየቦታው ሊያጽናኑን መጡ። ከሁሉም መሐከል ግን እግዚአብሔር ልዩ በረከቱንና ሰላሙን ሰጠን። ምንም እንኳ አብዛኛው የጠፋው ዕቃ በኢትዮጵያ የሚገኝ ባይሆንም፣ ተገቢ ጥንቃቄ አላደረግንም ነበር። ሰዎች ከእኛ ጋር ሊያለቅሱ ሲመጡ እናጽናናቸው ነበር። ጎላፊው እግዚአብሔር እንደ ሆነም እናረጋግጥላቸው ነበር። ይወደናልና ይጠብቀናል።

ከዚህ በፊት የማናውቃቸው ሰዎች እኛን ለማየት ይመጡ ነበር። ከእያንዳንዳቸው ጋር የኢየሱስን ፍቅር እንካፈል ነበር። እግዚአብሔር የዕቃችንን መጥፋት እንኳ ለራሱ እየተጠቀመበት እንደ ሆነ ማየት እንችል ነበር።

ቅዳሜ ቀን ሲደርስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችንን እንደገና መቀጠል የሚያስችሉን ሁኔታዎች ሁሉ ተመቻችተው ነበር። ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ የቀኑን ትምህርት እየጨረስን ሳለን አንድ ገበሬ ወደ እኛ እየሮጠ መጣ። ለእኛ የሚነግረን ዜና ነበረው። ዕቃችንን እንዳገኘው ስላሰበ ሄደን እንድናየው ፈለገ። ምንም እንኳ የመሸ ቢሆንም፣ ሁሉም ቄይተው እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ መረጡ። ምንም ነገር ቢመጣ የመሄድ ሐሳብ ያላቸው አይመስሉም ነበር።

ገበሬውን በመኪናችን ይዘነው ሄድን። ከአንድ ማይል በኋላ ወዳለው ወደ ትልቁ የመንደር ግጦሽ ስፍራ መራን። የምናውቃቸውን ዕቃዎች በቀላሉ ተመለከትን። ያለጥርጥር የኮቴ ጨርቅና መተኛችን ነበሩ። ሬይ እስሩን ለመፍታት ጊዜ ሳይፈጅ በላንድ ሮቨሩ ጀርባ ወረወረውና ወደ ሚጠብቁን ሰዎች አመራን።

ዝናብ መዝነብ ጀምሮ ነበርና ለብዙ ቀናት እርጥብ ነበር ነገር ግን ዕቃችን ምንም እርጥበት የለበትም። ደረቅ የሆነ ቦታ ተሸሽጎ እንደነበር ግልጽ ነው። ነገሩ እንዲህ ከነበረ ለምንድን ነው እኛ የመሰለነው? ይህ ጥያቄ አልተመለሰልንም ነበር።

ትልቁ ድንኳን ጋ ደርሰን እስሩን እየፈታን ስንበታተን ሁሉም ሰው በጉጉት ለማየት ተሰበሰበ። የጠፋውን ዕቃ ዝርዝር አምጥተን ዕቃውን ስናገኝ እየሰረገን መኖሩን እረጋገጥን። የጠፋው ዕቃ በሙሉ እስሩ ውስጥ ነበር። በእርግጥ አስቀድመን ያልጻፍናቸውንም ዕቃዎች አግኝተናል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ እነዚያ ዕቃዎች የጠፉ መሆናቸውን አላወቅንም ነበር።

ሰዎቹ በጣም ተገረሙ። ሁኔታው በፍጹም ሊረሱት የማይቻል ነበር። ከመካከላቸው አንዱ፣ «እግዚአብሔር ይህንን ለእናንተ ያደርግላችኋል። እናንተ ወደ እግዚአብሔር መጣቢያ አላችሁ እኛ ግን የለንም» አለ። ሌሎቹም በንግግሩ በመስማማት ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ።

እግዚአብሔር ጥያቄአችንን መለሰልን። የጸሎትን ኀይል ማንኛችንም በማንረሳው መልኩ አሳይቷቸዋል። ስለ ጸሎት ለረጅም ጊዜ ስንነግራቸው ነበር። ነገር ግን በእውነት እንደሚሠራ እነሱን ለማሳመን ይህንን ማየት ነበረባቸው። ያለንን ንብረት በሙሉ በእግዚአብሔር እጅ እናስቀምጥ ብለን ስናስብ ሰምተውን ነበር። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደ ሰማና እንደ መለሰልን በግልጽ የሚታይ ማስረጃ አየተመለከቱ ነው።

በዚያ ዕለት ምሽት ለመተኛት እንደ ተቸገሩ ዐስባለሁ። እኛ ምን ያህል እንደ ተቸገርን ዐውቃለሁና። እግዚአብሔር እኛን እንደሚጠብቀን መረጋገጡ ሌሎች ያላቸውን አመለካከት የሚለውጥ ነበር። ከዚያ ጊዜ አንሥቶ ሰዎቹ ለምንናገረው ሁሉ ልዩ ትኩረት መስጠት ጀመሩ።

ደግሞም እኛ ከእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ እንደ ተቀበልን ተሰማን። ሁሉ ነገር የሆነው ከጠየቅነውና ካሰብነው በላይ ነው። ከገደብ ባለፈ ደስታ ተሞላን። ከትንሽ ጊዜ ቈይታ በኋላ ጋደም ብለን ስናስብ፣ ቀኑን ሙሉ የተከናወኑት ነገሮች በሙሉ በጭንቅላታችን ሲመላለሱ ቈዩ። አንድ ጥሩ ነገርን አስተዋልን። ለእኛ የእግዚአብሔርን መልካምነት መቀበልና ዕቃችንን መልሰን ማግኘታችን በእምነት ትልቅ ርምጃ መራመድ ነበር። የእግዚአብሔር ጥበቃ እስከ የት እንደ ሆነ ስንረዳ በእምነታችን አደግን።

የሆነው ሁሉ በቂ ባለመሆኑ እግዚአብሔር አሁንም በሳምንቱ ማብቂያ ላይ ለእኛ ያስቀመጠልን ታላቅ ነገር ነበር። ቂስ ግርማ ወደ እኛ መጥቶ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ሳይሆን በአንደኛው ክፍለ ዘመን የሚመደቡ ነገሮችን በሙሉ ያንቀሳቀሰ አንድ ታላቅ ጥያቄ ጠየቀን።

ሲጠነቀሉ ከነበሩትም መካከል ብዙዎች መጽሐፋቸውን በማምጣት በሕዝብ ፊት አቃጠሉ፤ ዋጋቸውም ሲሰላ ዐምሳ ሺ ብር ያህል ሆኖ ተገኘ። በዚህ ሁኔታ የጌታ ቃል በኀይል እያደገና እያሸነፈ ሄደ።

የሐዋርያት ሥራ 19÷19-20

የጥንቈላ መጽሐፎች መቃጠላቸው

አንድ ቀን ከሰዓት ቂስ ግርማ እኛን ለብቻው የማናገር ዕድሉን ሲያገኝ ቀጥታ ወደ ጕዳዩ ገባ፤ «የሐዋርያት ሥራን እያነበብሁ ነበር፤ በምዕራፍ 19 ላይ ሰዎች በኢየሱስ ሲያምኑ ሁሉም የጥንቈላ መጽሐፎቻቸውን እንዳቃጠሉ ይናገራል። ያ አስፈላጊ ይመስላችኋል?» አለን።

ጥያቄውን ለመመለስ ቀላል ነበር። በተደጋጋሚ ሁለት ጌቶችን ማገልገል እንደማይቻል ተናግረናል። ከሕይወት ውስጥ ለሰይጣን የሚሆን ቦታ ካለ፣ መንፈስ ቅዱስ በዚያ ሰኖር አይችልም። ስለዚህ በሐዋርያት ሥራ ላይ የተፈጸመው አስፈላጊ እንደነበረ አረጋገጥንለት።

«ይህንን ነበር እኔም ያሰብሁት፤ በሚቀጥለው እሑድ ሁሉም ሰው ለማየት ሲመጣ እኔም የጥንቈላ መጽሐፎቼን አምጥቼ አቃጥላለሁ» በማለት ወዲያው ተናገረ።

በድንጋጤ ተውጠን ጸጥ አልን። ቂስ ግርማ ጠንቋይ እንደ ነበረ አመነ። ርግጠኛ እንደ ነበረ ለማረጋገጥ በድጋሚ ጠየቅነው። ነገሮችን ለመደበቅ ሳይሞክር በቀላሉ እንዲህ ሲል መለሰ፤ «አታውቁም ነበር እንዴ? የዚህ አካባቢ ሁሉ ዋና ጠንቋይ እኔ ነኝ። ጌታን እንደ ግል አዳኜ ስቀበል መጠንቈል አቆምሁ። ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ የጥንቈላ መጽሐፎቼ ቤቴ ውስጥ ናቸውና ይህን ወሳኔዬን ገና ለማንም ሰው አልተናገርሁም።» ግራ መጋባታችንን ሲረዳ የበለጠ ዐሳቡን ግልጽ አደረገልን። በብዙዎቹ ዘንድ እንደ ተለመደው ቂስ ግርማ የቤተ ክርስቲያንንም ምስጢር ለመማርና ዲያቆን ለመሆን ገና ልጅ ሳለ ነበር ከቤቱ ርቆ የሄደው። በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ባለ ጎጆ ውስጥ ከዕድሜ እኩዮቹ ጋር ይተኛ ነበር። በቂ ምግብ የሚያገኘው በተዝካር ድግስ ላይና የቤተ ክርስቲያን በዓሎች ሲከበሩ ብቻ ነበር። በሌላ ጊዜ ግን በልግስናና በልመና በሚያገኘው ምግብ ብቻ ኖሯል። የዲቁና ትምህርቱ ቤተ ሰቡን ለመርዳት ወይም ሌላ ነገር መሥራት በቂ ጊዜ አልሰጠውም ነበር። በሠለጠኑ አገሮች የሚታወቁት የትርፍ ሰዓት የክፍያ ሥራዎች በመንዝ አይታወቁም። በመጨረሻም ቂስ ግርማ ረጅም ጊዜ የወሰደበትን የዲቁና ትምህርቱን አጠናቀቀ። ከጋብቻና ከቤተ ሰብ ጋር ዐብሮ ሊያስሄደው የሚመኘው የቅስና እድገት መጣ። ቅስና በጣም የተከበረና ከሁሉም ሰው ከበሬታን የሚያስገኝ ማዕረግ ቢሆንም፤ አገልግሎቱ ረጅም ጊዜን ይጠይቃል።

በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ብዙ ቄሶች ለእያንዳንዱ ቤተ ሰብ ሥርዐተ ጥምቀትን፣ የቀብር ሥርዐትን ሊያስፈጽሙ ይገባል። እነዚህ አገልግሎቶች ደግሞ ረጅም ሰዓትን የሚፈጁ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም በቀናት የሚፈጸሙ ሆነው ይታያሉ። የሚከናወኑት ተራርቀው በሚገኙ በሰዎች መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ነው። አከባበራቸው የቄስን መር የሚጠይቅ ከቍጥር በላይ የሆኑ ሃይማኖታውያን በዓላትም አሉ። በዐጭሩ ቄስ መሆን ማለት የሙሉ ጊዜ ሠራተኛ መሆን ማለት ነው።

እንደ ዕድል ሆኖ የቄሱ ደሞዝ ከሥራው ጋር የሚመጣጠን አይደለም። ዋናው ቄስ እንኳ የሚያገኘው በብር ተተምኖ የሚሰጥ የግምት ክፍያ ያውም ከግማሽ ወር የማያልፍ ነው። ከሥራው ጫና በተጨማሪ ቄሱ ቤተ ሰቡን ለመመገብ ሲል ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ለመፈለግ ይገደዳል። ከዚያም በኋላ ያልታሰበ ነገር ይመጣል። እሑድ እግዚአብሔርን ከሚገለግለው ሰው ፊቱን ያዞርና በቀረው ሳምንት ደግሞ ሰይጣንን ያገለግላል። ጥሩ ክፍያ አለው። በመንዝ ብዙም ሳንቄይ በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ ዋነኛውን ስፍራ የሚይዙ ጠንቋዮች የሚባሉ ሰዎች እንዳሉ ማወቅ ቻልን። ጠንቋዮችን ርኅምና መጥፎ ሰዎች አድርገን ነው የምናያቸው። በዐይን ካየናቸው ጠንቋይ እንደ ሆኑ በርግጠኝነት ማወቅ እንችል ነበር። ነገር ግን ጠንቋይ የሆነ ሰው እስከዚያ ጊዜ ድረስ አይተን ስለማናውቅና ከእኛ ጋርም ብዙም የሚያገናኛቸው ስለሌለ ምንም ያህል በጉዳዩ ላይ እናስብበትም ነበር። መንገዳችን ከእነርሱ መንገድ ጋር ተገናኝቶ አያውቅም። እኛ እንዳሰብነው ደግሞ ሕይወታችንን የማይነካካ፣ የማይመለከተን ዐይነት ነበር።

ቄስ ግርማ ጠንቋይ እንደ ነበር ሲነግረን ለመጀመሪያ ጊዜ በመንዝ የአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ጥንቈላ በማይለያይ መልኩ የተያያዙ እንደ ሆኑ ተረዳን። ብዙዎች ጠንቋዮች ቄሶች ናቸው። በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን አትቃወማቸውም ወይም አታወግዛቸውም። ደብተራ የሚል መጠሪያ የተሰጣቸው ጠንቋዮችም አሉ። እነርሱ ደግሞ በመንዝ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን እርከን ከፍተኛውን ስፍራ የሚይዙ ናቸው።

ማሕሌት መቆመ፣ ክታቡና ክብረ በዓላቱ በሙሉ የዚች ምድር ልዑል ከሆነው ለሰይጣን የክብር መክፈያ መንገዶች ናቸው። ጠንቋዩ በክፍተኛ ጥንቃቄ የተገኘ ዕውቀትና ምስጢር ባለቤት ሲሆን፣ ይህን ዕውቀቱንም ጎይልንና መረጃን ለማግኘት ይጠቀምበታል። ጠንቋይን መፈታተን የሚያመጣውን ብዙ ችግር ያልተመለከተ በመንዝ ውስጥ የለም። ብዙዎች ለጠንቋዩ ያላቸው ስሜት በፍርሀትና በጥላቻ የተሞላ ነው።

የእንቆቅልሹን ምስጢር ይገልጽልን ጀመር። ብዙዎቹ የሚያደርጉት የጨለ ሀብልና ሁሉም ሕፃን የሚያደርገው ጌጣ ጌጥ ሁሉ ጥቅሙ ለጌጥነት ብቻ አልነበረም። ከጠንቋዩ የተሰጡና ክፉውን መንፈስ ማባበያ ናቸው። በተጨማሪም ጥቂት ሰዎችን ከወርቅ የተሠሩ ጌጦችን በአንድ ጆሮአቸው ብቻ አደርገው ተመልክተናል። ጌጡ በሰዎቹ ላይ ዛር ወይም ርኩስ መንፈስ እንዳለባቸው የሚያሳይ ምልክት እንጂ በአጋጣሚ የተደረገ እንዳልሆነ በመጨረሻ ተረዳን።

የሰይጣንን ችሎታ ያዩ የመንዝ ነዋሪዎች ሰዎቹን እንዲተዋቸው ከመመኘት ሌላ ትልቅ ምኞት የላቸውም። ይህንን ማየት የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ ደግሞ ከግቢው ውስጥ አንድ ሴት በስሕተት መወንጀሏን ስትቀበል ነው። ሴቲቱ በፈቃደኝነት ዛሩን ወይም ርኩስ መንፈሱን በመደበቅና ራሷን እንዲቈጣጠራት በማድረግ የቀረውን ቤተ ሰብ ታድናለች። በእርሷ መሥዋዕት በሽታን፣ ያዝመራ ብልሽትን፣ መቅሠፍትንና ሞትን እንደሚያመልጡ ያስባሉ። ሰይጣንን አልታዘዝም ብሎ ኋላ ዕዳውን ያልከፈለ ሰው መኖሩን ሕዝቡ አያውቅም። ጠንቋዩ ዛሩን በማሰገደድ ወደ አንድ ሰው እንዲገባ ወይም ከአንድ ሰው ውስጥ እንዲወጣ ያደርጋል።

በተጨማሪም ጠንቋዩ ጎይለኛ በረዶ እንዳይጥል ይከላከላል። ሁልጊዜ የዝናቡ ወቅት ጎይለኛ በረዶ የተቀላቀለበት ዝናብ ይታይበት ነበር። ዐዲስ የተዘራውን እህል ከበረዶ እንደሚጠብቅላቸው በማሰብ፣ ጠንቋዩ በዕርሻው ላይ ድግምት ደግሞ እህላቸውን ከውድመት ይከላከልላቸው ዘንድ በቤተ ሰቡ አንድ አንድ ብር ይከፈለዋል። ከዚህ ዐይነቱ ሥራ ብቻ ቄስ ግርማ በዓመት ሁለት ጊዜ ዘጠና ብር ያገኛል። ምንም እንኳ ዛርን የማስገደድ ጎይል ባይኖረውም፣ እግዚአብሔር ፊቱን እስከ መለስለት ጊዜ ድረስ እየተለማመደው ነበር።

እሑድ ዕለት ቄስ ግርማ ሲመጣ ብዙ ሰው በድንኳኑ ተሰብስቦ ይጠባበቅ ነበር። አጠገቡ ያለውን ዕንጨት በማቀጣጠል ላይ ሳለን ለመናገር ተነሣ። ጠንቋይ ሆኖ ያሳለፈውን ሕይወት ሲናገር የእያንዳንዱ ዐይን በእርሱ ላይ ነበር። እንዴት ተሳስቶ እንደ ነበርና እግዚአብሔርም በሚያስገርም ሁኔታ እንዳሳመነው ተናገረ።

ኦሪት ዘዳግም 18÷10-11ን ያነበበ መሆኑንና ሕይወቱ ምን ያህል አስከፊ እንደ ነበር ነገራቸው። ሟርተኛ፣ ወይም መተተኛ፣ ጠንቋይ፣ መናፍስት ጠሪ ወይም ሙት አነጋጋሪ፣ በድግምት የሚጠነቀሉ፣ እባብን በአስማት የሚቈጣጠር ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ እንደ ሆነ በግልጽ ተናገረ። የቄስ ግርማን ሕይወት የሚገልጸው ከዚህ የበለጠ ቋንቋ ሊገኝ አይችልም። በአንድ ጊዜ ጠንቋይም ክርስቲያንም መሆን እንደማይቻል አመነ።

በዚያ የነበሩት በሙሉ ጠንቋይ እንደ ነበር ስለሚያውቁ፣ ይህን ልምምድ ለምን መተው እንደ ወሰነ ለማወቅ ይፈልጉ ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በኢየሱስ ክርስቶስ በሙሉ ልቡ ሊያምን ነው። ቄስ ግርማ

የጥንቁላ መጻሕፍቶቹን አውጥቶ ወደ እሳቱ ሲጨምራቸው በተመለጠ ከሚመለከቱት ሰዎች መካከል ቍርጥ ቍርጥ እያለ የሚሰማ ትንፋሽ ሾልኮ ተሰማ።

ለሁሉም ሰው የማሰቢያ ጊዜ እየሰጠ የእሳቱ ነበልባል መጽሐፎቹን አቃጠለ። ክርስቲያን በእግዚአብሔር ብቻ ማመን እንዳለበትና ዲያብሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሸነፈ ሚሲዮናውያኑ ይናገሩ እንደ ነበር ሰዎቹ ያውቃሉ። የውጭ አገር ዜጋ ስለ ሆንን ለመፍረድ እንደሚቀለን ዐሰቡና የእኛን ምስክርነት ከመጤፍም አልቈጠሩትም። ለነገሩ እነርሱ ያለባቸው ችግር እኛ የለብንም። ከጠንቋይ ጋር አንገናኝም።

አሁን ግን የራሳቸው የሆነው ቄስ ግርማ መጥፎውን ነገር በሙሉ ለመጣል ፈቃደኛነቱን እያሳየ ነበር። ሰይጣንን እየተቃወመ ሕይወቱን በኢየሱስ እጆች ላይ እያስቀመጠ ነበር። የአግራሞትና የፍርሀት ስሜት በድንኳኑ ውስጥ ሰፈነ። ሁሉም በዚያ ዐይነት መንገድ ይሳካለት ዘንድ ተመኘ። እንዲኖራቸው የሚመኙትን ነጻነት ቄስ ግርማ አግኝቷል። ነገር ግን ውጤቱ ምን ይሆን? ቄይተው ማየት ይርባቸዋል።

ስለ ቄስ ግርማ የጀግንነት አቋም በቀያ ወሬ እንደ ሰደድ እሳት ተሠራጨ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን እንደሚበቀለው ወይም እግዚአብሔር እንደሚበልጥ ለማየት የሁሉም ሰው ዐይን በእርሱ ላይ ሆነ። የውጊያው መሥመር በግልጽ ተሠምሮ ነበር።

በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድም፣ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል በቤርያ ሞምር መስበኩን ባወቁ ጊዜ፣ ሕዝቡን ለመቀስቀስና ለማነሣሣት ወደዚያ ደግሞ ሄዱ።

የሐዋርያት ሥራ 17÷13

ዐመፅን ማነሣሣት

ቄስ ግርማ ውሳኔውን አልቀየረም። እሑድ እሑድ በቤተ ክርስቲያኑ ለሚሰበሰቡት ሰዎች ከቅዳሴ በኋላ መስበክ ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ከሌሎች ይበልጥ ታጋሾች ነበሩ።

የጥንቁላ መጽሐፎቹን ካቃጠለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በቤተ ክርስቲያኑ የሚከበረው ዓመታዊ በዓል ደረሰ። ወደዚያ በዓል ከሺ በላይ ሰዎች ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይህንን በማሰብ መንገዘ ሰዎች ወንጌልን መስማት ካለባቸው ይህ ጥሩ የመጀመሪያ ዕድል እንደሚሆን ወሰነ። ስለዚህ የሚሰብከውን ማዘጋጀት ጀመረ። ንግግር የማድረግ ተራው ሲደርሰው ስለሚናገራቸው ቃላት አወጣ አወረደ፤ ጸለየም። ሊናገር ያሰውን ለመስማት ፈጽሞ እንደማይፈልጉና ሰውጥን እንደማይወዱ ያውቅ ነበር። ሆኖም ሰዎቹን መምከር እንዳለበት ተሰማው።

ሲጠበቅ የነበረው የቀጠሮ ቀን በሚያምርና በጠራ ሁኔታ ነጋ። እንደ ልማዱ በአንድነት የተሰበሰበው ሕዝብ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተገኙቶ ታቦቱን ከማጀብ ወደ አንድ ከፍታ ቦታ ደርሶ ተመለሰ። ሰዎቹ በመመለስ ላይ ሳሉ ቤተ ክርስቲያን ከደረሱ በኋላ ስለሚመገቡት ምግብ ያስቡ ነበር። ያ ሁኔታ በጣም ለሚወደደው የበዓል አከባበር እጅግ ከፍተኛው ደረጃ ነበር።

ሥርዐቱ እንዳለቀ ወዲያውኑ ታቦቱ ወደሚቀመጥበት ስፍራ ሲገባ፣ ቄስ ግርማ ለመናገር ተነሣ። በሰዎቹ መካከል በቀስታ የሚደረጉ ንግግሮች ቀጠሉ። ለሚናገረው ነገር አትኩሮት የሰጠው ሰው አልነበረም። ነገር ግን የንግግሩን ጫፍ ሲያዳምጡ ያልተለመደ ነገር እየተፈጸመ እንደ ነበር አስተዋሉ። ምን እየተካሄደ እንዳለ ለመገመት ጆሮአቸውን ሰጡ።

የሰዎችን ያልተከፋፈለ ትኩረት ሲመለከት ቄስ ግርማ በጥንቃቄ ያሰበበትን መልእክት በእምነት አስተላለፈ። ጊዜ የማይሽረውን እውነት ማለት ሰው ኀጢአተኛ እንደ ሆነና እግዚአብሔር እንደሚያስፈልገው በድፍረት ሲናገር፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ በግልጽ ይሠራ ነበር። የሚናገረው እንደ ገባቸው ለማረጋገጥ የተሰበሰቡት በሙሉ ሁልጊዜ የሚያደርጓቸውን ልማዶች በመጠቀም ቀላል ምሳሌዎችን ሰጣቸው። በዚህ ጊዜ ዋናው ጉዳይ ላይ ደረሰ። ስለ እነርሱ እየተናገረ እንደ ሆነ ተረዱ።

«ነገር ግን ተስፋ አለ» በማለት ቀጠለ፤ «እነዚህ ጎጢአቶች ለእግዚአብሔር ንሰሓ በመግባትና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ በመቀበል ይቅር ሊባሉልን ይችላሉ።» በጸጥታ ሲያዳምጥ የነበረው ሕዝብ ወዲውኑ ማጒረምረምና ዙሪያውን መገለማመጥ ጀመረ። ከዚያም ከመካከላቸው አንድ ሰው ተነሥቶ መጮኽ ጀመረ፤ «እዚህ የመጣነው ይህንን ሁሉ ልናዳምጥ አይደለም። እንዲህ ብሎ እኛን ለመናገር ምን ዐይነት መብት አለው?»

ቄስ ግርማ ንግግሩን መቀጠል እስኪያቅተው ድረስ ግራ መጋባት በመፈጠሩ ተቀመጠ። በዚያ ቀን ከሌሎቹ ሰዎች ጋር ለመመገብ አልቄየም። በጣም ተስፋ ቈርጦ ነበር። በድጋሚ በመንዝ ያሉ ሰዎች ምንም ተስፋ እንደሌላቸው አመነ። ሰዎቹ በራሳቸው መንገድ እየሄዱ ነበር። መኖሪያ ቤቱ ድረስ እየሄደን አወራን። በመቀጠል ጸለይንና ለጥቂት ጊዜ ለመሞከር ወሰነ።

ምንም እንኳ በመንዝ ስልክ ባይኖርም፤ ጉዞውም ሁሉ በእግር ወይም በፈረስ የሚደረግ ቢሆንም፤ መጥፎ ወሬና አሉባልታ በፍጥነት ይዳረሳል። ቄስ ግርማ ሞክሮት የማያውቀውን በመስበኩ የደረሰበት ተቃውሞ ጠንካራና አፋጣኝ ነበር። ጥቂቶች ስብከቱን እኛ እንደ ጻፍንለት ተናገሩ። ራሱን ችሎ እንደማያደርገው እርግጠኞች ነበሩ። ብዙዎች ደግሞ በትክክል እየከፈልነው እንደ ነበር እርግጠኞች ነበሩ። በሕይወቱ ለታየው መሠረታዊ ለውጥ በአእምሮአቸው ውስጥ የተቀመጠው ግምታዊ ሐሳብ ይህ ብቻ ነበር።

ከአሉባልታዎቹ ጋር ደግሞ በራሱ ሕይወትና ንብረት ላይ ብቻ ሳይሆን በባለቤቱና በልጆቹ ላይ ማስፈራራት ይደርስ ጀመረ። ለብቻው መንዝ ወይም ከቤት ራቅ ወዳለ ስፍራ መሄድ አደገኛ ሆነ።

እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሳም ካናታ በመሐል ሜዳ ለሚኖሩ ተማሪ ዎችና የመንግሥት ሠራተኞች መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምር ነበር። ብዙዎቹ ዳግም የተወለዱ አማኞች ነበሩ። ሳም ቄስ ግርማን ምስክርነቱን ለተማሪዎቹ ያካፍል ዘንድ ጋበዘው።

ብዙዎቹ ተማሪዎች በኦርቶዶክስ ቤተ ሰብ ውስጥ ያደጉ ናቸው። ነገር ግን ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ከቤተ ሰቡ እምነት ሸሹ። ብዙ ጊዜ ትምህርት የጥንቱን ልማድ አሳንሶ ማየት ያስችላል። ስለዚህ ብዙ ጊዜ ተማሪዎች ከገጠር ሕይወት ጋር የተያያዘ ማንኛውም ነገር ኋላቀር እንደ ሆነና መቅረት እንዳለበት ያምናሉ። በሚያሳዝን ሁኔታ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ሁልጊዜ በዚህ ምድብ ይመደባል።

በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ቄስ ግርማ ሲያዳምጡት የነበረው ባለው የኅላፊነት ቦታ ብቻ ነበር። ነገር ግን ብዙም ሳይቈዩ እንደ ሌሎቹ የሀገሩ ቄሶች እንዳልሆነ ተረዱ። እነርሱ የሚያውቁትን አዳኝ እርሱም ያውቀዋል፤ ደግሞም በክርስቶስ ወንድማቸው ነበር።

ከምስክርነቱ በኋላ ሁሉም በአንድነት ጸለዩና እርስ በራሳቸው ተበረታቱ። እንደ አማኞች የነበራቸው ኅብረት ልዩ በሆነ የመዳን ደስታና እግዚአብሔር ሊሠራው ባለው ነገር በነበራቸው ጕጕት የተቀላቀለ ነበር። ከዚያ ጕብኝት በኋላ ቄስ ግርማ ብቸኝነትም ሆነ ተስፋ መቊረጥ አይሰማውም ነበር። ከተማሪዎቹ ደግሞ ምስክርነቱን ከሰሙት መካከል ዐምስቱ በሚቀጥለው ቀን ክርስቶስን ተቀበሉ።

ብዙም ሳይቈይ ስለ ተቃጠለው መጽሐፍ ሰማን። ያ ጊዜ ግን ለየት ያለ ጊዜ ነበር። የተቃጠለው መጽሐፍ ቅዱስ ነበርና።

ወደ ቀያ ድንኳናችንን ከወሰድን ከዐጭር ጊዜ በኋላ ነበር የጀመረው። አንድ ቀን ጠባዩ ጥሩ የሆነና አደገኛ ውሻ እግሩን ነክሶት ትልቅ ቍስል ያለበት አንድ መነኩሴ መጣ። እግሩ ከቁስለበት ትንሽ ቈይቶ ነበርና ከመታሸጉ በፊት የቍስሉን አካባቢ ማጽዳት አስፈላጊ ነበር። በጥንቃቄና በቀስታ ቍስሉን እያጠብሁ አወራን።

ሰውዬው የመነኰሰው ባለቤቱ ከብዙ ዓመታት በፊት በሞት ስትለየው ነበር። በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ከመጀመሪያ ባለቤቱ ውጪ ሌላ ሴት አግብቶ ቄስ ሆኖ መቀጠል አይችልም። ድጋሚ ሳያገባ መነኰሴ ሆኖ ከካህናቱ ጋር የቅስና አገልግሎቱን ግን መቀጠል ይችል ነበር። ስለዚህ መነኰሴው ቤት ስላልነበረው፤ ጊዜውን በመንዝ እየተዘዋወረ ያሳልፋል። ሲዘዋወር በተለይ በመንፈሳውያን በዓላት ወቅት ይሰብካል ወይም ያስተምራል።

ቍስሉን ለማጽዳትና ለማሽግ የተወሰነ ጊዜ ስለ ወሰደ፤ ስለምንሠራው ሥራ ለእርሱ ለመንገር ከበቂ በላይ ገዜ ነበረኝ። ከመሄዱ በፊት በተሟላው የመጻሕፍት ስብስብ ላይ እንዲጨምረው የአማርኛ አዲስ ኪዳን መጽሐፍ ሰጠሁት። በሚጓዝበት ቦታ ሁሉ ይዞት የሚሄደው የቄዳ ቦርሳው ብቻ ነበር። በዚያን ጊዜ አዲስ ባገኘው መጽሐፍ ከልቡ ተደሰቶ ነበር።

ከሦስት ወራት በኋላ ከቀያ በስተምዕራብ በምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚከበር በዓል ላይ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት አዲስ ኪዳን መጽሐፉን እንዳቃጠለው ሰማን። መጽሐፉ የዲያብሎስ መጽሐፍ እንደ ሆነ ተናገረ። የሐሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ራእይ 1÷8ን ጠቀሰ። «አልፋና አሜጋ እኔ ነኝ ይላል» ወደ ጠንቋይ ሄዶ የሚያውቅ ሙሉ በሙሉ ምስቅልቅል ያሉ ምስጢራዊ ቃላትን ይሰማል። ከእነዚህ ቃላት መካከል «አልፋ» እና «አሜጋ» ይገኙበታል። መጽሐፍ ቅዱስና ጠንቋይ በአንድ ዐይነት ቃላት ይጠቀማሉ። ከዚህ በላይ ምን ማረጋገጫ ያስፈልጋል?

ማንኛውም በቤተ ክርስቲያን ሊቅ የሚነገር ሐሳብ ሁሉ በሕዝቡ ዘንድ ያለ ምንም ጥያቄ ተቀባይነት አለው። ለነገሩ የቤተ ክርስቲያኗ መሪዎች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ምስጢርና ዕውቀት

የሠለጠኑ ናቸው። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በግእዝ ቋንቋና በአማርኛ ትርጕሙን በሙሉ እንደሚያውቁ ተደርጎ ይታሰባል። ይህ መነኩሴ ይህ ነገር ርኩስ ነው ብሎ ከተናገረ መሆን አለበት። ይህን መጫ የሆነ መጽሐፍ ስላስወገደላቸው ደስተኞች ነበሩ።

ሰይጣን መልሶ ለማጥቃት ጦሩን በሙሉ ያሰለፈ ነበር የመሠለን። በግልጽ እንደሚታየው ደግሞ በጥቂቱ እየተሳካለት ነበር። ማንም ማስታወስ ከሚችለው ጊዜ በላይ ተቈጣጥሮት የነበረውን ቦታ ለመከላከል ተገዶ ነበር።

እርሱም እንደ እነርሱ ድንኳን ሰፊ ስለ ነበረ፣ ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ በተመሳሳይ ሥራ ላይ ተሰማራ።

የሐዋርያት ሥራ 18÷3

ድንኳኖችን መሥራት

ዝናብ መዝነብ ሲጀምር ሁሉም ወደ ግብርናው ተመለሰ። በዝናብ የለሰለሰው ዐፈር በመጨረሻ ላይ ለመታረስ ሲበቃ እህል ለመዝራት ይችላሉ። ደረቁና ቡናማው ገጠር አዝመራው ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምር በአንድ ምሽት የተለወጠ መሰለ።

ድንኳናችንን እፍርሰን ወደ ቤት ሄደን ጥቂት ጊዜ ለማሳለፍ ዐሰብን። እየተወያየን ሳለ አንድ አውሮፕላን ምልክት ለመስጠት በድንኳናችን ላይ ዝቅ ብሎ በረረ። ሮጠን ስንወጣ አውሮፕላኑ የሚሲዮናውያን ጎብረት (የMAF(Missionary aviation fellowship) ንብረት እንደ ሆነ ተረዳን። የአውሮፕላን አብራሪው ድጋሚ አንድ ጊዜ ዞረና ትልቅ የፖስታ ሻንጣ ወደ ታች ወረወረ።

ብዙ ሳምንታት ፈጅቶ ከተሰበሰበው ወረቀት መካከል አንድ ትንሽ ማስታወሻ አገኘን። አንድ ሺ ምንጣፍ ትእዛዝ ያለበት ማስታወሻ ነበር። በድጋሚ እያነበብን በርካታ ቊጥር ሊኖራቸው ስለሚችሉ ነገሮች ተወያየን። ወዲያውኑ ዋና ዋናዎቹ የቀያ ሰዎች ሊያነጋግሩን ወደ እኛ መጡ። ሕዝባቸውን ለመርዳት ከልባቸው ይፈልጉ ነበር። በፀሓይ ሲና የነበረውን የተሳካ የምንጣፍ ሽመና ፕሮጀክት አይተው ስለ ነበር፣ በቀያም ይህን ተመሳሳይ ሥራ መሥራት እንደምንችል ለማወቅ ይፈልጉ ነበር።

አንድ ሰውየ ብዙ ቤቶች ያሉት ትልቅ ግቢ ነበረው። አንደኛውን ቤት ዝናብ ሲዘንብ እንስሳቶቹን ለማቈየት ብቻ ነበር የሚጠቀምበት። የሽመና ክፍል እንድናደርገው ፈቃደኛ መሆኑን ገለጸልን። ከዚህ በኋላ አንድን ወጣት ልጅ ወስደን በዐዲስ የሽመና ሥራ ልናሠለጥን ፈለግን። ከዚህ ውሳኔ ላይ የደረስነው ያ ወጣት ሌሎችን በማስተማር እንደሚረዳን በማሰብ ነው። ከጠቂት ሳምንታት በኋላም ወደዚያ ቦታ ልንመለስ ቃል ገባን።

ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታችን በፊት ሬይ በሕዝብ ልማት ቡድን ውስጥ እንደሚሠራ ያስብ ነበር። ልዩ ሥራው እጅ ሥራ አስተማሪ እንደሚሆንም ያውቅ ነበር። ያንን ሥራ ለመሥራት ያለው ብቃት ግን በታሪክ ቢ ኤ ዲግሪና በባዮሎጂ ትምህርት ኤም ኤ ነበር። በአሜሪካ ለሁለት ዓመት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲያስተምር የቈየ ሲሆን፣ በናይጀርያ ደግሞ በሚስዮናውን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሦስት ዓመት አስተምሯል።

ለሥራው ብቁ የሚያደርገው ለየት ያለው ነገር፣ ነገሮች እንዴት እንደሚሠሩ የማስተዋል የዕድሜ ልክ ልምዱ፣ የማይጠቅሙ ከሚመስሉ ነገሮች አንድን ዕቃ መሥራት መቻሉና አንድ ነገር እንደማይሠራ የሚያምነው ከመከራ በኋላ መሆኑ ነው። ከሚያየው ነገር ሁሉ በማይጠቅሙት ክፍሎች ሳይዘናጋ መሠረታዊውን ነገር ለይቶ የማየት የተፈጥሮ ችሎታ አለው።

በኢትዮጵያ በመንዝ ውስጥ ስለምንሠራበት ቦታ ሲያጠና ሁሉም በግ አርቢ እንደ ሆነ አስተዋለ። የሚረቡት ሥጋቸው ለምግብነት ስለሚውል ነው። ነገር ግን ከዋናው ምርት ጋር እኩል የሆነው ተረፈ ምርት ደግሞ ጸጉራቸው (ሱፍ) ነው። የመንዝ ሴቶች በኢትዮጵያ ጉበዝ ጥጥ ፈታዮች እንደ ሆኑ ይታሰባል። ይህንን የሚያደርጉት በእንዝርት በመጠቀም ነው። ይህ አሠራር አሰልቺና ቀስያለ ቢሆንም፣ ከዚህ ውጭ ሌላ መንገድ አያውቁም።

ይህ በእጅ የተፈተለ ሱፍ ቀዝቃዛውን የተራራ አየር ለመከላከል በብዛት በሚሠራ የተሸመነ ብርድ ልብስ ላይ ይውላል። ከገቤ የሚቀርበው ብርድ ልብስ ከመብዛቱ የተነሣ ሸማኔዎቹና ጥጥ ፈታዮቹ የሚያገኙት ትርፍ አነስተኛ ነው።

በከተማው ውስጥ ሱፉን ለሌላ ጥቅምም ያውሉታል። በሽመና ትንንሽ ምንጣፎችን ይሠሩበታል። ብዙ የእጅ ሥራ ትምህርት ቤቶች በኢትዮጵያ ባህል ዲዛይን የተሠሩ ማራኪ ምንጣፎችን ይሠራሉ። ምንጣፎቹ የሚሠሩት በትምህርት ቤቱ ባሉ በትልልቅ የሽመኔ ዕቃዎች ላይ ሲሆን፣ ዐዲስ ተማሪ መግባት የሚችለው ይማር የነበረ አንድ ተማሪ ሲያቋርጥ ብቻ ነው።

በምዕራብ አሜሪካ በማደጋችን አሜሪካውያን ሕንዶች የሚሠሯቸውን የሚያማምሩ ምንጣፎች እናውቃለን። ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታችን በፊት በማዛታቸው ጥቂት ጊዜ ቈይተን አንድ ሽማኔ ሲሸምን ተመለከትን። በተለይ ሬይ በሰውየው የሽመና ጥበብ ማለትም የሽመና መሣሪያውን በመወጠርና ምንጣፍ የሚሠራበትን የፀጉር ክር በማዘጋጀት ዘዴው ላይ የተለየ ትኩረት አድርጎ ነበር።

ስለ ትምህርቱ የተጻፉ መጽሐፎችን አግኝቶ የትምህርቱን ቅደም ተከተል በመጽሐፉ ውስጥ በተገለጸው መሠረት በአእምሮው እየሳለ በጥንቃቄ አነበባቸው። ኢትዮጵያ በደረሰንበት ጊዜ ሬይ ስለ ሽመና ብዙ ያውቅ ነበር። ይህንን ተመርኩዞ በአዲስ አበባ የሚገኙ የእጅ ሥራ ትምህርት ቤቶችን እየጐበኘ የሚሠሩትን አወዳደረ።

የኢትዮጵያ ምንጣፍ ከአሜሪካውያን ሕንዶች በወፍራምነቱ ቢለይም፣ መሠረታዊ የሽመና ሕጎቹ ግን አንድ ናቸው። ሬይ አስተውሎ ሲመለከታቸው ባለሙያዎቹ የሚያደርጉት ነገር በሙሉ አስፈላጊ ስለ መሆኑ እርግጠኛ ሆነ። በተጨማሪም የሚጠቀሙበት

መሣሪያ እነርሱ እንደሚሠሩት ውድና የተወሳሰበ መሆን እንደሌለበት ዐሰበ።

ወደ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመጣ በአዲስ አበባ የአማርኛ ቋንቋ እያጠናን ሳለ፣ በመንዝ ደግሞ ሚስዮናውያን የሚሠሩት የእጅ ሥራ ትምህርት ቤት እየተሠራ ነበር። በከተማው ውስጥ ለብዙ ጥቅም የሚያውሉትና በሦስት መቶ ብር የሚገዛው የምንጣፍ መሥሪያ የሚገዛውና የሚታሸገው በትምህርት ቤቱ ክፍል ውስጥ ነበር። እስከዚያው እኛ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርታችንን ጨረስንና ወደ መንዝ መጥተን የመኖርያ ቤታችንን ሥራ መከታተል ጀመርን። ኢትዮጵያ ከደረስን ከዓመት በኋላ ሬይ ለመጀመሪያ ጊዜ የሽመና ትምህርት ለማስተማር ዝግጁ ነበር።

ስለ ምንጣፍ ሽመና እኛ መንዝ ከመሄዳችን በፊት በዚያ አካባቢ ተሰምቶም አያውቅም። ሰዎቹ ስለ ልብስ ሽመና በደንብ ያውቃሉ፣ እንዲያውም በእኛ አካባቢ ችሎታ ያላቸው ብዙ ሸማኔዎች ነበሩ። የእጅ ሥራ ትምህርት ቤታችንን ስንከፍት የመጀመሪያው ችግራችን ተማሪዎችን ማግኘት ነበር።

ሰዎቹ ልንሠራው ስለምንፈልግ ስለ ዐዲሱ ሥራ በግልጽ ይጠራጠሩ ነበር። ትምህርቱ ብዙ ሰዓትን እንደሚፈጅና ገንዘብ ሊገኝበት እንደማይችል ዐሰቡ። ስለዚህ ለመማር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች አልነበሩም። ችግሩ የተቀረፈልን መጀመርያውኑ ወደ መንዝ በወሰደን የልዕልት ተናኘ ወርቅ የሕግ አማካሪ በነበረው በአቶ ገብረ ሕይወት አማካይነት ነበር።

ከቤተ ክርስቲያን የሚያገኙት ጥቂት ስለ ሆነ ቋሚ ደሞዝ የሚያስፈልጋቸው ቄሶችና ዲያቆኖች እንደ ሆኑ ዐሰበ ። በዚህ ተማምኖ ወደ መንዝ መጣና ከአካባቢው ዋና ቄስ ባገኘው ምክር መሠረት በግሉ የመጀመሪያዎቹን የሽመና መሣ ሠልጣኝ አባላት መረጠ። ትምህርት ቤቱ በሃያ ዐምስት ተማሪዎች ተከፈተ። ሰዎቹ ወደ ትምህርት ቤቱ ይመጡ የነበረው ፈልገው ሳይሆን፣ አቶ ገብረ ሕይወት መሄድ እንዳለባቸው ስለ ነገራቸው ብቻ ነበር።

በዚያን ጊዜ ሠልጣኞቹ ሽማኔ ለመሆን ዐዲስ እንደ ሆኑት ሁሉ፣ ሬይም ሽመናን ለማስተማር ዐዲስ ነበር። በተጨማሪም የምንጣፍ ዲዛይንን መሥራት ለሬይ በጣም ዐዲስ ነበር። ነገር ግን ሊሠራው የሚችል ሌላ ሰው ከሌለ መሠራት ነበረበት። በመጀመሪያዎቹ ምንጣፎች ላይ የበግ፣ የአንበላ፣ የቤተ ክርስቲያን፣ የመፈክርና የጀኤሜትሪ ዲዛይኖችን ሞከረ።

ከመጀመሪያዎቹ ምንጣፎች መካከል አሁንም ጥቂቶቹ አሉ። ልክ የአንደኛ ክፍል ተማሪ እንደሚሞነጫጭረው ያለ ውበትና ጥበብ ነበረው። ሆኖም በዚያን ሰዓት በታላቅ ኩራት ነበር የምንመለከታቸው። ተማሪዎቻችን በእውነተኛም ምንጣፎችን እየሸመኑ ነበር።

ብዙም ሳይቈይ ሬይ በምንጣፉ ላይ የኢትዮጵያን መስቀል ዲዛይን ሞከረ። እርግጥ ዲዛይኑ ትክክል ነበረ። መስቀሎቹ በውበታቸው የታወቁና የተለያዩ ክፍላተ ሀገር የፈጠራ ውጤቶች የሆኑና በርካታ የተለያዩ ዲዛይኖች ያሏቸው ናቸው። ሬይ የተለያዩ የመስቀል ቅርጾችን ወደ ምንጣፍ ንድፍ ለወጣቸው።

በተጨማሪም ከዲዛይኖች መሻሻል ጋር በሽመናው ተግባር ላይም የሽመናው ሥራ በፍጥነት እየተከናወነ በሄደ ቍጥር ምንጣፎቹ እያማሩ መጡ። ሬይ በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ የባሕር ዛፍ አገኘ። በተጨማሪም የቢንጂ ዕቃዎች ከሚሸጡበት ስፍራ ገመድና ቢንጂ ገዝቶ ዐስራ ዐምስት ብር የፈጀ በጣም ጥሩ የሽመና መሣሪያ ሠራ።

የመጀመሪዎቹ የሽመና ተማሪዎች በቤታቸው የየራሳቸውን የሽመና ዕቃ በመሥራት ነበር የተመረቁት። ለሁለተኛ ዙር ለማስተማር ተማሪ በማግኘት ረገድ ምንም ችግር አልነበረም። ምክንያቱም የመጀመሪያዎቹ ሽማኔዎች ገንዘብ ሲያገኙ ታይቷልና በድጋሚ ያተኰርነውም ዲቆናትና ቀሳውስት ላይ ነበር። ሥራችን በአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ እምነትን ለማሳደር የሚከናወን እስከ ሆነ ድረስ፣ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር መሥራታችን ጥሩ ነበር። በተጨማሪም አንድ የሃይማኖት መሪ የራሱን የኑሮ ወጭ መሸፈን የቻለበትን የጳውሎስን የድንኳን ሥራ መርሕ አምነን ተቀበልነው።

በየቀኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን እነርሱ የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ እየተሰማመዱት ሲመጡ፣ እኛ ደግሞ ቃላቱን እያወቅን ሄድን። አካሄዳችን ሁለት ዐይነት ሂደት ነበረበት፤ እነርሱ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ይጠይቃሉ። እኛ ደግሞ በምን እንደሚያምኑ እየተረዳን መጣን።

የሦስት ዓመት ጉዞአችንን ከመጨረሳችን በፊት እያደገ የሄደ የምንጣፍ ንግድ ሥራ ነበረን። አሁን ሁሉም የሽመና ተግባር የሚከናወነው በቤታቸው ነበር። ሬይ የሽመና ዕቃውን ለመጠገን ወይም የሁልጊዜ ምክር ለመስጠት ይሠራ ነበር። ጥቂቶቹ አንድ ክፍል ሊሸፍን የሚችል ምንጣፍ የሚሠራ የሽመና ዕቃ ነበራቸው። የተለመደው የምንጣፍ ገበያ ልዩ ልዩ ዲዛይኖችና የተለያየ መጠን ያላቸው ምንጣፎች ለሽያጭ ሲቀርቡበት ይታያል።

ተማሪዎቹ ሽመናን ከተማሩ በኋላ በንግዱ ላይ የነበረን ዋና ኀላፊነት ምንጣፎቹን ገዝተን ወደሚሸጥበት ወደ ሚሽን ጠቅላይ መምሪያ መውሰድ ነበር። ለምንጣፎቹ መሸጥ በአዲስ አበባ ገበያ ከማደጉ ጋር ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ትእዛዝ ይደርሰን ጀመር። ከአንድ ዓመት በኋላ ፕሮጀክቱ ራሱን የቻለ ሆነ። ለእያንዳንዱ ወር ገበያ የሚመደበው ገንዘብ ካለፈው ወር ሽያጭ ነበር የሚገኘው።

ለአንድ ሺ ምንጣፍ ትእዛዝ ሲደርሰን የምንጣፉ ንግድ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነበር። ነገር ግን በዚህን ጊዜ የተፈለገው የምንጣፍ ዐይነት በሰሜን ኢትዮጵያ የሚሠራው ልመጥ ምንጣፍ ነበር።

ብዙዎቹ የተመለከትናቸው ምንጣፎች የማይስቡና በቸልተኝነት የተሠሩ ነበሩ። በገበያ ላይ የጥራት ቍጥር ስለሌለ፣ ሬይ ተማሪዎቹን የተሻለ ምንጣፍ እንዲሠሩ እንደሚያስተምራቸው ወሰነ።

በቀያ የሽመናን ትምህርት በተሰጠን ቤት ውስጥ ጀመርን። ዐሥራ ስምንት ተማሪዎች በአቅራቢያ ካሉ አብያተ ክርስቲያናት ተመረጡ። ግማሾቹ የመጽሐፍ ቅዱሱን ጥናት መርሐ ግብረ በጕጕት ይከታተሉ ከነበሩት መካከል ነበሩ።

ተማሪዎቹ የትምህርቱን መሠረታዊ ዘዴ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀባቸውም ነበር። እጆቻቸው ሽመናውን በጥበባዊ ሁኔታ ለማቀላጠፍ አልሰነፉም። በየቀኑ የከሰዓት በኋላ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አለን። ነገር ግን አንድ ቀን እነርሱ ሲሠሩ መጽሐፍ ቅዱስን እናነብላቸው ዘንድ ጠየቁን። ትኩረት በመስጠት ያዳምጡ ነበር። ጣልቃ የሚገቡትንም አንድ ነገር እንዲደገምላቸው ሲፈልጉ ወይም ያልተረዱት ነገር ካለ ብቻ ነበር።

ትልቅ ችግር የነበረው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በጭራሽ አለመተዋወቃቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ሳለን ለእያንዳንዱ ቍጥር በአማርኛው ትርጉም ላይ ተመሳሳዩን እንፈልግላቸው ነበር። ስለ ችግሩ ብዙ ካሰብንበት በኋላ ከዓመታት በፊት ችግሩ እንደ ተቀረፈ አስተዋልን። ለዚህ ችግር መፍትሔው የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች እየደጋገሙ በፍጥነት የማግኘት የቡድን ውድድር ማድረግ ነበር።

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በአማርኛ በዝርዝር ጽፈን ለጠናቸው። ዝርዝሩን በማስታወስና ያለ ስሕተት በቃል በመዘርዘር ክፍሎቹን ፈልጎ ማግኘትን ተለማመዱ። እንደ ተዘጋጁ ሲያስቡ ፈተና ለጠናቸው። በዐሥራ ዐምስት ሰከንድ ወይም ባነሰ ሰዓት ውስጥ ከዐዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ክፍል ማግኘትና ከፊቱና ከኋላው ላይመለከቱ ምን ክፍል እንዳለ ከተናገሩ፣ ዐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ይሸለማሉ። ለብሉይ ኪዳንም ተመሳሳይ ችሎታ ካላቸው ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይሰጣቸዋል።

ብዙዎቹ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሸለሙ ይወዳደሩ ዘንድ እንፈቅድላቸዋለን። ሁልጊዜ እሑድ ከሰዓት በኋላ ስበሰባችን ሲጠናቀቅ በሽመና ክፍል ውስጥ ይቀመጣሉ። በመቀጠል እኔ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እጠራለሁ። የሚፈልጉትን እግኝተው ለማመልከት የሚያሳዩት ጕጕት የሕፃናትን ጕጕት ይመስል ነበር። በሕገ መሠረት የሚፈልጉትን ክፍል ሲያገኙ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ተራምደው በጣታቸው ማመልከት አለባቸው። በጣም በስሜት በተሞሉበት ጊዜ ግን አንድ እርምጃ ወደ ፊት መራመዳቸው ለጀብድነቱ የሚያጓጓ ነበር። ስለዚህ ወደፊት ብዙ እርምጃዎችን መራመድ ወይም ‹ይኸው!› ብሎ መጮኽን ይመርጡ ነበር። ይህ የሞቀ የውድድር ልምምድን በመካከላቸው ሊፈጥር ቻለ።

ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስተማሪያ መሣሪያ ማለት የካሴት ማጫወቻ ነበረን። የአማርኛ ስብከቶችና መዝሙሮች በካሴት ላይ በአዲስ አበባው የሚሲዮን ስቱዲዮ ውስጥ ይቀዳ ነበር። ካሴቶችንና የካሴት ማጫወቻዎችን የሚያውስ ቤተ መጻሕፍት ከፈትንና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጥሩ ፍላጎት ላላቸው ለማደል አስቀመጥነው።

በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ አማርኛን አቀላጥፈው የሚናገሩ በፕሮቴስታንት ክርስቲያኖች የቀረቡ መዝሙሮችንና ስብከቶችን አዳመጡ። ሁልጊዜ የካሴት ማጫወቻዎቹ እንዲሠሩ በማድረግና በማን እጅ እንደ ነበሩ ማስታወሱ ቀላል ባይሆንም ጥቅሙ ይበልጥ ነበር። ተማሪዎቹ በርከት ያሉ ካሴቶችን በማድመጥ መስበክንና መዘመርን እየተለማመዱ ሄዱ።

ከአሎ ከመሄዳችን በፊት የጀመረው ዝናብ ለብዙ ሳምንታት ቀጠለ። ነገር ግን የሽመናውን ትምህርት ለመጀመር ወደ ቀያ በሄድንበት በዚያ ቀን ሙሉ በሙሉ ዝናቡ አቆመ። ሰዎቹ ዝናቡ እንደሚቀጥል ዐስበው ስለ ነበረ እህል ዘሩ። የተዘራው ብቅ ብቅ ማለት ጀምሮ ነበር። ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆኖ ከቁየ ሁሉም ነገር ይሞታል፤ አዝመራም አይኖራቸውም። ከዚህም የባሰው ነገር ደግሞ ለወደፊቱ የሚዘሩት እህል አይኖራቸውም ማለት ነው።

በመጀመሪያ ሕዝቡ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታቦቱን እንዲወጣ አስደርገው ዝናብን ይሰጣቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ። በመቀጠል ደግሞ ወደ ጠንቋይ ሔዱ። ነገር ግን ከዚያም በኋላ ዝናብ አልጣለም። አንድ ሰው እኛ በቀያ ድንኳናችንን እንደ ተከልን ዝናብ የቆመ መሆኑን አስታወሰ። ድንኳኑ እስከዚያ ጊዜ ድረስ እንደ ተተከለ አለ። ዝናብ ያልጣለው ግን ድንኳን ከተተከለበት ቀን አንሥቶ ነው። በግልጥ ሊመለከቱት ይህ ሁኔታ የሆነ ግንኙነት ያለው ይመስላል።

የምንኖርበትና የምናስተምርበት ግቢ የሚገኘው ከሸለቆ በላይ ባለ በጣም ከፍ ያለ ድንጋይ አጠገብ ነው። በየሳምንቱ ጫፍ ላይ መኪናችንን አቁመን ዕቃችንን ወደ ታች ይዘን ነው የምንወርደው። አንድ ቀን አንድ ጓደኛችን መኪናችንን ከሚቆምበት ቦታ እንድናነሣው መከረን። የእኛን በዚያ መኖር የማይወዱ ጥቂት ሰዎች ስለ ጉዳዩ ሊነጋገሩ እንደ ሰማ ነገረን። መኪናችንን ቁልቁል ወደ ታች ገፍተው ገደል ውስጥ ሊጥሉት በማቀድ ላይ ነበሩ።

በሌላኛው መንገድ በሸለቆ ጫፍ ዞሮ በትንሹ ጅረት ዐልፎ ላንድ ሮቨራችንን ከግቢው አጠገብ ለማቆም አንድ ሰዓት ይፈጃል። ነገር ግን አንዴ ከግቢው አጠገብ ከቆመ፣ ከቅርብ እየተመለከትን መጠበቅ እንችላለን። በየትም አቅጣጫ ተገፍቶ ሊገለበጥ ደግሞ አይችልም።

በቀጣዩ ቀን ዝናብ ዘነበ መሬቱን እንደ ብርድ ልብስ የሸፈነ ጎይለኛ በረዶ ነበር። በረዶው በድንኳናችን ጣራ ላይ ተከማችቶ ነበር። ከከፍታው ስፍራ ጉርፍ ድንኳን ወደ ተከልንበት ስፍራ ሲመጣ፣ ትንሽ

የተከላከለው ነገር ዐጥሩ ብቻ ነበር። ወዲያውኑ ድንኳናችን በውሃ ተሸነፈ።

ያጋጠመንን አሥጊ ሁኔታ የተመለከቱ ሽማኔዎች ከሽመናው ክፍል በፍጥነት መጥተው ውሃው ዐልፎ እንዲሄድ በድንጋዩ ግርግዳ ላይ ቀዳዳዎችን በረበሩ። ሬይም ደግሞ ቱቦ ይቁፍር ነበር። በዚህ ሁኔታ ችግሩ ተወገደ። ይህ መፈጠሩ ደግሞ ድንኳናችን ዝናቡን አቁሞታል የሚለው አሉባልታ እንዲቆም ረዳን። ከዚህ በኋላ ስለ መኪናችን ምንም ዐይነት ፍርሀት አላደረብንም።

በአንድ እሑድ ዕለት በውድድር አሸንፈው ያገኙትን መጽሐፍ ቅዱስ የያዙ ዲያቆናት ከአቃፌ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔዱ። ከቅዳሴ በኋላ ለተሰበሰቡት ሰዎች ከዐዲስ ኪዳን ሊያነቡላቸው ሞከሩ። ነገር ግን የነበሩት ሰዎች ተበሳጭተው ከማንኛውም መንዘ እጅ በማይጠፉው ዱላ አባረሯቸው። ከዚህ የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል በቡታ ክርስቲናቸው ለማሰማት ጊዜው ገና እንደ ሆነ ለመደምደም ተገደዱ።

ጊዜ እያለፈ በሄደ ቍጥር ነገሮች አስደሳች እየሆኑ መጡ። ሳምንቱን ሙሉ በሽመና ክፍል እነርሱ እየሠሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይኖረንና አሑድ ደግሞ ትልቅ ስብሰባ ይካሄዳል። ሰዎቹ እኛን በግል ለማነጋገር በብዛት ይመጡ ጀመር። የሚሸለመው መጽሐፍ ቅዱሶችም ቍጥር እየጨመረ ሄዷል። የካሴት ሬዲዮ በተከፈተ ቍጥር ለማድመጥ የተዘጋጀ ሕዝብ ሁልጊዜ አለ።

ነገር ግን እስከዚያ ጊዜ ድረስ ያገኘነው በክርስቶስ ዳግም የተወለደ አንድ አማኝ ብቻ ነበር። ከተወለዱ አንሥቶ ክርስቲያን ነን ብለው በሚያምኑት በእነዚህ ወጣት ወንዶች ልብ ውስጥ ጌታ እየሠራ እንደ ሆነ ይሰማን ነበር። ቢሆንም በርግጠኛነት ይህን እንዴት እናውቃለን? ምን እያሰቡ እንደ ሆነ የምናውቅበት ምንም መንገድ የለም። የመነቃቃት ስብሰባ እንዳኖረን ወሰንን። በመሀል ሜዳ በቅርቡ ተሠርቶ ያለቀው ማኅበረ ሰብ ልማት አዳራሽ ለእንግሊዙት ዝግጁ ነበር። በሮቹንና መስኮቶቹን ያዘጋጀው የእኛ ሚሲዮን ነበር። በአሜሪካን አገር የለመድነው የመነቃቃት ፕሮግራም ለሳምንት የሚዘልቅ በመሆኑና አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ረጅም መንገድ ተጉዘው በመምጣታቸው የስድስት ቀን የመነቃቃት ፕሮግራም እንዲኖረን ዐቀድን።

የምንጀምርበት ቀን እየተቃረበ ሲመጣ በጉጉት እየተሞላን ነበር። በርግጥ ማን እንደሚመጣ የምናውቅበት መንገድ አልነበረም። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ላይ የሚገኙትንና የእኛ ሚሲዮናውያን አዘውትረው ከሚሄዱባቸው ዐሥር አብያተ ክርስቲያናት የሚመጡትን ቀሳውስትና ዲያቆናት ጋብዘን ነበር። እንዲመጡ ስንጋብዛቸው በትሕትና ነበር ያደመጡን ነገር ግን ምን ሊያደርጉ እንዳሰቡና ምን እንደ ተሰማቸው ምንም ዐይነት ምልክት አላሳዩም።

እንግዲህ፣ እግዚአብሔር ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፣ ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይረዳ፣ ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው እጅግ ተነካ፣ ጴጥሮስንና ሌሎቹንም ሐዋርያት፣ «ወንድሞች ሆይ፣ታዲያ ምን እናድርግ?» አሏቸው። ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፣ ንስሓ ግቡ! ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

የሐዋርያት ሥራ 2÷36-38

መነቃቃት

በመጨረሻ ላይ ዝግጅት ተደርጎ እንዳለቀ የሚጠበቀው ቀን ደረሰ። በጊኒ ካናታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚገኙ ሴቶች ሳምንቱን ምግብ የማዘጋጀት ሥራ በዝቶባቸው ነበር። ከገቢያ ገብስ ተገዝቶ ወደ ከተማው ወፍጮ ቤት ሊፈጭ ተወሰደ። አንድ ላምም ወደ ካናታ ግቢ እንዲመጣ ተደርጎ በቂስ ከተባረከ በኋላ ታረደ። ከዚያም ሥጋው ተበስተና እንዲደርቅ ተንጠለጠለ።

በማኅበረ ሰቡ አዳራሽ አንድ ጥግ ላይ ለመተኛት እንዲመች ጭድ ተጉዘገዘ። በካሴት ሬዲዮ ላይ ድምፁን የሚያውቁት ሰባኪ ንጉሤ ተፈራና ከእኛ ከሚሰዮናውያን መካከል የሆነው ዩሐንስ ቼን ለስብሰባው ከአዲስ አበባ መጥተው ነበር።

እሑድ ምሽት ላይ ለሳምንት ፕሮግራም ሥልሳ ዐምስት ቀሳውስትና ዲያቆናት መጡ። በማግስቱ በአቅራቢያ ያሉት በአያንዳንዱ ቀን እየተመላለሱ ለመካፈል መምጣት ሲጀምሩ ቍጥራቸው ከመቶ በላይ ነበር። በቦታው የተገኘው ሰው ቁጥር ካሰብነው በላይ ሆነ።

በየቀኑ ለእያንዳንዱ ሰዓት በአንድ ነገር ላይ መርሐ ግብር ነድፈን አዘጋጅን። መርሐ ግብሩ ስብከትን፣ ትምህርትን፣ ዐጫጭር ፊልሞችን፣ በፍጥነት የሚሸከረከሩ ሠንጠረዦችን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ፈልጎ የማግኘት ውድድርን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የማስታወስ ሥራን፣ የቡድን ውይይትን፣ የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜዎችንና መዝሙርን ያጠቃለለ ነበር። ከጠዋት አንሥቶ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ስድስታችን እየተከፋፈልን እነዚህን ሁሉ ለመምራት ችለን ነበር።

የከተማውን ሰዎች በየቀኑ 11 ሰዓት ላይ እንዲመጡ ጋበዝናቸው። ተማሪዎችና የመንግሥት ሠራተኞች በእነዚህ ሰዓታት ላይ አዳራሹን በጣም ይሞሉታል። የአማርኛ መዝሙሮችን በመዘመር እንጀምረለን። ተማሪዎቹ መዘመር ይወዳሉና አዳራሹ ከድምፃቸው የተነሣ ያስተጋባል። ኦርቶዶክሳውያን ጓደኞቻችን ከዚህ በፊት እንደዚህ ዐይነት መዝሙር ሰምተው ስለማያውቁ ተደስተውና ስሜታቸውም ተነሣሥቶ ነበር። የመዝሙሩ ግጥምም ተጽፎ በእጃቸው ስለ ነበር ዑደረው ለመዘመር በጣም ይጥሩ ነበር።

በስብሰባው ላይ በጣም ማራኪ ከነበሩት ሥራዎች መካከል አንዱ በቀደ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያጠኑ በነበሩት ቀሳውስት፣ ዲያቆናትና በዶክተር ካናታ ቤት በሚማሩት ተማሪዎች መካከል የተካሄደው አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ፈልጎ የማግኘት ውድድር ነበር። የዶክተር ካናታ ተማሪዎች ብዙውቹ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ነበሩና ስለ ውድድሩ ከሳምንታት በፊት ሲሰሙ ቀልድ መስሏቸው ነበር። ከሌሎቹ በሚበልጠው የትምህርት ደረጃቸው በመደገፍ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የመፈለጉን ውድድር በቀላሉ እንደሚያሸንፉ እርግጠኞች ነበሩ። በቅንነት መዘጋጀት የጀመሩትም ዶክተር ካናታ ቁም ነገር ያለበት ውድድር መሆኑን ካሳመናቸው በኋላ ነበር።

የውድድሩ ሰዓት ሲደርስ ተሳታፊዎቹ ፊታቸውን ወደ ተመ ልካቹ አድርገው ተሰለፉ። ቁሶቹና ዲያቆናቱ ሲሠሩ የከተማው ሰዎች ይመለከቷቸው ስለ ነበር፣ ጓደኞቻቸው ያሰምንም ችግር እንደሚያሸንፉ እርግጠኞች ሆኑ። ተማሪዎቹን ጨምሮ ለመወዳደር ጠንካራ የነበሩት ከዐምስት አብያተ ክርስቲያናት የመጡት ነበሩ። በመጀመርያው ምሽት የማጣራት ዙሮች ነበሩ። ተማሪዎቹ በተሳተፉባቸው ውድድሮች ሁሉ አሸነፉ። ከአቃፊ የመጡት ዲያቆናትም በውድድሩ አሸንፈው ነበር።

በቀጣዩ ምሽት ሁለቱ ቡድች ፊት ለፊት ተገናኙ። ሁሉም ሰው ሁለቱም ቡድኖች ሲወዳደሩ ስላያቸው፣ ውድድሩ ቀላል እንደ ማይሆን ተገመተ። አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ፈልጎ ለማግኘት የነበራቸው ፍጥነት አስደናቂ ነበር። ከዚህ የተነሣ ብዙዎቹ በዐይ ናቸው ተመልክተው ባያረጋግጡ ኖሮ ፈልገው ያገኙአቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማመን ይቸገሩ ነበር።

ውድድሩን ለማሸነፍ አንድ ቡድን ከሦስት ዙሮች ውስጥ በሁለቱ ብዙ ነጥቦችን ማግኘት አለበት። አንድ ዙር የሚያልቀው አንድ ቡድን ዐሥር ነጥብ ላይ ሲደርስ ነው። በመጀመሪያ ላይ ተማሪዎቹ ፈልጎ በማግኘቱ ተግባር ተሳክቶላቸው ነበር። ነገር ግን በቂ ቍጥር አልነበራቸውም። ከቀደ የመጡት ዲያቆናት እያንዳንዱን ዙር ያለምንም ክርክር አሸንፈው ነበር። በማንኛውም ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው ስላልተማሩ ከሕዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር ሲወዳደሩ የበታችነት ስሜት ተሰምቷቸው ነበር። ነገር ግን በዚያ ምሽት ይህ ስሜት አልታየባቸውም።

በመጨረሻም ቀዳሚ ተግባሩቱ ተጠናቀቁና የመልእክቱ ጊዜ ደረሰ። ዩሐንስ ቼንና ንጉሤ በየምሹቱ ረዘም ያለ ብዙ ስብከት ይሰብኩ ነበር። ምንም እንኳ መልእክቶቻቸውን ለየብቻ የሚያዘጋጁ ቢሆንም፣ በግልጽ እንደ ታየው ሁለቱንም ተመሳሳይ መንፈስ እየመራቸው ነበር። ግልጽ የሆነውንና ዋናውን ሐሳብ ይናገሩ ነበርና አድማጮቹ በሰሙት ሁሉ ልባቸው ተነክቶ ነበር።

ከምሽቱ አንድ ሰዓት በፊት ፕሮግራሙን ለመጨረስ እንሞክራለን። በዚያን ሰዓት ሁሉም ላይመሽበት ተቻኩሎ ወደ ቤቱ

ስለሚሄድ፣ በፍጥነት አዳራሹ ባዶ ይሆናል። ከዚያም ሌሊቱን በዚያ የሚያሳልፉትን ቀሳውስትና ዲያቆናት ምግብ እንዲመገቡ እናደርጋለን። አራት አራት እየሆኑ በመሶቡ ዙሪያ ይቀመጣሉ። ከዚያም እንጀራና ወጥ በተጨማሪም የተቀቀለ ሥጋ እናቀርብላቸዋለን። ሻይና ፍራፍሬ ተርቦ ካበቃ በኋላ ምግቡ ተበልቶ ይጠናቀቃል። ቀኑን ሙሉ ሥራ በዝቶባቸው ከዋሉ በኋላ ዘና ሊሉ ማቅና ጨዋታ በቀላሉ ይጀምራሉ። በዚህ ጎብረት ውስጥ እኛም እንቀላቀላለን። በመጨረሻ እኛም በመሶቡ ዙሪያ የመቀመጡን ዕድል እናገኛለን።

የቀኑ ፕሮግራማችን በዚህ ዐይነት ተጠናቀቀ። ነገር ግን የተሻለው ገና ይቀጥላል። በእያንዳንዱ ምሽት እራት ከተበላ በኋላ ጭዱ ላይ ተቀምጠን በንጉሤ የሚመራ ነጻ የሆነ ውይይት ይኖረናል። መጽሐፍ ቅዱሱን በውጪም በውስጥም ያውቅ ነበርና በግልጽ እንደ ታየው በመልሶቹ ሁሉ የጌታ ምሪት ይታይ ነበር። የሚስዮናውያንን ያህል መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ ማግኘታቸው ለሰዎቹ ዐዲስ ነገር ነበር። በጣም ከመደሰታቸውና ከመገረማቸው የተነሣ ሰምተው አይጠግቡትም ነበር።

ረቡዕ ዕለት የከሰዓቱ አገልግሎት እንዳለቀ የበለጠ መማር የሚፈልጉ ወይም ልዩ ጸሎት የሚያስፈልጋቸው ካሉ እንዲቂዩ ሁሉንም ጋበዝናቸው። ቄይተን ግን እንደሚጨልምና ስብሰባውን መዝጋት እንዳለብን ተረዳን። ሁልጊዜ ምሽት ላይ ወደ ቤት የሚያደርሳቸው ብርሃን ሳይጠፋ ለመሄድ ይፈልጉ ነበር።

በጸሎት ስብሰባውን ከዘጋን በኋላ የዕለቱ ስብሰባ እንዳለቀ መሄድ የሚፈልግ መሄድ እንደሚችል አስታወቅን። በሚያስገርም ሁኔታ ማንም አልተንቀሳቀሰም። በግልጽ እንደ ተረዳነው ንግግራችን አልገባቸውም ነበር። ሌላ ጊዜ እንደምናደርገው ምናልባት አማርኛውን ተሳስተን ይሆናል በማለት በድጋሚ ነገርናቸው። በዚያ ጊዜ በኋላ ሰዋሰዋዊ ስሕተት ሠርተን ድጋሚ እንዳይገባቸው እንዳናደርግ በጣም ተጠነቀቅን። ነገር ግን ማንም አልተንቀሳቀሰም። በቋንቋው ላይ ያለንን ውሱን ችሎታ በመጠራጠር ንጉሤ እንዲነግራቸው ጠየቅነው። ስለዚህ እርሱ በጥንቃቄ ነገራቸው። ቢነግራቸውም ቁጭ ብለው በተስፋ ይጠብቁ ጀመር።

በመጨረሻም ያልገባን እኛ እንጂ እነሱ እንዳልሆኑ ግልጽ ሆነልን። ሁሉም ተጨማሪ ትምህርትን ለመስማት ፈልገው ነበር። ስለዚህ ንጉሤ በድጋሚ ጎጢአተኛ መሆንን ማመን ምን ማለት እንደ ሆነ አብራራላቸው። ጎጢአተኛ እንደ ሆኑ ካመኑ በኋላ ከእግዚአብሔር ይቅርታን መጠየቅ አለብን። ኢየሱስ አንዴ የጎጢአትን ዋጋ ስለ ከፈለ ሌላ ነገር ማድረግ አስፈላጊ አይደለም። በቀጣዩ ቀን ንጉሤን ወይም አንድን ሚስዮናዊ ለማናገር ለሚፈልጉ ሰዎች ነገሮችን ካዘጋጀን በኋላ ገለጻውን በጸሎት ጨረስን።

ከእራት በኋላ ምስክርነቱን ለምሽቱ ቀሳውስትና ዲያቆናት ማካፈል ይፈልግ እንደ ሆነ ቄስ ግርማን ጠየቅነው። ሲጸልይበት እንደ ነበረ ነገረን። ምንም እንኳ ትንሽ ቢፈራም ለመናገር ግን ፈልጎ ነበር። ትክክለኛው ጊዜ ያ ጊዜ እንደ ሆነ ለእርሱም ተሰምቶት ነበር።

የተሰበሰቡት በሙሉ ሲናገር ዐይናቸውን ከእርሱ ላይ ሳይነቅሉ በጽሞና አዳመጡት። እርሱ የሚናገረውን ዐይነት ነገር ሰምተው አያውቁምና እንዲት ቃል እንኳ እንድታመልጣቸው አልፈለጉም። ጥንቁላ ጎጢአት እንደ ሆነ፣ እንዴት እንዳመነና የነበረበትን ክፉ ልማድ ሙሉ በሙሉ እንዴት እንደተው ተናገረ። የጥንቁላ መጽሐፉን በማቃጠል ሕይወቱን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ጣለ። ይህን የጀማና ሥራ ከሠራ ሦስት ወራት ዐልፈዋል። ሰይጣንም እስካሁን እርሱን ለመንካት አልቻለም። እግዚአብሔር በእምነት ይጠበቀው ነበር። መንፈስ ቅዱስ ቄስ ግርማን ሲናገር እየመራው ነበርና ምስክርነቱ የብዙዎችን ልብ ነካ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ተናግሮ ሲያበቃ፣ ሰዎች ጸጥ ብለውና በተ መሰጠ ውስጥ ገብተው ነበር ማስተዋል ያለባቸው ብዙ ነገር ነበርና።

ከዚያ ቀን ቀደም ብለን እንዴት መጸለይ እንደሚገባ መማር ለሚፈልጉ እንደምናስተምር ቃል ገብተን ነበር። በመጨረሻ የከሰዓት በኋላው አገልግሎት እንደ ተጠናቀቀ ትክክለኛው ጊዜ ያ እንደ ሆነ ተረዳን። በመጀመሪያ ጸሎት በቀላሉ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደ ሆነ አስረዳን። ጸሎት በአንድ ወገን በኩል ብቻ የሚደረግ ንግግር ሳይሆን መናገርንና ማድመጥን ያጠቃልላል። በቀላሉ እንዲገነዘቡት ግልጽ የሆነ ምሳሌ ሰጠናቸው። እግዚአብሔርንና መልካም አባትን አነጻጸርን። ልጆቹ ችግራቸውን ይዘው በፊቱ ሲቀርቡና ለእርሱ ሲነግሩት ይደሰታል። ልጆቹን ስለሚወዳቸውም ሊረዳቸው ይፈልጋል። በተፈጥሮ ደግሞ ስለ መለሰላቸው ሲያመሰግኑት ደስ ይሰኛል።

አባት ለልጆቹ ምግብን፣ ልብስንና መጠለያን፣ የሚስፈልጋቸውንም ሁሉ ያዘጋጃል። እርሱን ረስተው እርስ በርሳቸው ብቻ ሲነጋገሩ ያዝናል፤ አይረዳቸውምም። እርሱን እንዲያነጋግሩት ማድረግ ይችላል ሆኖም ያንን አያደርገውም። ግዴታ ስለ ሆነባቸው ሳይሆን ስለሚወዱት በፈቃደኝነት ወደ እርሱ ቢመጡ ይመርጣል። የምድር አባታችንን እንደምናናግረው ሁሉ ሰማያዊ አባታችንን ማናገራችን ትክክልና ጥሩ ነው።

በአማርኛ መጸለይን የተለማመዱ መሪዎች ሁሉ በክፍሉ ዙሪያ ተሰበጣጥረው ተቀመጡ። ከዚያም የቀሩትን ሰዎች ይቀላቀሉ ዘንድ አበረታታናቸው። ብዙዎቹ ነገሩን ለማወቅ ካላቸው ጉጉት የተነሣ ወይም እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅ ባላቸው ልባዊ ፍላጎት ምክንያት ተቀላቀሉ። እግዚአብሔርን የማነጋገሩን ዕድል ያገኙ ዘንድ ራሳችንን ዝቅ አድርገን ጸለይን። በዕድሜ ዘመናቸው ሁሉ እርሱን ለማገልገል ሲጥሩ የነበሩ ብዙ ሰዎች እስከዚያ ጊዜ ድረስ ያላወቁትን እግዚአብሔርን አነጋገሩት።

በዚያ ምሽት መንፈስ ቅዱስ በብዙዎቹ ልብ ውስጥ ይሠራ ፡በርና የመጀመሪያውን እምነት ርምጃ እንዲራመዱ አበረታታቸው። በመጀመሪያ ላይ በማመንታት ሲናገሩ፣ የተቃወማቸው ወይም የተሣለቀባቸው ሰው ስላልነበረ፣ በራሳቸው ተማመኑ። ይህ ስብሰባ ለእነርሱ ምን ማለት እንደ ሆነ በማወቃቸው እግዚአብሔርን አመሰገኑት።

የጸሎት ጊዜ ወደፊትም እንደሚቀጥል በመጠበቅ ስሜት ተጠ ናቀቀ። ጌታ እየሠራ እንደ ነበር በግልጽ ይታይ ነበር። በዚያ ምሽት በቀላሉ እንቅልፍ አልወሰደንም። በጣም የሚያስደስት ቀን ነበር። ለቀጣዩ ቀን ደግሞ ምን እንደሚዘጋጅልን ዐሰብን የሚዘጋጅልን የበለጠ እንደሚሆን ተሰማን።

አላዘንም ነበር። እንደ ተለመደው አንድ ሰባኪ ወይም አስተማሪ የአጸፋ ምላሽ የሚጠበቅበትን ጉባኤ በትምህርት ያነቃቃል። የቀኑ መልእክቶች በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ የተመሩና በዚያ የተሰበሰቡትንም ፍላጎት በሚገባ ያሟሉ ነበሩ።

ብዙዎቹ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከገጠር የመጡ ስለ ነበሩ፣ ከተማውንና የከተማውን ሱቆች የመጐብኘቱን ዕድል ስላላገኙ፣ የጎሙሱን ዕለት ከሰዓት በኋላ ጊዜ ልንሰጣቸው ወሰንን። የሆነው ሆኖ በምስጋና ፈንታ ቅሬታ መኖሩን ተረዳን። ለመማር ስድስት ቀን ብቻ እንዳላቸውና በሌላው ጊዜ ወደ ገበያ እንደሚሄዱ ተናገሩ። ምንም ጊዜ ማባከን አልፈለጉም። ስለዚህ መቁየት ለፈለጉት የውይይት ቡድኖችን መሠረትን።

ልክ ሥራችንን ስንጀምር አንድ ሰው ወደ ውስጥ ገባ። የገባው እያጉረመረመና ጮኽ ብሎ እያወራ ነው። ሰውየውን ለማነጋገር አይቻልም ነበር መጠጥ ጠጥቶ ሞቅ ብሎት ነበርና። ሳም ካናታ ወጥቶ ሊያግባባው ሞከረ ነገር ግን መጨረሻ ላይ ማስፈራራት ጀመረ። ስብሰባችንን በዚያ ሁኔታ መበጥበጡን ካላቆመ ፖሊስ እንደምንጠራ ሳም ካናታ ነገረው።

ሳም ካናታ የተናገረው እንዳለቀ ወዲውኑ አንድ ፖሊስ ወደ ውስጥ ገባ። የሰከረው ሰውዬ ፖሊሱን እንደ ተመለከተ በፍጥነት ወጣ። በአጠገቡ እየተካሄደ ያለውን ነገር ያላወቀው ፖሊስ ኪሱ ውስጥ አንድ አጁን አውጥቶ የታሸገ ጣቱን ለሳም ካናታ አሳየው። ቀደም ብሎ እጁን ያሸገለት ሳም ከሳምንት በኋላ ተመልሶ እንዲመጣ ነግሮት ነበርና። የፖሊስ ጣቢያው ከማኅበረ ሰቡ የልማት አዳራሽ አቅራቢያ ስለ ነበር ቀደም ሲል ለመምጣት ወስኗል። ልክ በዚያን ሰዓት መምጣቱ አጋጣሚ እንዳልነበር በጣም አርግጠኞች ነበርን።

ምሽት ላይ እንደተለመደው ለውይይታችን ስንሰባሰብ ተሳታፊ ዎች እንዲናገሩ ዕድል የምንሰጥበት ጊዜ ያ ጊዜ እንደ ሆነ ተሰማን። በዚያ ሳምንት እግዚአብሔር በልባቸው ውስጥ ምን እንዳስቀመጠ

ለመናገር የሚፈልጉ እጃቸውን እንዲያወጡ ጠየቅናቸው። እጃቸውን ያወጡ ይሆን? ወይም እጃቸውንም ቢያወጡ የሚናገሩት ነገር ትርጉም ይኖረው ይሆን? ብለን ዐሰብን።

በሚያስደንቅ ሁኔታ ሁሉም እጃቸውን አወጡ። በባህላቸው መሠረት በዕድሜ የሚተልቁት መነኩሴ ይናገሩ ዘንድ መድረኩን ሰጧቸው። ስለ ሌለ ነገር ሳያወሩ ቀጥታ ወደ ነጥቡ ገቡ። ጌታ በሕይወታቸው በሠሩት ኀጢአት ስለሚፈርድባቸው ንስሓ መግባትንና የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንደሚፈልጉ ተናገሩ። የእኒህ መነኩሴ ምስክርነት በልባቸው ውስጥ ይከብዳቸው የነበረውን ሸክም ያምኑ ዘንድ ለሌሎቹ መንገድ ጠረገላቸው።

በዚያ ጊዜ እኔና ሬይ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣን ዐምስት ዓመት ሆኖን ነበርና አማርኛችንም የበለጠ እየተሻሻለ ነበር። ነገር ግን በዚያ ምሽት ሰዎቹ የሠሩትን ኀጢአት ሲዘረዝሩ ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ ጊዜ በኋላ ትርጉማቸውን ልናውቅ የማያስፈልጉንን ቃላት ተናገሩ። ነገር ግን እያንዳንዱ የዐሥርቱ ትእዛዛት ሲጠቀስ በበቂ ሁኔታ ሰምተን ተረዳን። ዝሙትና ስርቆት የተለመዱ ኀጢአቶች ቢሆኑም ነፍስ ግድያም ተጠቅሷል። በመንዝ ከሚገኙት ወንዶች መካከል እነዚህ የተሻሉ ነበሩ። አንድ ሰው ተናግሮ እንደ ጨረሰ ወዲውኑ ሌላ ሰው በቦታው ይተካና ንስሓ ገብቶ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ይጠይቃል።

እኩለ ሌሊት ላይ መዘመር ጀመሩ። ከመዝሙረ ዳዊት ላይ የለመዷቸውን የድሮ መዝሙሮች በግእዝ ቋንቋ ሲዘምሩ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳቸው ላይ ትርጉማቸውን ተመለከቱ። ሲያነቧቸውም በሚያስተላልፉት መልእክት ተደሰቱ። አንድ ሰው ከበሮ ሲመታ፣ ሌሎቹ ድምፃቸውን ከፍ አድረገው፣ ውድ ልጁን አዳኝ አድርጎ የላከላቸውን እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። ሰምተን የማናውቃቸውን ልዩ መዝሙሮች ለሰዓታት ሳያቋርጡ ዘመሩ።

ሁሉም በልባቸው ውስጥ ያለውን በሙሉ እንዲናገሩ ሌሊቱ በቂ አልነበረም። ነገር ግን ለእነርሱ ያ ጥሩ ጅማሬ ነበር። በመጨረሻም ንጋቱ እየተቃረበ ሲመጣ ጥቂት ሰዓት ተኙ። በቀጣዩ ቀን ማለዳ ላይ ብዙ ቀሳውስትና ዲቆናት በፀሓይ ሲና ለቀብር ሥርዐት ተጠሩ። ሌሊቱን እዚያ በማሳለፋቸውና ከዚያ በፊት በዚህ ሁኔታ ስላልተጠሩ እግዚአብሔርን አመሰገንን።

በዚያ ቀን ከሰዓት በኋላ ሌላ የመጠጥ ሞቅታ የሚታይበት ሰው ወደ እኛ መጣ። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ መልስ ያልሰጣቸውን ጥያቄዎች ማለት «ሙሴ የት ነበር የተቀበረው?» በማለት በቀጣ ጠየቀ። እርሱ ከውስጥ እየጮኸና እየተከራከረ ሳለ ሌላ ቡድን ከውጪ ደረሰ። በቡድኑ ውስጥ ያሉት ሰዎች በመንዝ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የሚቈጣጠረውና በመሐል ሜዳ የሚገኘው ቤተ ክህነት መሪዎች ነበሩ። ሥራቸው በአዲስ አበባ ላሉት ጳጳስ ተጠሪ

በመሆን በመንዝ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት በጎላፊነት ማስተባበር ነው።

ያንን ስብሰባ እንድናዘጋጅ ማን ሥልጣን እንደ ሰጠን ሊጠይቁን ነበር የመጡት። መጀመሪያውኑ ችግር እንደሚያስከትል በማሰብ ሳም ከብዙ ሳምንት በፊት ከቢሮአቸው ሁለት ቁሶችን አነጋግሮ ነበር። ቁሶቹ በድንገት ተጠርተው ከመንዝ ከሄዱ ሁለት ሳምንት ዐልፏቸው ነበር። ጌታ በዚህ መንገድ ችግሩን እንደ ቀረፈው ተሰማን።

እየተከራከሩን ላለ በድጋሚ ጌታ ጣልቃ ገባ። ሰክሮ የነበረው ሰውዬ ከውጪ ሆኖ ክርክሩን ሲሰማ ምን እየተካሄደ እንዳለ ለማወቅ ዘሎ ገባ። በፍጥነት ለእኛ በመወገን ከቤተ ክህነት የመጡትን ግን በመቃወም ይጮኽባቸው ጀመር። አባረራቸውና ጠፋ። ነገሮች ሲስተካከሉና ጸጥታ ሲሰፍን ውይይታችንን ቀጠልን።

ያለፈው ምሽት ድንቅ ልምምድ አልተደገመም። ዐርብ ቀን ላይ ብዙዎቹ ወደ ውጭ ወጥተው ነበርና ምሽት ላይ ስንሰባሰብ ብዙ ሐሳብን የሚወስድ ነገርና ረብሻ ነበር። ይህ የእግዚአብሔርን ሥራ መገመት እንደማንችል ዐዲስ ትምህርት አስተማረን። ማድረግ የምንችለው ጥሩ ነገር እግዚአብሔር ሲሠራ ዕድሉእንዳያመልጠን ሁልጊዜ ተዘጋጅተን መጠበቅ ነው።

ቅዳሜ ጠዋት ከመሄዳቸው በፊት አንድ የመጨረሻ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራም አካሄድን። ዐብረን ብዙ ጊዜ ያሳለፍንና መልካም ሐሳብን የተከፋፈልን ሰዎች ለመሰነባበት አቃተን። ብዙዎቹ ወደ ቤት ሲሄዱ ከስድስት ቀን በፊት ከነበረው ማንነታቸው ብዙ ተለውጠው ነበር።

ፀሓይ ሲና ወደሚገኘው ቤታችን ስንመለስ መንገዱን በሙሉ ለድንቅ ሥራው እግዚአብሔርን እያመሰገንን ነበር። በላያችን ላይ ባፈሰሰው በረከት ተጥለቅልቀን ነበር። በመንዝ ምድር እንዲታይ ብዙ ጊዜ የጸለይንበት መነቃቃት መጨረሻ ላይ እውን ሆነ። የሰይጣን ጎይሎች ዳግም ላይነሡ ድል ተመቱ።

ነገር ግን ዲያብሎስ በቀላሉ ተስፋ አይቈርጥም። ባለው መሣሪያ ሁሉ ታገለ። የመልስ ምቱንም የሰነዘረው ከስብሰባው ጥቂት ቀናት በኋላ የሚዋጋበት መሣሪያ እንደ ጋለ ነበር።

«ይሁን እንጂ ይናገርበት የነበረውን ጥበብና መንፈስ መቋቋም አልቻሉም። ስለዚህ፣ «እስጢፋስ በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ሲሰነዝር ሰምተናል» የሚሉ ሰዎችን በስውር አዘጋጁ። በዚህ ሁኔታ ሕዝቡን፣ የአገር ሽማግሌዎቹንና የሕግ መምህራኑን በማነሣሣት፣ እስጢፋስን አስይዘው በአይሁድ ሸንጎ ፊት አቀረቡት፤ እንዲህ ብለው የሚመሰክሩ የሐሰት ምስክሮችንም አቆሙበት፤ «ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራና በሕጉ ላይ የስድብ ቃል መናገሩን በፍጹም አልተወም፤ ምክንያቱም ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ስፍራ እንደሚያጠፋና ከሙሴ የተቀበልነውን ወግ እንደሚለውጥ ሲናገር ሰምተናል።»

የሐዋርያት ሥራ 6÷10-14

ስደት

ስብሰባው ካለቀ ከሁለት ቀን በኋላ ስለ ስብሰባው የአሉባልታ ወሬ ተናፈሰ። በስብሰባው ያልተሳተፉ ብዙ ቀሳውስትና ዲያቆናት በተሳታፊዎች ላይ ጥርጣሬ ዐደረባቸው። ስብሰባው ላይ ያልተጋበዘ ማንም ቁስና ዲያቆን ስላልነበር፣ እነርሱን ጥፋተኞች አድርገው መወንጀል ከፈለጉ ምክንያቱ ሌላ ነገር መሆን ነበረበት። ወዲያውኑ አንድ ሐሳብ አፈለቁ። በእነሱ አስተሳሰብ መሠረት ትክክለኛውን የክስ ምክንያት ፈጠሩ።

ስብሰባው ላይ የአህያ ሥጋ እንደ መገብናቸው ወሬ ተናፈሰ። መቼም ከአህያ ሥጋ የበለጠ መጥፎ ነገር አይኖርም። አህያዎቹ የተሰነጠቀ ሰኮና ስለሌላቸው፣ በብሉይ ኪዳን የአመጋገብ ሕጎች ላይ በማይበሉ እንስሳት ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። አርቶዶክሳውያን የአይሁድን የአመጋገብ ሕግ በጥንቃቄ ያከብሩ ነበርና ይህኛው መከበር ያለበት ስለ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። የአህያ ሥጋ ሊበሉ ቀርቶ የሞት አህያን እንኳ አይነኩም።

በእነርሱ አስተሳሰብ ያልተቀደሰ ወይም የረከሰ ነገርን መብላት ወይም መንካት ያረክሳል። ስለዚህ ለሳምንት ከእኛ ጋር የነበሩትን አገልጋዮች ከቤተ ክርስቲያናቸው አግደዋቸው ነበር። በቅዳሴ ላይ እንዳይሳተፉ ወይም የቅስና ሥራቸውን እንዳያከናውኑ ተከለከሉ። ውጤቱም ከቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ መወገድን አስከተለ። ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ይህን መጥፎ ጎጢአት መናዘዝና ንስሓ መግባት ነበር። ከዚያም በአብያተ ክርስቲያናቸው በድጋሚ ሊጠመቁና ወደ ቀድሞ ቦታቸው ሊመለሱ ይችላሉ። በድጋሚ መጠመቅ በራሱ እንደ መናፍቅ የሚያስቈጥር ቢሆንም እንኳ፣ የአህያ ሥጋ ከመብላት ጋር ሲነጻጸር ትንሽ ነው።

በእኛ ላይ ለመመስከር ፈቃደኛ የሆኑ ብዙ ምስክሮች ነበሩ። አንድ ሰውየ፣ «በፀሓይ ሲና በሚገኘው ቤታቸው አህያ ዐርደው ሥጋውን ወደ መሐል ሜዳ ሲወስዱ አይቻለሁ» ብሎ መሰከረ። ሌላው

ሰውየ ደግሞ፣ «ሬይ አህያ ሲያርድ ፎቶ አንሥቼዋለሁ ሆኖም ፎቶው ገና አልደረሰም» በማለት ተናገረ። ሌላው ምስክር ሳም አህያዎቹን ዐርዶ ጭንቅላታቸውን በግቢው ውስጥ ሲቀብር አይቻለሁ አለ።

ብዙ ሰዎች እርስ በርሱ የሚጋጨው ምስክርነት አላስጨነቃቸውም። ሕጉ እንደ ተጣሰ ለማሳመን የአንድ ሰው ቃል ብቻ በቂ ነበር። ምንም ቢሆን ጢስ ባለበት እሳት አለ። እነዚህን የረከሱ ሰዎች ከተቀደሱት አብያተ ክርስቲያኖቻቸው ማራቅ እንዳለባቸው ተሰማቸው። በስብሰባው ከተካፈሉት ዐሥር አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ውስጥ ዐምስቱ አብያተ ክርስቲያናት በእኛ ስብሰባ ላይ የተሳተፉትን ሰዎች አስወገዷቸው።

ጎረቤቶቻቸውና ጓደኞቻው በጥርጣሬና ባለማመን መንፈስ ይመለከቷቸው ጀመር። ጥቂቶቹ በፀሓይ ሲናና በቀያ መካከል በሚገኘው ዐመድጉያ በሚባለው በግጦሽ ስፍራ ላይ ድብደባና ማስፈራራት ደርሶባቸው ነበር። ከዚህ የተነሣ ለጥንቃቄ ሲሉ ለወራት ያህል በጉዟቸው ሁሉ በቡድን በቡድን እየሆኑ ነበር የሚጓዙት።

ቀላሉን መንገድ በመከተል ጥፋታቸውን አምነው ችግሩን መቅረፍ ይችሉ ነበር። ነገር ግን የአህያ ሥጋ እንዳልመገብናቸው ያውቃሉ። አምነውን ነበርና እንደማናታልላቸው እርግጠኞች ነበሩ። ከእነርሱ ጋር በነበርን ጊዜ የምግብ ሕግጋቶቻቸውን እንዳንጥስ እንዴት እንጠነቀቅ እንደ ነበር አይተዋል። ዐዲሶቹ አማኞች አሁን ያለው ችግር ከአህያው ሥጋ የበለጠ ትልቅ ችግር እንደ ሆነ አስተዋሉ። ችግሩ የተከሠተው በሰይጣን በተከፈተ ውጊያ ሳቢያ ነበርና እነርሱም መሠረታቸውን ሳይለቁ ጸንተው ቆሙ።

ይህ እየሆነ ሳለ ወዲያውኑ ሌላ ችግር መጣ። በየዓመቱ ግንቦት ላይ ልክ በዚህ ጊዜ እያንዳንዱ ግቢ ጥቁር ጠቦትን ለሰይጣን መሥዋዕት ያቀርባል። ይህ ልዩ በግ ቦረንቲቻ በመባል ይታወቃል። ሰዎቹ ይህን መሥዋዕት በመሠዋት ለሰይጣን የሚያቀርቡት፣ በአዝመራቸውና በእንስሳታቸውን እንዲሁም በቤተ ሰቦቻቸው ሕይወት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በመመኘት ነው።

አንዴ የመሥዋዕቱ አቀራረብ ሥርዐት ካለቀ በኋላ ዘና በማለት በዓሉን ያከብራሉ። እስከሚፈልጉት ድረስ ሥጋ ከሚመገቡባቸው ጥቂት ጊዜዎች ውስጥ አንዱ ይህ በዓል በመሆኑ ሁሉም ሰው በጉጉት ነው የሚጠብቀው። ሥርዐቱ ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚፈጸመው ግን እያንዳንዱ የቤተ ሰብ አባል ከተሳተፈ ነው።

በመሐል ሜዳው ስብሰባ ላይ እግዚአብሔር ከገሠጻቸው ጎጢአቶች መካከል አንዱ ለጣያት የሚቀርብን ሥጋ መብላት ነበር። ለእነርሱ ቦረንቲቻ ጣያት ነውና እንደገና የተወለዱ ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ ስለ ተሰማቸው፣ በሥርዐቱ ላይ መካፈል አልፈለጉም። ከስብሰባው አንድ ሳምንት በኋላ የመሥዋዕቱ ጊዜ ደረሰ። ዐዲስ አማኞች እንደ መሆናቸው መጠን ምርጫ እንዲያደርጉ ተገደዱ። ለሚያምኑት ነገር

መቆም ወይም ስምምነት ላይ መድረስ ነበረባቸው። አስቸጋሪ እንደሚሆን ርግጠኞች ቢሆኑም፣ ትክክለኛውን መንገድ መረጡ። ቤተ ሰቦቻቸው ቢደነግጡም በሥርዐቱ ላለመሳተፍ ወሰኑ። ይህ ሰይጣንን ያሳዘናል ድግምቱም አይሠራም። በሥርዐቱ ላይ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ በእያንዳንዶቹ ላይ ከፍተኛ ጫና ተደርጎባቸው ነበር። መሳተፍ ወይም ከቤት መባረር ነበረባቸው። ይሁን እንጂ ወደ ኋላ አልተመለሱም ወይም ጽኑ እምነታቸውን አልተዉም። በቤተ ሰቦቻቸው የተባረሩት የሚቄዩበት ሌላ ቦታ መፈለግ ነበረባቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእያንዳንዳቸው በሚያስፈልጋቸው ሁሉ በቂ እንደ ነበረ አረጋገጠ፤ ከዚህም የተነሣ በእነዚህ መከራዎች ውስጥ እያለፉ በሕይወት መኖር ችለዋል።

ከታላቁ ስብሰባ በኋላ ብዙም ሳይቈይ ተሳታፊዎቹ ወደ እኛ መጥተው መዝሙር እንድናስተምራቸው ጠየቁን። በመሐል ሜዳ የሰሟቸውን መዝሙሮች ወደዋቸው ነበር። በቤተ ክርስቲያኖቻቸው የሚዘምሩት ማሕሌት በመቆም ስለ ሆነ፣ በባህላቸው ያልተለመደ ነገርን ለማስተዋወቅ ስናመነታ ቈይተናል። አሁን እነርሱ ስለ ጠየቁን አስቀድሞ ከሰሟቸው መዝሙሮች ውስጥ አንዱን አስተማርናቸው። የቤተ ክርስቲያኖቻቸው መዝሙሮች ሁሉ በግእዝ ቋንቋ የሚቀርቡ ስለ ነበሩ፣ በየቀኑ በሚጠቀሙበት የአማርኛ ቋንቋ መዘመር ለእነርሱ እንግዳ ነበር። የመዝሙሩን ቃላትና መልእክትም በጣም ወደዱት።

ሁሉም የዲቁና ትምህርት እንዲማሩና በተከታታይም በትምህርታቸው ውስጥ ረጅምና ውስብስብ ማሕሌቶችን ለቅዳሴ በቃላቸው እንዲያጠኑ ይደረግ ነበር። ለብቻ ወይም ከብዙ ሰዎች ጋር አንድ ላይ ይዘምራሉ። ምንም እንኳ የማሕሌት የዜማ ቃና ሁልጊዜ አንድ ዐይነት ቢመስልም፣ እያንዳንዱ ዘማሪ በዜማው ላይ የራሱን ልዩ የዜማ ስልት ይጠቀማል። ስለዚህ የሚዘምሩት ማሕሌት ተመሳሳይ ሆኖ ቢቀርብም፣ በትክክል አንድ ዐይነት ስለማይዘምሩ የጎበረት መዝሙርን አይመስልም።

መዝሙር ሲዘመር የተወሰነ ቅርጽ እንደሌለው ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ሲዘምር በተመሳሳይ ሁኔታ መዘመር እንዳለበት ለማስረዳት ችግር ነበር። እንደ አማራጭ እኔ አንድ ስንኝ ስዘምር ከእኔ በኋላ እነርሱ እየደገሙት አንድ መዝሙር በተደጋጋሚ ተለማመድን። የሚበቃቸውን ያህል ዘምረዋል ብዬ ባቆምሁ ቍጥር ከመካከላቸው አንዱ «እንደገና እንዘምር» ሲል ይሰማል።

በመጀመሪያው ቀን ያንን መዝሙር ዐምሳ ጊዜ እንደ ዘመርነው እርግጠኛ ነኝ። በመጨረሻም በሙዚቃው ስልት ላይና ታች ላይ ቃላቱን አንድ ላይ አሰባስቦ በመዘመር ጥሩ ሥራ ሠሩ። ከዚያም በኋላ መዝሙሩ በትክክል ምን እንደ ሆነ ይታወቅ ጀመር።

ከመሐል ሜዳው ስብሰባ አንድ ሳምንት በኋላ አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ ከቤተ ክርስቲያኖቻቸው የተባረሩት በቡድን ወደ

ቤታችን መጡ። በጣም ተስፋ ቈርጠው ነበር። ለቦረንትቻው የተዘጋጀውን ምግብ አንበላም በማለታቸው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳትሆን ቤተ ሰቦቻቸውም በጥብቅ እየተቃወሟቸው ነበር። ስለዚህ የሐዋርያት ሥራን አንድ ላይ አነበብን። ደቀ መዛሙርቱ በተደጋጋሚ እንዴት ይሠቃዩ እንደ ነበር ከዚያ ክፍል ተመለከቱ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ታማኝ እንደ ነበረና ከአጠገባቸውም እንዳልራቀ የሚያሳይ መሆኑን ተረዱ። እስከ ሌሊቱ ጊዜ ድረስ ጸለይን፤ መጽሐፍ ቅዱስም አጠናን። ከዚያም ብርድ ልብሳቸውን ለብሰው ምንጣፉ ላይ ጋደም አሉ። በቀጣዩ ቀን ወደ ቀያ ተመልሰው ሲሄዱ በጣም ተበረታተው ነበር።

ስለ ኢትዮጵያውያን ጓደኞቻችንና እየገቡበት ስላለው ችግር ስንጨነቅ ሳለ፣ ለእኛም ችግር እየተዘጋጀልን ነበር። በእንቅስቃሴው ያልተደሰቱ ጥቂት ሰዎች ችግር ፈጣሪ መጤዎች ብለው ያሰቡንን እኛን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስወግዱበት መንገድ የተመቻቸ መስሎ ታያቸው።

ጳውሎስም ወጥቶ ሕዝቡ ፊት ለመቅረብ ፈልጎ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ከለከሉት ከአውራጃው ባለ ሥልጣኖች አንዳንድ ወዳጆቹ እንኳ፣ ጳውሎስ ወደ ጨዋታ ማሳያው ሰፍራ ደፍሮ እንዳይገባ ሰው ልከው ለመኑት።

ጉባኤውም ተበጣብጦ አንዱአንድ ነገር ሲናገር ሌላውም ሌላ እየተነጋገረ ይጯጯህ ነበር፤ አብዛኛው ሰው ለምን እዛ እንደተሰበሰበ እንኳ አያውቅም ነበር። አይሁድም አስከንድሮስን በሕዝቡ መካከል ገፍተው ወደ ፊት ባወጡት ጊዜ፣ አንዳንዶቹ እንዲናገርላቸው ጮኹ፤ እርሱም ሊከራከርላቸው ፈልጎ ዝም እንዲሉ በምልክት ጠቀሳቸው። ነገር ግን እርሱ አይሁዳዊ መሆኑን ባወቁ ጊዜ ሁሉም በአንድ ድምጽ «የኤፌሶኗ አርጤምስ ታላቅ ናት» እያሉ ሁለት ሰዓት ያህል ጮኹ።

የሐዋርያት ሥራ 19÷30-34

ክስ

ብዙም ሳይቈይ ማስፈራሪያዎች በእኛ ላይ ይሰነዘሩ ጀመር። በሁኔታው የተጨነቁ ጓደኞቻችን የከናታን መኖሪያ ቤት ለማቃጠል ያቀዱ ጥቂት ሰዎች እንዳሉ ሲያስጠነቅቁን ወደ እኛ መጡ። ሌሎች ደግሞ በመንዝ የሕይወት ማቈያ መሥመራችን የሆነውን የሚሲዮኑን አውሮፕላን ለማውደም አስፈራሩን። የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባላትም የሳም መኪና ወደ አቅራቢያቸው መጥቶ ቢያገኙት በድንጋይ እንደሚከሰክሱት በግልጽ ተናገሩ።

የተሰያዩ ወንጀሎችን እንደ ፈጸምን ተቈጥሮ ተከሰን ነበር። ክሱን የሚያረጋግጥ ምንም ነገር አለመሩ እየተሠራጨ የነበረውን የአሉባልታ ወሬ አቀዘቀዘው። በመጨረሻ ላይ ለፍርድ የሚቀረብበት ቀን እስኪወሰን ድረስ ለሁለት ሳምንት ያህል ጭንቀታችን እያየለ ሄደ። ምንም እንኳ በሕጋዊ መንገድ የተከሰስንበትን ጉዳይ ባያሳውቁንም፣ እንደ ተከላሽ የክስ መዋሪያ ወረቀት ተቀብለን ነበር። የተከሰሱትም በዚያ ጊዜ በመንዝ ይኖሩ የነበሩ ሦስት የሚሲዮን ቤተ ሰቦች ነበሩ።

በቀጣዩ ቀን የከናታ ቤተ ሰቦች ጤና ጣቢያ መጥተው ተገናኙ። ወሬአችንና ሐሳባችን ሁሉ በቅርብ በተከሠቱ ነገሮች ላይ ያተኰረ ነበር። ብዙ ሳይቈይ ስለሚታየው ክስ ስንነጋገር፣ ለጥቂት ሙልፍ ሰዎች ወደ መንዝ ለምን እንደ መጣን የማስረዳቱን ዕድል አናገኝ ዘንድ ተመኘን። ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ እየታገዘ በነገሥታት ፊት ምስክርነት መስጠቱን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እኛም ወደ ፍርድ ቤት ስንሄድ በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር ይጠቀምብን ዘንድ ጸለይን።

ለፍርድ ከመቅረባችን በፊት ለመጨረሻ ስብሰባ ወደ ቀያ ከሰዓት በኋላ ተመልሰን ሄድን። በመንገዱ ላይ በሁለት ቦታ ትልልቅ ድንጋዮች ተደርገው ስላገኘን ዞረን መሄድ ነበረብን፤ ቢሆንም በመጨረሻ ቦታው ላይ ደረስን።

ዐዳዲሶቹ ምእመናን ቤተ ሰቦቻችን በጉዳዩ ላይ ከእኛ ጋር ተወያዩ። እየተጋፈጥነው የነበረው ከባድ ችግር ለእነርሱ በገይል ተሰምታቸው ነበር። በሚችሉት ሁሉ እኛን ለመርዳት ልባቸው በሐዘን ተገፋፋ። ጥቂቶቹ አብረውን ሄደው ለእኛ ሲሉ ከሰዎች ጋር ሊደባደቡ ሐሳብ አቀረቡ። ነገር ግን ያ እርምጃ መወሰድ ያለበት ትክክለኛ እርምጃ አልነበረም። ሰይጣንን በራሱ ስልት ተጠቅመን ማሸነፍ እንደማንችል ተሰማን። የእግዚአብሔር ጦርነት በመሆኑ የውጊያው ስልት ጎላፊ እግዚአብሔር ራሱ ነበር።

በዚያ ቀን ምሽትና በቀጣዩ ቀን ጠዋት ላይ ከሐዋርያት ሥራ አነበብን። ከዚያ ቦታ ለቀን ከመውጣታችን በፊት በድጋሚ አንድ ላይ ጸለይን። በመጨረሻም ድንኳናችንን አፍርሰንና ሁሉንም ነገር በላንድ ሮቨር መኪናችን ላይ ጫንን። ለመሰነባበት እጃችንን ስናውለበልብ የጓደኞቻችን ዐይኖች እንባ አቀረሩ። ይሁን እንጂ ችግሩ ሁሉ በእግዚአብሔር ቍጥጥር ሥር እንዳለና እንደሚያሸንፍም የእርግጠኝነት ስሜት ተሰማን።

ቤታችንን ዐልፈን የካናታንና የቤድሰል ቤተ ሰቦች እየጠበቁን ወደ ሚገኙበት ወደ መሐል ሜዳ ሄድን። በጎብረተ ሰቡ መካከል ተደ ማጭነት ያላቸው ጥቂት ወዳጆቻችን ደኅንነታችን አሳስቧቸው ወደ ፍርድ ቤት እንዳንገባ መከሩን፤ በእነ ካናታ ቤት ሆነን እንድንጠባበቅ ነገሩን። ፍርድ ቤት መቅረብ ችግር እንደሌለው ካረጋገጡም እንደሚያሳውቁን ገለጹልን።

በዚያ ያለው የመንግሥት ትምህርት ቤት ከሰዓት በኋላ ተዘጋ። ከዘጠኝ መቶ ተማሪዎቹ መካከል አብዛኛዎቹ አስቀድሞ ይታወቅ ወዳልነበረው ስብሰባ ጉረፉ። ከተማው በአጠቃላይ ተዘግቶ ወደ ሕዝቡ አዳራሽ ተሰበሰቡ። ውጤቱ ምን እንደሚሆን ብዙ ግምት ነበርና ሁሉም የሚሆነውን ለራሱ ማየት ጓጓ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ እኛ በካናታ ቤት ሆነን እየተጠባበቅን ቈየን። ወዲያውኑ ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ፊት ሐሳባችን ለመግለጽ ወይም ራሳችንን ለመከላከል እንዲት ቃል እንኳ የመናገርን ዕድል እንደማናገኝ ግልጽ እየሆነልን መጣ። ልናደርገው የምንችለው ነገር ቢኖር መጸለይና ሁኔታው በጌታ ቍጥጥር ሥር እንደሚሆን በማመን መጽናት ነበር። በርግጥም በእነዚያ ከሰዓት በኋላ በነበሩት ረጅም ሰዓታት ያደረግነው ይህን ብቻ ነበር።

ፀሐይ መጥለቅ ስትጀምር የሰው ዘር በከተማው ሲንቀሳቀስ ተመለከትን። ከእኛ ጋራ ለመድረስ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የነበሩት የትምህርት ቤት ሕፃናት ናቸው። ስብሰባው እንዴት እንደተካሄደ ጠየቅናቸው። ከእነርሱ ያገኘነው ብቸኛ ምላሽ በግዴለሽነት ትከሻቸውን መነቅነቅና በፍጥነት ዐንገታቸውን ማቀርቀር ነው።

በመቀጠል ጥቂት የካናታ ተማሪዎች መጡ። ስብሰባው መጥፎ እንደ ነበር በመናገር ከበፊቶቹ የበለጠ መረጃ ሰጡን። በኢትዮጵውያን ባህል የመጥፎ ወሬ ተናጋሪ ትልት ሰው ወይም ወሬው ከሚነገረው

ሰው ይበልጥ አስፈላጊ ሰው መሆን አለበት። ይህንን ባህል ደግሞ እኛ እናውቀው ነበር። ስለዚህ እስከ አሁን ድረስ ለማወቅ የጓጓንበት ነገር ለመንገር ከመካከላቸው ብቁ እንደ ሆነ የተሰማው ሰው አልነበረም።

በመጨረሻም የረጅም ጊዜ ወዳጃችን የነበረው ለሕዝብ ልማት ተቀጥሮ የሚያገለግለው ሠራተኛ ጉዳዩን በዝርዝር ነገረን። ከዐምስት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ታቦት በመስረቅ እንደ ተከሰሰን ስንሰማ ምንም አልተደነቅንም። ከመንዝ መልከአ ምድር ወጣ ገባነት የተነሣ እንዲህ ዐይነቱ ጀብዱ ያለ ሄሊኮፕተር እንደማይቻል እንኳ አላሰቡም። በትውስት እንሰጣቸው የነበሩ ካሴቶች በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሐሰት ቅስቀሳዎች እንደ ነበሩባቸው እርግጠኞች ሆነው የመሰከሩብን ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ሌሎች ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን በመቃወም እንሰብክ እንደ ነበር መስክረዋል።

በፍርድ ቤቱ ክስ ሲያቀርቡብን የነበሩት ሰዎች የተወሰኑ ወንዶች ብቻ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በመንግሥት ላይ ወይም በመንዝ ባሉ ዋና ዋና ሰዎች ላይ ቅሬታ የነበረባቸው ናቸው። በእኛ ላይ በሚደርሰው ጉዳት ሳቢያ የሚበቀሉብትን ዕድል ተመለከቱ። ይሁን እንጂ ትክክለኛ ቅሬታቸው ከእኛ ሁኔታ ጋር ፈጽሞ አይገናኝም።

ጥቂት ሰዎች እኛን በመደገፍ ለመመስከር ሞክረው ነበር። ነገር ግን አንድ ሰው ተነሥቶ የድጋፍ ምስክርነት ሲሰጥ ወዲያውኑ ሁሉም ሰው በአንድነት በገይል ይጮኽበታል። አንድ ዳኛ እኛን ደግፎ ሲናገር ወዲያውኑ «ከሚሽኑ ገንዘብ በልተሃል» ተብሎ ተከሰሰ። ምንም እንኳ የተከሰሰበት ጉዳይ እውነትነት ባይኖረውም፣ ምስክርነቱን ዋጋ እንዳይኖረው አድርጎታል። እኛን ለመከላከል የሞከረ አንድ ሌላ ሰው እስኪደክም ድረስ ተደብድቦ ሊያመልጥ ችሏል።

የፍርድ ውሳኔ ላይ እስኪደርሱ ድረስ ለዐምስት ሰዓት ስብሰባው ቀጠሉ። በተደረሰበት ስምምነት መሠረት አንድ የፊርማ ወረቀት ተዘጋጀ። ያ የተዘጋጀ የፊርማ ወረቀት በተቻለ ፍጥነት በመንዝ የሚገኙት ሚሲዮናውያን በሙሉ ለቀው እንዲወጡ ይጠይቃል። በዚያ የነበሩ ሰዎች በሙሉ እንዲፈርሙ ግፊት ተደርጎ ባቸው ነበር።

ለሚደርስ መጥፎ ነገር ሁሉ ራሳችንን ያዘጋጀን ቢሆንም እንኳ፣ ውሳኔው አስደንጋጭ ነበር። ልክ ሰባት ዓመት ስንጸልይበት የነበረው መነቃቃት በመንዝ ምድር እውን ሲሆንና ቋንቋውን በደንብ መልመድ ስንጀምር ነበር ከመንዝ እንድንወጣ የተጠየቅነው። በርግጥም ያ ጊዜ ለቆ ለመሄድ ትክክለኛ ጊዜ አልነበረም።

ትእዛዙን ተቃውመን ተከራከርን። ክርክሩ በሥርዐት የተካሄደ ካለመሆኑ የተነሣ ሕጋዊነቱ የተሟላ አልነበረም። ነገር ግን በጉዳዩ ላይ ከተወያየንበትና ከጸለይንበት በኋላ መታገል እንደ ሌለብን ተሰማን። እግዚአብሔር አሁንም ሁሉንም ነገር በመቈጣጠር ላይ ነበር። ለፍርድ እንድንቀርብ ከተወሰነበት ቀን በፊት እግዚአብሔርን ለሚወዱ ነገር

ሁሉ ለበጎ እንደሚደረግ የሚገልጽ ካሴት አንድ ላይ ሰምተን ነበር። ቃል ኪዳኑን ከልብ ተቀብለነው አምነንበታል። ይህን ለማረጋገጥ ዕድሉ ይህ ነበር።

ችግሩን በአእምሮአችን አውጥተን አውርደን ወደ ቤት ተመለስን። ቤት ስንደርስ መሽቶ የነበረ ቢሆንም እንኳ እንቅልፍ የወሰደን ዘግይቶ ነው። ሕልማችን ብትንትኑ ወጣ። ተመልሶ መምጣት እንደማይፈቀድልን እያሰብን ከመንዝ ለቆ ለመሄድ ዕቅድ አወጣን።

በቀጣዩ ቀን ከሰዓት በኋላ ጥቂት ጓደኞቻችን ሊጎበኙን መጡ። በጣም ተሰፋ ቈርጠው ነበር። ምኞታቸው ልክ እንደ እኛ ምኞት ከስሞ ነበር። በሚቀጥለው ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደን በሥርዐቱ ለመካፈል ስለሚያስፈልገው ጥበብ አስቀድመው ዐሰቡ። ምናልባት መሄዳችን የማያስተማምን ነበር። የሰዎቹ ስሜት ምን መልክ ለኖረው እንደሚችል ለመገመት ርግጠኞች አልነበሩም።

እሑድ ዕለት የጳንጠቆስጤ በዓል ነበር። በቤተ ክርስቲያኑ የነበረው ግርግር ከተለመደው ይበልጣል። ቅዳሴው በማለቅ ላይ ሳለ ነበር እኛ የደረስነው። ምንም ዐይነት ችግር አልነበረም። ዕምሳ የሚሆኑ ቀሳውስትና ዲያቆናት ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መንገዱን አቋርጠው ወደ ሕዝቡ አዳራሽ ከእኛ ጋር ሄዱ። የጥናቱን ገለጻ ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታና በትኵረት ተከታተሉ።

ጥናቱን አስተምረን ከጨረስን በኋላ የመጀመሪያውን የሚሲዮናችንን የመላላክ ኮርስ መጽሐፍ መውሰድ ለሚፈልግ ሀሉ አከፋፈልን። መጽሐፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች ይገኙበታል። ደኅንነት በኢየሱስ እንዴት እንደሚገኝም በጥንቃቄ ያብራራል። አብዛኛው ሰው መጽሐፉን ወሰደ። በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች ለመማር እርዳታ እንደሚስፈልግ በአንዳንዶች ሐሳብ ቀርቦ ነበር።

ከሰዓት በኋላ ለሳምንታዊ ስብሰባችን ወደ ቀያ ሄድን። ምናልባት አንድ ሰው መኪናችንን ወደ ገደል ለመገፍተር ቢያስብ ብለን ከሠራተኞቻችን መካከል አንዱን እንዲጠብቅ ይዘነው ሄድን። ቦታው ላይ ስንደርስ ከሌላው ጊዜ የበለጠ ሰው ይጠብቀን ነበር።

በመጀመሪያ ሁሉም ይነጋገሩ የነበረው ስለ ክሱ ጕዳይ ነው። ነገር ግን ንግግሩ ሙሉ በሙሉ እንዲቆም ካደረግን በኋላ ትኵረታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ላይ ሆነ። ከዚህም የተነሣ ልዩና ያማረ ጥናት ጊዜ ነበረን። ቀጥሎም በሁኔታው ውስጥ የጌታ ፈቃድ ይፈጸም ዘንድ በተለየ መንገድ ልመና የቀረበበትን ጸሎት ጸለይን።

የምንሄድበት ሰዓት ሲደርስ ኰረብታው ድረስ ብዙ ሽኚ ተከተለን። መመለስ የምንችል መሆናችንን ስላላወቅን ለመሰነባበት በጣም ያስቸግር ነበር። በጣም ታማኝ የሆኑ ጥቂት አማኞች ከዚያ ቦታ ፈጥነው ለመሄድ አልፈለጉም። ሌሎቹ ከሄዱ በኋላ ቈየት ብለው ለመጸለይ ወደ ፀሓይ ሲና መሄድ ይችሉ እንደ ሆነ ጠየቁ።

በመኪናችን ተሳፍረው ቤት እስክንደርስ ድረስ፣ «ለእግዚአብሔር የማይቻለው ነገር አለ ወይ?» የሚለውን የአማርኛ መዝሙር በመደጋገም ይዘምሩ ነበር። ቤታችን በደረስን ጊዜ ብዙ ጓደኞቻችን ቤታችን ውስጥ ተቀምጠው ሲጠብቁን አገኘን። እስከ እኩለ ለሊት ድረስ አንድ ላይ ሆነን ጸለይንና በጌታ ቃል ኪዳን ተጽናናን። በመቀጠልም በጠረጴዛችን ዙሪያ ሆነን ዳቦና ሻይ ዐብረን ተሳተፍን። አንድ ላይ ሆነን ስንመገብ ትስስራችን ጠበቀ።

ዐብረን ከተመገብን በኋላ ለጥቂት ሰዓታት ለመተኛት በሶፋው፣ በወንበሮችና በምንጣፉ ላይ ጋደም አሉ። ንጋት ላይ በድጋሚ መጸለይ ጀመርን። ለኛ ዕለት ከሁሉም ቦታ ቀሳውስትና ዲያቆናት መጥተው ከእያንዳንዱ ቡድን ጋር ጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አካሄድን። ከቀያ የመጡት ቀን ላይ ለመጡት በተደጋጋሚ መሰከሩላቸው። እነዚያ ሰዎች በዚያ መገኘታቸውን ቀያዎች ሌላ መዝሙር ከእኛ ጋር ለማጥናት ተጠቀሙበት።

ኀሙስ ቀን ሌላ ሕዝባዊ ስብሰባ ተካሄደ። በዚህ ጊዜ ስብሰባው የተካሄደው በፀሓይ ሲና የሕዝብ አዳራሽ ነበር። ሰዎች በስብሰባው ለመከፋፈል ከተለያዩ አቅጣጫዎች መጡ። አሁንም ስብሰባው እኛን የሚያጠቃልል አልነበረም ነገር ግን ዜናው ጥሩ ስለ ነበር በፍጥነት ወደ እኛ ደረሰ። በስብሰባው ላይ የተለያዩ ሰዎች ሚስዮናወያን በምን በምን ዐይነት መንገዶች እንደ ረዷቸው ሥርዐት ባለው ሁኔታ ተናገሩ። ያስገኘናቸውን ጥቅሞች ሁሉ ከዘረዘሩ በኋላ እኛ ከመምጣታችን በፊት ወደ ነበረው ሕይወታቸው መመለስ ምን ማለት እንደ ሆነ ለማስተዋል በቂ ጊዜ ወሰዱ።

በስብሰባው ላይ እንዳሉ የልማቱ ባለሥልጣንና ጥቂት ሠራተኞች ወደ መንግሥት የበግ ዕርባታ ጣቢያ ሲጓዙ በፀሓይ ሲና በኩል ዐለፉ። በማኅበረ ሰቡ አዳራሽ ውስጥ ብዙ ሰው ተሰብስቦ ሲመለከቱ ሁኔታውን ለማወቅ ቆም አሉ። ስለዚህ በአጋጣሚ በስብሰባው ላይ ተገኙ። ነገር ግን ሕዝቡ እግዚአብሔር እንደ ላካቸው እርግጠኛ ነበሩ።

በውይይቱ ማለቂያ ላይ በዚያው እንድንቈይ የሚጠይቅ የፊርማ ወረቀት ተዘጋጀ። ወረቀቱ ላይ የተፈረመው በሙሉ ድምፅ ተወስ ኖነበር። ከዚህም በተጨማሪ ወደ መሐል ሜዳ፣ ወደ ትምህርት ሚኒስቴርና በኢዲስ አበባ ወደ ሚገኘው ቤተ ክህነት እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ ወደ ንጉሡ የሚሄዱ ተወካዮች ተመረጡ።

ከስብሰባው በኋላ መልካሙን ዜና ሊነግሩን ሁሉም ወደ እኛ መጡ። የእግዚአብሔር ሥራ እንደ ነበር አምነው ነበርና ለማመስገን ፈጠኑ። ነገር ግን የመጀመሪያው ትእዛዝ ስላልተሻረና አሁንም እንዳለ ስለ ሆነ የመሄጃ ሰዓታችን ደርሶ ነበር። ምንም እንኳ ከመንዝ እንድንወጣ ብንገደድም እንኳ፣ እግዚአብሔር መልሶ እንደሚጠራን ጓደኞቻችን ርግጠኞች ነበሩ። የዚህ አንዱ ማረጋገጫ በመሐል ሜዳ

ምስክርነት ከሰጡት ሰዎች መካከል ሦስቱ የተናገሩትን መቀየራቸው ነው።

ከረጅም የስንብት ቃላት ልውውጥ በኋላ ሁሉም ሄደና ምሽቱን መኪናችን ላይ እጅግ ውድ የሆኑ ዕቃዎችንና ጥቂት የድንኳን ዕቃዎችን ስንጭን ቈየን። በማግስቱ መንዝን ለቅቀን ወደ አዲስ አበባ ሄድን።

የቤድሶል ቤተ ሰብ አባላት ከመርሐ ግብሩ አንድ ወር ያህል አስቀድመው የዓመት ፈቃድ ለመውጣት ከኢትዮጵያ ሄዱ። የዐዳሪ ትምህርት ቤቱ ለክረምት ተማሪዎችን እያሰናበተ ነበርና። በሐምሌ ወር ልናከናውን ያቀድነውን ሥራ ትተን ከካናታ ቤተ ሰብ ጋር ወዲያውኑ ዕረፍት ለመውጣት ወሰንን። በመንዝ ነገሮች ወደ የትኛው አቅጣጫ እንደሚሄዱ ለማየት አንድ ወር በቂ ነበር።

ወደ ኬንያ አንድ ላይ በመኪና ሄድን። ጉዞው በጣም የምንፈልገውን የርምጃ ለውጥ አስገኝልን፤ ከልጆቻችን ጋርም ጊዜ እንዲኖረን ዕድል ሰጠን። ነገር ግን ልንደሰት የሚገባንን ያህል አልተደሰትንበትም። ሁልጊዜ በአእምሯችን ውስጥ ይብላላ የነበረው ጥያቄ ወደ መንዝ እንመለስ ይሆን? የሚል ነበር። ከአራት ሳምንት በኋላ በአዲስ አበባ በሚገኘው ሚሲዮን ጠቅላይ መምሪያ ስንደርስ፤ በመጀመሪያ መስማት የፈለግነው ከመንዝ የመጣውን ዜና ነበር። ሰዎች ለእኛ የሚነግሩን አስደሳች ነገር ነበራቸው።

ወደ ኬንያ ከሄድን ከሁለት ሳምንት በኋላ ከመንዝ ዐሥራ ስድስት ተወካዮች ረጅሙን መንገድ በአውቶቡስ ተሳፍረው በመንዝ ወደ ከተማ ደረሱ። እያንዳንዳቸው የተፈረሙባቸው ደብዳቤዎችን ይዘው መጥተው ነበር። ሰዎች የመጡት የሚሰዮን ሥራ ከሠራንበት ቦታ ብቻ ሳይሆን፣ መንዝ ሳለን ካልደረስንባቸው ሌሎች ቦታዎችም ጭምር ነበር። የመጡት ስለ ሥራችን ሰምተው ከእነርሱ ጋርም እንድንሠራ ፈልገው ነው።

ተወካዮች ወደ መንዝ ተመልሰን በመሄድ እንድንሠራ የሚጋብዝ ደብዳቤ ለሚሰዮናችን አቀረቡ። ሚስዮናችን ሥልጣን ላይ ከነበሩ ሰዎች የተቀበለው በሕጋዊ መንገድ የመጣ የመጀመሪያው ሰነድ ነበር። ተወካዮች አዲስ አበባ ሲመጡ የነበሩት ሚስዮናውያን የእኛ ሚስዮን ለመተባበር ያለውን ፈቃደኝነት ገልጸው ሻይ ጋበዟቸው።

ይህንን ሁሉ ከሰማን በኋላ ጊዜ ሳናጠፋ በቀጣዩ ቀን ወደ መንዝ ተጓዝን። ከዚያ በፊት ተሰምቶ በማያውቅ በጋለ ስሜትና ፍላጎት ተቀበሉን። ሰዎች እኛን ለማቀፍና ለመሳም ከየቦታው መጥተው ነበር። ፍቅራቸውን ለመግለጽ በመቶዎች የሚቈጠሩ ዕንቊላሎች አመጡልን። እግዚአብሔር መልሶ ወደዚያ ቦታ ስለአመጣን ደጋግመው ያመሰግኑት ነበር።

ክሳችን በሚታይበት ጊዜ በመጀመሪያ ላይ ወደ መንዝ ያመጣን አቶ ገብረ ሕይወት በእስራኤል አገር ህክምና ላይ ነበር፤ ስለ ሆነም

እስከ ክረምቱ ማለቂያ ድረስ ተመልሶ አልመጣም። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ብዙ ሰዎች እርሱን ስለሚያከብሩትና እኛንም እንዲቀበሉን ስላዘዛቸው የእኛን በዚያ መገኘት በትዕግሥት ይመለከቱት ነበር። ሁልጊዜ በመንዝ ችግር ሲያጋጥመን ነገሮችን የሚያስተካክለው እርሱ ነበር። አሁን ያለ እርሱ ርዳታ መምራት ነበረብን። ለመጀመሪያ ጊዜ እኛ በራሳችን በሠራነው ሥራ ተገመገምን። በመንዝ የነበሩት ሰዎች ያዩትን ነገር ስለ ወደዱት እንመለስ ዘንድ ተወካዮችን ወደ አዲስ አበባ ላኩ።

ከዐምስት ወራት በኋላ አቶ ገብረ ሕይወት በቀድሞው መንግሥት ወዳጅነት ተወንጅሎ ለስምንት ዓመት ወህኒ ቤት ወረደ። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ጥበብ ተመለከትን። የእኛ በመንዝ መገኘት እስከዚያ ድረስ በእርሱ ሥልጣን ቢሆን ኖሮ ምናልባት በዚያ ሰዓት ከአገር እንድንወጣ እንገደድ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ስለማይውቅ፣ በፖለቲካው ለውጥ ሳቢያ የእኛ የሚሰዮን ሥራ ይቀጥል ዘንድ በጥንቃቄ ዐቀደ። በዚያን ጊዜ አደገኛ መስሎ የታየው ክስ በሌላ መንገድ ሊመጣ የማይችል ነገርን አስገኘ።

ጋልዮስ የአካይያ ገዥ በነበረበት ጊዜ አይሁድ ተባብረው በጳውሎስ ላይ ተነሡ፤ ፍርድ ወንበር ፊት አቅርበውትም፣ «ይህ ሰው ሕጉ በማይፈቅደው መንገድ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ እያሳሳታቸው ነው» አሉ።

ጳውሎስ ሊናገር ገና አፉን ሲከፍት፣ ጋልዮስ አይሁድን እንዲህ አላቸው፤ «የአይሁድ ሰዎች ሆይ፤ ያቀረባችሁት ጕዳይ ስለ ዐመፅ ወይም ስለ ከባድ ወንጀል ቢሆን ኖሮ ላዳምጣችሁ በተገባኝ ነበር፤ ነገር ግን ክርክራችሁ ስለ ቃላትና ስለ ስሞች እንዲሁም ስለ ሕጋችሁ በመሆኑ፣ እናንተው ጨርሱት፤ እኔ በእንዲህ ዐይነት ነገር ፈራጅ ለመሆን አልሻም። ስለዚህ ከፍርድ ወንበር ፊት አስወጣቸው።

የሐዋርያት ሥራ 18÷12-16

ብርታት

የቀያ አማኞች እስከዚያ ጊዜ ድረስ በአብያተ ክርስቲያቻቸው መርሐ ግብሮች ከመሳተፍ ታግደው ነበር። እናም የማስፈራሪያ ዒላማ መሆናቸው ቀጠለ። ከዚያም አንድ ቀን ከመሐል ሜዳ ፍርድ ቤት መጥሪያ ደረሳቸው። ከሁለት ዓመት በፊት ከቤተ ክርስቲያናቸው ታቦት ሰርቀው ለሚስዮናውያን ሸጠዋል ተብሎ ክስ ቀርቦባቸዋል። በዚያን ጊዜ እነዚህ ሰዎች እኛን እንደማያውቁን ያስተዋለ እንኳ አልነበረም። በፍርድ ቤት ራሳቸውን እንዲከላከሉ ተወሰነ።

ከቀያ ወደ መሀል ሜዳ ደርሶ መልስ በእግር የአንድ ቀን ጕዞ ከመሆኑም በላይ መንገዱ አስቸጋሪ ነው። ብዙ ገዜ ሰዎች ለደርሶ መልሱ ጕዞ ሁለት ቀን ይመድባሉ። የእኛ ወዳጆች የዕርሻ ሥራቸውን አቋርጠው ወድ ጊዜያቸውን በመሠዋት በተወሰነው ቀን መልስ ለመስጠት መሄድ ነበረባቸው። ቦታው ላይ በደረሱ ጊዜ የከሰሳቸው አልተገኘም። ስለዚህ በድጋሚ እንዲመጡ ሌላ ቀን ቀጠሮ ተሰጣቸው።

ለሁለተኛ ጊዜ ረጅሙን ጕዞ ተጓዙ፤ ሆኖም ይህም ከንቱ ነበር። ክሱ ሁለቱም ወገኖች ካልተገኙ አይሰማምና ከሳሻቸው ድጋሚ ስላልመጣ፣ አሁንም ክሱ ለሌላ ጊዜ ተሳለፈ።

ለሦስተኛ ጊዜ መሄድ ሲጀምሩ የመጨረሻው እንደሚሆን ዐውቀው ነበር። በሕጉ መሠረት አንድ ተከሳሽ ለአንድ ክስ ሦስት ጊዜ ብቻ ነው ሊጠራ የሚችለው። በደረሱ ጊዜ ጕዳዩ በመንዝ ገዥ እንደ ተያዘ ሰሙ። ፍርድ ቤት መጥቶ ጕዳዩን ለማወቅ የቀረበባቸውን ክሶች አነበቡላቸው። የትኛውንም ሕግ በመጣስ እንዳልተከሰሱ ሲመለከት በእንደዚህ ዐይነት ጕዳዮች ላይ ሥልጣን እንደሌለው በመናገር ክሱን በአጠቃላይ ውድቅ አደረገው። በተጨማሪም ክሳቸው ለሦስተኛ ጊዜ ሳይታይ በመቅረቱ ከቀያ የመጡትም በዚህ ጕዳይ ላይ በድጋሚ እንደማይጠሩ ተረጋገጠ።

እንደ ተለመደው የዝናቡ ወቅት በሰኔ ላይ ሲጀምር ሁሉም ወደ ዕርሻ ሥራቸው ተመለሱ። በሬ ጠምደው በሹል ማረሻ ያንን ደረቅና ድንጋያማ መሬት በማረስ ለላምንታት ወገብ የሚቁርጥ ሥራ ይሠራሉ። ዘሩ ብዙ የዕድገት ጊዜ እንዲያገኝ ቶሎ ለመዝራት ይቻኮላሉ። ሐምሌ ወር ላይ የክረምቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከቤታችን አጠገብ በድጋሚ ተከፈተ። ከአዲስ አበባ ሁለት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎች ትምህርቱን እንዲመሩ መጡ። እኛም በተለያዩ መንገዶች እንረዳቸው ነበር። የገጠር ኑሮ ከተማ ላደገ ማንኛውም ሰው በጣም ትልቅ ለውጥ ነው።

እሑድ ቀን በቤተ ክርስቲያን አንደኛው አስተማሪ 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13ን ሰበከ። በቤተ ክርስቲያን በጣም የሚፈለገው ነገር የፍቅር ጕዳይና የሰዎች ወደ ኢየሱስ መምጣት መሆኑን ተናገረ። በመቀጠልም የቤተ ክርቲያንን ሕጎች በሙሉ መፈጸም ያለ ፍቅር ጥቅም እንደ ሌለው አስረዳ። ሁለተኛው አስተማሪ ደግሞ ለመስበክ ሲነሣ የመጀመሪ ው አስተማሪ የተናገረውን በሙሉ ደገመው።

ረጅም መንገድ ተጕዞው የሚመጡት ሳምንት በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ይቈያሉ። ሲመጡ የሚመገቡት ምግብ ይዘው ይመጣሉ፤ የሚተኙበት ቦታ ግን ከዚያው ይሰጣቸዋል። ጥቂት የዐዲስ ምእመናን ቤተ ሰቦች አባሉቻቸው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲማሩ አይፈልጉም ነበር። ስለዚህ እነርሱ ለሳምንት የሚሆነውን ምግብ ይዘው እንዳይመጡ ከለከሏቸው።

ለእነዚያ ተማሪዎች የሚበቃቸውን ምግብ ለማግኘት በጣም ከባድ ቢሆንም፣ አማኝ ጓደኞቻቸው ያላቸውን በማካፈል ታማኝ ነበሩ።

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከሚመጡት መካከል በቀያ ከአብያተ ክርስቲያኖቻቸው የተባረሩ ነበሩበት። ሁልጊዜ ሰኞ ጠዋት ላይ ወደ ፀሓይ ሲና አድካሚ የእግር ጕዞ በማድረግ ዐርብ ከሰዓት በኋላ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ነሐሴ ወር ላይ ከተሰደዱ ሦት ወር ሞላቸው። በሁሉም ነገር ትዕግሥተኛ ለመሆን ይሞክሩ ነበር፤ ወደ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው ለመመለስም ፍላጎት ነበራቸው። ከዚህ የተነሣ ለቤተ ክርስቲያናቸው ጠቃሚ እንደ ሆኑ የሚያ ረጋግጡበት ጥሩ ሐሳብ ወደ አእምሯቸው መጣ፤ ከአዲስ አበባ የመጡትን ሁለት አስተማሪዎች ወደ ቀያ አብረዋቸው ሄደው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያነጋግሩላቸው ዘንድ ጠየቋቸው።

ለክሱ በቀረብንበት ቀን በከባድ ሁኔታ ሲወነጅሉን የነበረው ሰው አንድ ነገር እንድናደርግለት ሊጠይቀን ወደ እኛ መጣ። ባለቤቱ በጣም ታማ ስለ ነበርና ወደ ጤና ጣቢያው መምጣት ስለማትችል፣ መኮ እንዲያያት ሬይ በመኪና ይዞት ይሄድ ዘንድ ፈለገ። በዚያ በዝናባማ ወቅት ያገለግል የነበረው ጭቃ የበዛበት መንገድ ለመሄድ የሚያስችል አልነበረም። በከባድ መኪና፣ በጭቃ ጎማዎችና በሰንሰለቶች እንኳ

የትም ቦታ ለመሄድ በጣም አስቸጋሪ ነበር። በዚያ ሁኔታ የትም ለመጓዝ መሞከር ማለት አደጋን መጋበዝ ማለት ነው።

ነገር ግን ሰውዬው አጥብቆ ለመነ። ዶክተሩ ካልሄደ ምናልባት ባለቤቱ ትሞታለች። ስለዚህ መኮ ሴትዮዋን ያያት ዘንድ ሬይ ሊወስደው ተስማማ። ወደ ሰውየው ቤት ሲሄድ እግረ መንገዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱን አስተማሪዎች ቀያ ሊያደርሳቸው ይችላል። ለሊቱን በቀያ አሳልፈው በቀጣዩ ቀን በዚያ ካሉ ተማሪዎች ጋር በእግር ሊመለሱ ታስቦ ነው እንደዚያ የሚሆነው።

ሬይ መኪናው በጭቃ ሳይቀረቀርበት መኮ ለሴትየዋ በጣም የሚያስፈልጋትን የፔንሲሊን መርፌ ለመስጠት ቻለ። ከዚያ በኋላ ቡና እየጠጡና ዳቦ እየበሉ ሁሉም ለመነጋገር ዕድሉን አገኙ። በጣም ሲቃወመን የነበረው ሰውየ በዚህ ጊዜ ወደ እርሱ አካባቢ መጥተን እንድናስተምር ጉተጉተን።

እሑድ ከሰዓት በኋላ ተስፋ የቁረጡ አስተማሪዎችና ተማሪዎች ወደ ፀሓይ ሲና እየተንተቱ መጡ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ጠዋት ላይ ሄደው ነበር፤ ነገር ግን ገና እግራቸው የቤተ ክርስቲያኑን ቅጥር ግቢ ሳይረግጥ ተባረሩ። ሊያገኟቸው ሮጠው የተከተሏቸው ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በቤተ ክርስቲያናቸው እንዲሰጥ እንደማይፈልጉ በመናገር ጮኹ። መልእክታቸው ግልጽ እንደ ሆነ ለማረጋገጥ አስተማሪዎቹንና ይዘዋቸው የመጡትን በዱላ እየመቱ ሁሉንም አባረሯቸው። ታሪኩን ለእኛ እየነገሩን ላለ አስተማሪዎቹ እንዲህ ዐይነት ባሕርይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖሩን ለማመን አቅቷቸው ነበር። ነገር ግን ማስረጃ በመኖሩ መከራከርና ማስተባበል አልቻሉም።

በቀያ ከአብያተ ክርስቲያኖቻቸው የተባረሩት ተማሪዎች ወደ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው ይመለሱ ዘንድ እንዲረዷቸው የጠየቋቸው የአዲስ አበባ አስተማሪዎች ያያ[illegible] መከራ ከከሸፈ በኋላ፤ የአካባቢውን አስተዳዳሪ ስለ ችግራቸው አዋይተው ይረዳቸው ዘንድ ለመጠየቅ ወሰኑ። ከቀያ ሰባት ወጣት ወንዶች ሊያነጋግሩት ሄዱ። እኛ ራሳችን ወደ መሐል ሜዳ እንሄድ ስለ ነበር ይዘናቸው ሄድን። ከእኛ ላንድ ሮቨር መኪና ከወረዱ በኋላ ወደ አስተዳዳሪው ቢሮ አመሩ። በእኛ ክስ ላይ በግልጽ ይቃወም የነበረውን ሰውየ ሲያገኙት ከእርሱ አጠገብ ብዙም አልራቁም ነበር። በማስፈራራት ወደ አስተዳዳሪው ቢሄዱም በቤታቸው በሰላም እንዳይኖሩ እንደሚያደርጋቸው ነገራቸው። ዐመድጉያ ላይ እንደሚጠብቃቸውም በግልጽ ዛተባቸው። ያንን ዘር የማይዘራበትና ፍሬ የማያፈራ ትልቅ የግጦሽ መሬት ሳያቋርጡ ደግሞ ወዴትም መሄድ አይችሉም።

ምንም እንኳ የአስተዳዳሪውን ሥልጣን ላለመድፈር ቢፈሩም ለማነጋገር ቁርጠው ተነሡ። እዚያው ቆመው እያናገሩት ሳለ አስፈራር ቶአቸው የነበረው ሰውየ ተይዞ ወደ እስር ቤት ተወረወረ። አስቀድሞ የተናገረውን የእስር ቤቱ ጠባቂ ሰምቶት ስለ ነበረ ተናገረበት።

በተጨማሪም ሁለት ሌሎች ሰዎች በእርሱ ላይ ሊመሰክሩበት ፈቃደኛ ሆኑ። እርሱ እስር ቤት ገብቶ ሲቆለፍበት የተገላቢጦሽ ሆኖ ታየ።

ከቀያ የመጡት ተማሪዎች በቀጣዩ ቀን ፈተና ስለ ነበረባቸው አስተዳዳሪውን እንዳነጋገሩ ፀሓይ ሲና ወደሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመመለስ ዐቅደው ነበር። ነገር ግን የሰውየውን መታሰር ሕጋዊ ለማድረግ ክስ መመሥረት ነበረባቸው። አስተዳዳሪው ቂይተው በቀጣዩ ቀን ጠዋት ላይ ይህን ጉዳይ ይፈጽሙት ዘንድ ነገራቸው።

ጉዳዩ ጊዜ እንደሚወስድ ያውቁ ስለ ነበር በፍርድ ቤት ጉዳይ ወስጥ መግባት አልፈለጉም። ነገር ግን አስተዳዳሪው ሊረዳቸው እየሞከረ ስለ ነበር፣ ምክሩን ተቀበለው መፈጸም ነበረባቸው። መሐል ሜዳ ቂይተው በማግስቱ የፍርድ ቤቱ ቢሮዎች እስኪከፍቱ ድረስ በር ላይ ይጠባበቁ ነበር። ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሰነዶችን በቅጡ አይቶ ለመፈረምና መሐላ ለመፈጸም ቀኑን ሙሉ ዋሉ። አንዳንድ ጊዜ የተከሰሱት እነርሱ ራሳቸው የሆኑ ይመስላቸው ነበር።

በመጨረሻ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት እንዳይሄድ ተወሰነ። ያስፈራራቸው ሰውየ ድጋሚ እንደማያስፈራራቸውና ወደ ቤተ ክርስቲያንም ከመሄድ እንደማይከለክላቸው በሚያረጋግጥ ሰነድ ላይ ፈረመ። ሰውየው ቃሉን ካጠፈ ፖሊስ መልሶ ወደ ወህኒ ቤት ሊያስገባው መብት ነበረው።

ይህ ሁሉ ከተደረገ በኋላ ሰዎቹ ወደ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው በሕጋዊ መንገድ መመለስ እንደሚችሉ አስተዳዳሪው ወሰነ። በጦርነቱ በዚህ መንገድ ያሸነፉ መሰሉ። በቀጣዩ ቀን ወደየመሪያቸው ሲመለሱ የዚህ ጉዳይ ወሬ ለአነርሱ ቀድሞ እንደ ደረሰ ታወቀ። ለዚህ ምላሽ ሰዎቹ ስልታቸውን በመቀየር ዐዲስ የተቃውሞ ዕቅድ ነድፈው ነበር።

ቀደም ሲል የአህያ ሥጋ በልታችኋል ተብለው ከተከሰሱት መካከል አንድም ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመምጣት ቢሞክር፣ ግልጽ ተቃውሞ እንዲደረግበትና ሰውም እንዳይቀርበው ተወሰነ። በርግጥ ምንም የተለወጠ ነገር አልነበረም። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ምእመናኑ ከልዩ ልዩ ተጽዕ የተነሣ ስደተኞች ነበሩ። አንድ ሰውጥ ግን ይታይ ነበር፤ ይኸውም ብዙ የሚያበረታቷቸው ጓደኞች የነበሩ መሆናቸው ነው።

በዚያን ዓመት የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምርቃት ከተለመደው ትንሽ ለየት ያለ ነበር። መርሐ ግብሩ በቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ አልተጀመረም ምክንያቱም ቀሳውስቱ ደሞዛቸው ስላልተከፈላቸው ዐድማ ላይ ነበሩ። በዚያ ፈንታ ሬይ እንዲሰብክ ተጠየቀ። ፈተናውን ላለፉትና በሰዓት በመገኘት ታማኝ ለነበሩት ሠልጣኞችም የመጽሐፍ ቅዱስ ሽልማት ተሰጠ።

ቄስ ግርማ አንድ አስገራሚ ዜና ሊነግረን ወደ እኛ ሲመጣ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እየተገባደደ ነበር። በመንዝ የሚገኘው ቤተ ክህነት ለቀያና ለአካባቢው ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር እንዲሆን ቄስ ግርማን መረጠው። እንዴት ያለ አስደናቂ ዕድል ነው! ነገር ግን ከዚህ ሹመቱ ጋር የተያያዘ አንድ ሌላ ነገር ነበረ። የቄስ ግርማ እድገት ለአንድ ዓመት በአዲስ አበባ የቅስና ትምህርት ቤት መግባትን ይጠይቅ ነበር። ዐዲሱ ትምህርት በቀጣዩ ሳምንት እንዲጀምር ስለ ታቀደ ውሳኔውን በፍጥነት ማሳወቅ ነበረበት።

የእርሱ መንዝን ለቆ የመሄድ ሐሳብ ለእኛ አስደንጋጭ ነበር። የዐዲሶቹ አማኞች ዋና መሪ ነበርና። ቄስ ግርማ ከመለወጡ በፊት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያገለግሉ ለነበሩ ወጣት ወንድ ዲያቆናት የጥንቅላናን ትምህርት ያስተምር ነበር። ከጊዜ በኋላ እነዚያ ዲያቆናት በክርስቶስ ስላመኑ፣ ለምክርና በእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት ለማደግ የሚመጡት ወደ እርሱ ነበር። ለመመስከር ብዙ ዕድሎችን አግኝቶአል። ያለ እርሱ ነገሮችን ለመከወን እንደሚያስቸግረን ርግጠኞች ነበርን።

በተጨማሪም ባለቤቱንና ሁለት ወንድ ልጆቹን ለረዥም ጊዜ ትቶ መሄዱ በጣም ቢያሳስበውም፣ በአካባቢው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ለመሆንና ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው። በመጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ነገሩ እንዴት እንደ ሆነ ለማየትና ከዚያም እንደ ሁኔታው ሐሳቡን ሊለውጥ እንደሚችል ዐሰበ።

ቄስ ግርማ አዲስ አበባ ከደረሰና ጠቅላላ ሁኔታውን ካስተዋለ በኋላ በዚያው ለመቈየት ወሰነ። በየወሩ ዐዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ልጆቻችንን ለመጠየቅና ዕቃ ለመግዛት ወደ አዲስ አበባ ስንሄድ፣ ቄስ ግርማን እንጐበኘው ነበር። በእነዚያ ዐጫጭር የጉብኝት ጊዜያት ብዙ የምንወያይበት ነገር ነበር፤ በመንዝ ስላለው ስለ ቤተ ሰቡም ሆነ ስለ አማኝ ጓደኞቹ ዜና የመስማት ከፍተኛ ጕጕት ነበረበት። በሁሉም ነገር የብቸኝነት ስሜት ዐድሮበታል። ሁልጊዜ የምናደርገው ጸሎትና ውይይት ሦስታችንንም አበረታታን።

በአዲስ አበባ የቅስና ትምህርት ቤት ያሉ ሌሎች ሰዎች የእኛን ጕብኝት በቅርብ መከታተል ጀመሩ። ቄስ ግርማ በአብዛኛው በየቀኑ የሚማረው ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ታሪክና በኦርቶዶክስ ባህል ላይ ያተኰረ ነበር። ወዲያውኑ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሰብክ የሚሰማበትን ቦታ ሲያፈላልግ እርሱ ካለበት ብዙም የማይርቅ አንድ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን አገኘ። በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥሩ የሰንበት ትምህርትና ስብከት ስለሚሰጥ፣ በሥርዐተ ቅዳሴው ቀደም ብሎ በጠዋት በመሳተፍ በዚያ ቤተ ክርስቲያን የሚቀርበውን ስብከት ለማድመጥ በሰዓቱ መድረስ ይችል ነበር።

በተጨማሪም ከካህናት ማሠልጠኛው ትምህርት ቤት ቀጥሎ የአንድ ወታደራዊ ማሠልጣኛ ጠቅላይ መምሪያ ስለሚገኝ፣ ጥቂት ወታደሮችን ከዚያ ተቋም አግኝቶ ኀደኛ አደረጋቸው። ከኦርቶዶክስ እምነት አንጻርም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎችን ያቀርቡለት ጀመር። እነርሱን ለማነጋገር ባገኘው ዕድል ቄስ ግርማ ደስተኛ ነበር። ወዲውኑ ያገኛቸውና በየጊዜው የሚመሰክርላቸው ሰዎች ናቸውና። ወታደሮቹ በየትኛውም ሰዓት ላይ ለጦርነት እንደሚጠሩ ስለሚያውቁ በሕይወት ውስጥ ስለሚያጋጥማቸው ጕዳዮች ሁሉ ያስቡ ነበር።

በዚያ ዓመት በልግ ላይ በቤታችን አቅራቢያ በፀሐይ ሲና በሚገኘው የማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንድንጀምር ጥያቄ ቀረበልን። ከሌላ ቦታ ይበልጥ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅዳሴ አስቀድሰናል። ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን በሄድን ቊጥር ሬይ እንዲሰብክ ይጠየቅ ነበር። እሑድ እሑድ እንድናስተምር የቤተ ክርስቲያኑ ሰዎች ፈቅደው ይጋብዙን ዘንድ ለዓመት ያህል ጸልየናል። እሑድ ቀን ዋናው ቄስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ማወቅ እንዳለባቸውና ልናስተምራቸው የምንችለውም እኛ እንደ ሆንን በዚያ ቀን በቤተ ክርስቲያን ለተገኙት ሁሉ ማስታወቂያ ተደረገ። ከመጀመሪያው ጊዜ አንሥቶ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነበርና በተገናኘን ቊጥር ብዙ ሰው መጥቶአል።

ከዚህኛው ጥናት በተጨማሪም እሑድ ከሰዓት በኋላ ከቡድኑ ጋር በሽመናው ክፍል ለመገናኘት ወደ ቀያ እንሄዳለን። በዝርጉ ምንጣፍ ላይ የሚያገኙት ትርፍ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ የሚያደርጋቸው አልነበረም። ስለዚህ እነዚህን ተማሪዎች አስቀድሞ ውጤት ተገኝቶበት በነበረው ወፍራም ምንጣፍ በድጋሚ ማሠልጠን ጀመርን። ከፀሐይ ሲና በጣም ጕበዝ የነበረው የሽመና አስተማሪ እንዲያስተምራቸው ወደ ቀያ መጣ። እኛም ከሳምንት ውስጥ በተወሰኑ ቀናት ወደዚያ እየሄድን አብረነው እንሠራለን።

በእኛ አቅራቢያ ይኖር የነበረ አንድ የመንግሥት ትምህርት ቤት አስተማሪ ረቡዕ ረቡዕ ምሽት ላይ በግቢው ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንድናካሒድ ጋበዘን። በየሳምንቱ ክፍሉ ውስጥ ብዙ አስተማሪ ዎችና ተማሪዎች ይሰበሰባሉ። ከአመት በፊት መጽሐፍ ቅዱስን ለማስተማር እንመኘው ከነበረ ዕድል ሁሉ የበለጠና የሰፋ ዕድልን ማግኘት ቻልን።

በቀያ የሽመና ሥራ ማስተማር ስንጀምር በየቀኑ እንሰጠው የነበረው ትምህርት በእጅ ሥራና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ አተኰረ። ከዚያ በኋላ ሞልቶትን በቋንቋ አስተማሪነት ስላልፈለግነው፣ ጀሪ ቤድሶል በእንስሳት ህክምና ሥራ ላይ እንዲረዳው እያሠለጠነው ነበር። ዋልቶት በዐዲሱ ሥራው ላይ እያለም እንኳ በየሄደበት ሁሉ በማስተማርና በመስበክ ሥራ በዝቶበት ታይቷል።

ሁሉም አማኞች ማድረግ ከሚወዷቸው ነገሮች መካከል አንዱ መዘመር ነበር። ከጅመሩ እነርሱን ስናስተምር እኛም

የአማርኛ መዝሙሮችን አብረናቸው ተማርን። ምእመናኑ በጣም የሚወዷቸውና በቀላሉ የሚለምዷቸው መዝሙሮች በኢትዮጵያ የተጻፉ የአካባቢው ተወላጆች መዝሙሮች ናቸው። የኢትዮጵያ ሙዚቃ ለምዕራባውያን ዝቅተኛ ድምፅን የሚፈጥር በምሥራቃዊው ዐምስት የመዚቃ ኖታ መጠን የተቃኘ ሙዚቃ ነው።

በአዲስ አበባ ከግእዝ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ የተተረጐሙ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መዝሙሮች የተጻፉበት መጽሐፍ አገኘን። በአዲስ አበባ በሚገኘው በኦርቶዶክስ ሚሲዮን ሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ከሚዘምር ዘማሪ ጋር ተዋወቅን። እርሱ መዝሙሩን በካሴት እንድናደምጥ ጋበዘን። ከመጽሐፉ ውስጥ ብዙዎቹን መዝሙሮች ቀድቷቸው ነበርና ለመንዝ ምእመናን የምናስተምረው ካሴቱን ከመጽሐፉ ጋር እያያዝን ነው። በመጨረሻም ከስድስት ወራት በኋላ ታኅሣሥ ላይ በመሐል ሜዳው ስብሰባ ላይ ተካፍለው የነበሩት ዲያቆናት ወደ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው። የጊዜው ማለፍ ሌላ ሁኔታ ማስገኘት የማይችለውን ነገር አስገኘ፤ ለረጅም ወራት በዚያ ሁኔታ መጠበቃቸውም መልካም ውጤትን አስገኝቶላቸዋል። በዚያ ጊዜ ውስጥ ጥብቅ ትስስር ያለበት የምእመናን ኅብረት ወደ መሆን አድገው ነበር። በየሳምንቱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይገናኛሉ፤ በስብሰባዎቹ ወቅትም የመዝመር ካሴቶችን ያዳምጣሉ። የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ ዕውቀትን መጨበጥ ጀመሩ። መዝሙር መዘመር ተምረዋል፤ ከዚያም በኋላ የመዝሙራትን ሁሉ ዐይነት መዘመር ቻሉ። ብዙ ጊዜ ለጸሎት ይገኛሉ፤ ለእግዚአብሔር ሥራም ምስክሮች ሆኑ።

በመጨረሻ ላይ በአብያተ ክርስቲያኖቻቸው አገልግሎታቸውን ሲቀጥሉ ለመስበክና ለመመስከር ዝግጁ ሆነው ተገኙ። ብዙ ጊዜ እንደሚታየው ስደት እሳቱን በማጥፋት ፈንታ ነበልባሉን የበለጠ አጋግሎታል። እሳቱ በቀላሉ በማይጠፋበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር።

አንድ ቀን ወደ ጸሎት ስፍራ ስንሄድ፣ በጥንቁላ መንፈስ ትንቢት የምትናገር አንዲት የቤት አገልጋይ አገኘችን፤ አርሷም በዚህ የጥንቁላ ሥራዋ ለአሳዳሪ ዎችዋ ብዙ ገንዘብ ታስገኝላቸው ነበር። ይሽቸው አገልጋይ ጳውሎስንና እኛን አየተከተለች፣ «እነዚህ ሰዎች የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ፣ የልዑል እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው!» በማለት ትጮኽ ነበር፤ ይህንም ብዙ ቀን ደጋገመችው፤ ጳውሎስ ግን በዚህ እጅግ በመታወክ ዞር ብሎ ያንን መንፈስ፣ ከእርሷ እንድትወጣ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዣለሁ!» አለው፤ መንፈሱም በዚያው ቅጽበት ወጣላት።

የሐዋርያት ሥራ 16÷16-18

ጠላት

በመንዝ ለስድስት ዓመት ያህል ከቄየን በኋላ ያወቅነው የመጀመሪያው ጠንቋይ ቄስ ግርማ ነበር። ነገር ግን አንድ ጊዜ ሰይጣን በጠንቋዮቹ ተጠቅሞ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ካወቅን በኋላ ተጽዕኖውን የበለጠ የምናረጋግጥበትን ሁኔታ እንመለከት ጀመር።

ወደ መሐል ሜዳው ስብሰባው መጥቶ የነበረ አንድ ሰውየ በግልጽ ጠንቋይ እንደ ሆነ አመነ። ቄስ ግርማና ሌሎች ሰዎች የቀድሞ ልምዳቸውን ማለት ጥንቁላን እያወገዙ ሲመሰክሩ ሰምቶ እርሱም ወደ ተመሰሳሳይ ተግባር አመራ። በመጀመሪያ በዚያ ለተሰበሰቡት ሁሉ የሰይጣን ባሪያ እንደ ነበር ተናገረ። ይህንም የጀመረው ከዐምስት ዓመት በፊት በርኩስ መንፈስ ሲያዝ ነበር። በዚያ ጊዜ ስሙን የነበረበትን ሁኔታ ወደ ሚያንጸባርቅ ሌላ ስም ለወጠ። ርኩስ መንፈስ በውሃ ውስጥ እንደማኖር ስለሚታመን ባሕሬ የሚለውን ስም መረጠ። ይህ ሰው ጠንቋይ በነበረባቸው ዓመታት ውስጥ ለብዙ ጊዜያት ለሰይጣን በሚቀርቡ መሥዋዕቶች ላይ ተሳታፊ ነበር። ሰይጣንን ለማስደሰት በዐንገቱ ላይ ጨሌ አድርጎአል። ብዙ ዐይነት ጨሌዎች እንዳሉ ቢታወቅም፣ የእርሱ ጨሌ ግን ውስጡ የብራና ቁራጭ ያለበት ትንሽ የቁዳ ቦርሳ ነበር። የተጠቀለለው ብራና ርዝመቱ የእርሱን ቍመት ያህላል። በላዩ ላይ ቁጥሮችና ጽሑፍ በከፍተኛ ጥንቃቄ ተቀርጾበት ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ሁሉም ይህን ጨሌ ዐንገቱ ላይ ሲመለከቱ፣ ሰውየውን ሰይጣን እንደሚቈጣጠረው ዐወቁ።

ወደ እርሱ ለሚመጡት ሰዎች የጥንቁላ ሥራን ለመሥራት የሚጠቀምባቸው ብዙ መጻሕፍትና ክታቦች ነበሩት። ስብሰባው እየቀጠለ ሲሄድ እርሱ የሌለውን ነጻነት በስብሰባው ተሳታፊ ሌሎች ሰዎች ላይ መመልከት ጀመረ። ያንን ነጻነት ደግሞ መጋራት ስለ ፈለገ እንድንጸልይለት ጠየቀን።

ክርስቶስ ወደ ልቡ እንዲገባ ምን ማድረግ እንዳለበት ጥያቄ አቀረበ። መጀመሪያ ላይ በጥንቆላ ለሠራው ኀጢአት ንስሐ መግባትና

ያንኑ ተግባር እርግፍ አድርጎ መተው እንዳለበት ነገርነው። ያ ማለት ደግሞ ክታቦቹንና የጥንቁላ መጻሕፍቱን ማስወገድና እምነቱን ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ማድረግ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ዲያብሎስ እንዴት በክርስቶስ እንደ ተሸነፈ አሳየነው፤ በእርሱ ሕይወትም ኢየሱስ ይህንኑ እንደሚያደርግ አስረዳነው።

ይህን ሐሳብ እያዘነ ተቀበለው። ቀላል ርምጃ አልነበረም። ጨሌውን ከዐንገቱ ላይ አውልቆ ለእኛ ሰጠን። ቀጥሎም አንድንጸልይለት ጠየቀ ነገር ግን በዚያን ቀን ራሱን አሳልፎ ለጌታ ለመስጠት ብርታትን አላገኘም ነበር። ትንሽ ሊያስብበት እንደሚፈልግ ተናገረ። ስብሰባው ካለቀ በኋላ ወደ ሳም ካናታ ቤት ደጋግሞ በመሄድ ያነጋግረው ነበር። ይሁን እንጂ ከዚያም በኋላ ቢሆን ጀርባውን ለሰይጣን ሰጥቶ በክርስቶስ ለማመን አልቻለም።

በየዓመቱ ልጆቻችን ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ ይሄዳሉ። ዐምስታችንም እነርሱ ወደ ቤት ሲመጡ የዕረፍት ጊዜያችንን ለማሳለፍና ትምህርት ቤት ሲሆኑ ደግሞ ወደ ከተማ እየሄድን እነርሱን ለመጐብኘት እንጓጓለን። ምንም እንኳ በመንዝ የነበርነው ሚሲዮናውያን እኛ ብቻ በመሆናችን ትንሽ ቢከብድም፣ ቀላሉ መንገድ በአውሮፕላን መጓዝ ነበር። ነገር ግን ወደ አየር ማረፊያ የሚወስደን ሰው አልነበረም።

በምስጋና ቀን በዓሉን ከልጆቻችንና ከሚሲዮናውያን ቤተ ሰብ ጋር ለማሳለፍ ወደ ከተማ ለመሄድ ጠዋት ላይ የጉዞ ፕሮግራም አስያዝን። የፀሐይ ሲናው አየር ማረፊያ ማኰብኰቢያው ላይ የአደገውን ዐረም ቁልል ለማስወገድ ተጀምሮ በነበረው ሥራ ምክንያት ለጊዜው ተዘግቶ ስለ ነበር፣ ወደ መሐል ሜዳ የአንድ ሰዓቱን ረጅም ጉዞ ማድረግ ነበረብን። ሻንጣችንን ይዤ ከአየር ማረፊያው አጠገብ ሬይ አደረሰኝና መኪናችንን ከሁለት ማይል በኋላ ወደሚገኘው ወደ ሳም ካናታ ግቢ ወሰደን። አውሮፕላኑ እስኪመጣ እዚያ ሆነን ለመጠበቅ ሬይ በእግሩ ቶሎ መጣ።

አውሮፕላኑ የሚመጣበት ሰዓት ዐለፈ። ሰዓቱ ቢያልፍም ቁይቶም እንኳ አልመጣም። በጣም ጠበቅን። ከሚመጣበት ጊዜ አንድ ሰዓት ዐልፎ ነበር። ወደ ሳም ካናታ ቤት ሄደን በዐጭር ሞገድ ሬዲዮ ላይ ስለ ሁኔታው ከኤም ኤ ኤፍ ልናረጋግጥ አልደፈርንም። ምክንያቱም እኛ በሄድንበት ጊዜ አውሮፕላኑ ቢመጣ ጥሎን ይሔድ እንደ ነበር ሥጋት ዐድሮብናል። የአውሮፕላኖቹ የበረራ ፕሮግራም ሁልጊዜ የተጨናነቀ በመሆኑ አውሮፕላን አብራሪዎቹ በየትም ቦታ አላስፈላጊ መዘግየት እንዲያጋጥማቸው አይደረግም። ስለዚህ መጠበቃችንን ቀጠልን።

በመጨረሻም በደቡባዊው ሰማይ ላይ የምናውቀውን የተለመደ ነጥብ ተመለከትን። ነጥቡ እያደገ ሲመጣ የሞተሩ ድምፅ ተሰማን። አብራሪው ከማረፉ በፊት ሁሉ ነገር ትክክል እንደ ሆነ ለማረጋገጥ የማረፊያ ቦታውን ዞረው። ትክክለኛነቱን ካረጋገጠ በኋላም

አውሮፕላኑን አሳረፈው። ሰዓት ስለ አሳለፈ ጊዜውን በወሬ ሳያጠፋ እኛንና ዕቃችንን በፍጥነት ጫነን። አብራሪው መንገድ ላይ ያረፈደበትን ምክንያት እንደማይስረዳን ቃል ገባልን። ለመዘግት ያበቃቸው ጉዳይ በጣም ለየት ያለ ታሪክ እንደ ሆነ ነገረን። እርሱ ራሱ እንኳ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ለማመን አቅቶት ነበር። ወዲያውኑ አየር ላይ መብረር ስንጀምር ታሪኩን መናገር መጀረ።

በዚያን ቀን ጠዋት ላይ በአዲስ አበባው ዋና አየር ማረፊያ ላይ ሲንደረደር የነበረ አንድ ተጓዥ ብቻ ነበር። ከመንዝ የሄደ የዐሥራ ሁለት ዓመት የሥጋ ደዌ በሽተኛ ነው። ሕመሙ ለየት ያለ ስለ ነበር ለልዩ ሕክምና ወደ አዲስ አበባው የሥጋ ደዌ ሆስፒታል የላከው ሳም ነበር። ስሜት የማይሰማውን እግሩን ከጉዳት ለመጠበቅ ልዩ ጫማ አድርጎአል። ከእዚህ የተነሣ የሚራመደው በብዙ ችግርና በመከራ ነበር። ልጁ በበሽታው ምክንያት ደካማ፣ ከዕድሜውም አንጻር ትንሽ ነበር።

አብራሪው ከቦሌው አየር ማረፊያ ለመነሣት ከተንደረደረ በኋላ ልጁ ወደ መጸዳጃ ቤት መሄድ እንደሚፈልግ ምልክት አሳየው። አውሮፕላን አብራሪውም ለልጁ መፍቀድ እንዳለበት ጥቂት ካሰበ በኋላ አውሮፕላኑን ድንጋይ የተነጠፈበት መንገድ ጫፍ ላይ አቆመው። የአውሮፕላኑ በር እንደ ተከፈተ ልጁ በፍጥነት አፈተለከ። ዘሎ ወጣና በአየር ማረፊው ላይ ሩጫውን ቀጠለ። አየር ማረፊው ከኢትዮጵያ አየር ማረፊያዎች ሁሉ ትልቁ ስለ ነበር ብዙ አውሮፕላኖች ነበሩበት። አብራሪያዎችን ችግሩን ለመቈጣጠሪያ ማማው ሠራተኛ ተናገረና ልጁን ተከትሎ መሮጥ ጀመረ። እርሱ ከልጁ ስለሚተልቅና አካላዊ ሁኔታውን በማገናዘብ ጥቂት ደቂቃዎች እንደሚወስድበት ዐስቦ ነበር።

ነገር ግን ልጁን መያዝ አልቻለም። በመቈጣጠሪያ ማማው ላይ ያሉ ሰዎች ችግሩን ሲመለከቱ፣ የአየር ማረፊያውን እሳት አደጋ ክፍል አሰማራ። የክፍሉንም ሠራተኞች በሙሉ ከኋላው ላከ። አውሮፕላን አብራሪውና እሳት አደጋ ሠራተኞቹ በሙሉ ሊያዝ ያልቻለውን ልጅ ለመያዝ ጥረት አደረጉ። ሲመለከቱት የገዛ ዐይናቸውን ማመን አልቻሉም። አየር ማረፊያው ላይ እንዳለ እንዳይዙት ልጁ በቀላሉ ወደ ፊትና ወደ ኋላ እንደ ሜዳ ፍየል ይሮጥ ነበር። አየር ማረፊያው የዘወትር ሥራውን እንዲቀጥል ልጁን ለመያዝ ከአንድ ሰዓት በላይ ነበር የፈጀው።

ለደኅንነት ሲባል ልጁ ወደ እሳት አደጋ ክፍል ተወሰደ። አብራሪውም በፕሮግራሙ መሠረት ልጁን ሳይዝ ወደ መንዝ ሄደ። ታሪኩን እየነገረን ሳለ እግሩ የተንሻፈፈው አካል ጉዳተኛ ልጅ ሮጦ ስለ ቀደመው በጣም ይገረም ነበር።

አየር ማረፊያው ላይ ስንደርስ ልጁን ወደ ሥጋ ደዌ ሆስፒታል ይዘን መመለስ ነበረብን። ወደ መንዝ የሚወስደውን ሰው ለማግኘት ሌላ ቀን መጠበቅ ነበረበት። ሬይ ወደ እሳት አደጋው ክፍል በእግሩ

ሲሄድ እኔ መኪናውን ለማምጣት ሄደሁ። መንገድ ላይ በደስታ ሐሳብ ለሐሳብ ሲለዋወጡ አገኘኋቸው። መኪናውን እኔ አሽከረክር ስለ ነበር፣ ሬይ ልጁን ይዞ በኋለኛው ወንበር ላይ ተቀመጠ። በሆስፒታሉ አጠገብ ወደሚገኘው የሚስዮን ግቢ እየተጓዝን ሳለ በመንዝ ስለሚታወቁ ልዩ ልዩ ነገሮች አወራን። ይህን ሲያጫውተን ደስተኛና የተረጋጋ ሰው መሰለ።

ከሚስዮኑ አንድ ማይል ርቀት ላይ ትንሽ ወንዝ ተሻገርን። ወዲውኑ ተሰዋወጠና መጮኽ ጀመረ። መኪና ውስጥ እየተንፈራገጠና እያለቀሰ ርዳታ እንዲደረግለት ይጠይቅ ጀመር። ወደ ሚስዮኑ ግቢ ደርሰን ስለ ነበር፣ ሬይ መኪናውን መንዳት እንድቀጥል ነገረኝ። ልጁ በጎይለኛ ስሜት ውስጥ እንዳለ በመኪናው በር አጁ በጣም በመመታቱ ተሰበረ። መኪናው ውስጥ እንዳይዘልና የበለጠ ራሱን እንዳይጐዳ ሬይ ማድረግ የሚችለውን ሁሉ አደረገ።

መንገድ ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ በሚጮኸው ልጅ ላይ አፈጠጡ። በሚስዮኑ ግቢ ውስጥ ስንገባ በዚያ ምን እየተካሄደ እንደ ሆነ ለማየት ብዙ ሰዎች ተከተሉን አንድ ሰውየ ልጁን እንደሚገባ ስላልያዝን ፍርድ ቤት ከሰሶ ሊያቀርበን መጣ።

ልጁን ወደ ሆስፒታል ወስደነው እጁ በጆሶ ታሸገለት። ከዚያም ከሁለት ቀን በኋላ ወደ መንዝ ተመለስን። በዚያን ጊዜ ግን ካናታና ባለቤቱ አብረውን ነበሩ። በጉዞው ላይ የሕመም ስሜት እንዳይሰማውና እንዲረጋጋ ሳም ሁለት ዐይነት ማደንዘዣ ለልጁ ሰጠው። ከዚያ በኋላ አንደ በፊቱ እየተጫወተና እያወራ ነበር።

ከሁለት ቀን በፊት በመጣንበት መንገድ ስንመለስ፣ በወንዙ ላይ ወደ ተሠራ አንድ ድልድይ ላይ ደረስን። ወንዙ ለመታየት ግልጽ እየሆነ ሲመጣ፣ ልጁ እንደ በፊቱ መጮኽና መንቀጥቀጥ ጀመረ።

ከማደንዘዣው የተነሣ በጣም አላስቸገረም፤ ሆኖም ለመቃወም በጣም ተነሣሣ። ይህን ጊዜ ምን እያለ እንደ ነበር ተረዳን። በተደጋጋሚ፣ «ውሀ ውስጥ ናቸው። ሊይዙኝ ነው። ጀርባዬ ላይ ሊውጡ ነው» እያለ ጮኸ። ድልድዩን ስናቋርጥ ከመኪናው ዘሎ ለመውጣት ሞከረ።

ይህ ሁሉ እየተካሄደ ሳለ በኢየሱስ ጥበቃ ሥር እንደ ሆነ ሳም እያረጋገጠለት ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ኀይል ይነግረው ነበር። ሳም ይህንን በማድረግ ልጁን እንዲረጋጋ ረዳው። ወንዙን ዐልፈን ስንሄድም ዐርፎ ተቀመጠ።

እንደዚህ ዐይነት ነገሮችን ከሚያውቁ ዐዳዲስ ክርስቲያን ወንድሞቻችን ጋር ለመነጋገር በጣም ጓጉተን ነበር። ታሪኩን ነግረናቸው ልጁን ሳናላያቸው፣ ጋኔን የያዘው እንደ ሆነ ነገሩን። ከመጥፎ ወይም ከሰይጣናዊ ቤተ ሰብ የተወለዱ ልጆች በአጋንንት ለመያዝ የተጋለጡ እንደ ሆነ አስረዱን። አጋንንት በውሀ ውስጥ

እንደሚኖሩ ያምናሉ። ጓደኞቻችን ብዙ የእንደዚህ ዐይነት ጉዳዮችን ምሳሌ ለመስጠት ችለው ነበር።

ከመሐል ሜዳው ስብሰባ ስድስት ወር በኋላ ታኅሣሥ ወር ላይ ትልቅ ስብሰባ ነበረን። በዚህ ጊዜ የተጠቀምንበት አዳራሽ ክቤታችን አጠገብ ተሠርቶ ያለቀው ዐዲሱ የፀሓይ ሲና ማኅበረ ሰብ አዳራሽ ነበር። ስብሰባው የአራት ቀን ስብሰባ እንዲሆነ ወሰንን። ሥጋ በማቅረብ ባለፈው አጋጥሞን የነበረውን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ብዙ ርቀት ተጉዘው ለመጡት እናቀርብ የነበረው ደቦ፣ ሻይና አትክልት ብቻ ነበር። ንጉሤ ተፈራ ወደ መንዝ ተመልሶ መጥቶ ነበርና መልእክቶቹም ጊዜያቸውን የጠበቁና በዋናው ነጥብ ላይ ያተኰሩ ነበሩ።

ምሽት ላይ የምናደርጋቸው ውይይቶች በየቀኑ ከምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ አስደሳች ነበሩ። በቅርቡ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው መልሰው የተቀበሏቸው ሰዎች ጌታ በስደቱ ወቅት እንዴት ከእነርሱ ጋር እንደ ነበር መሰከሩ። ጌታ በሕይወታቸው ይሠራ እንደ ነበር ብዙ ማረጋገጫዎች ነበሩ።

በሦተኛው ቀን ሌሊት ላይ አንድ ዲያቆን ሲቃኘ ሁሉም ከእንቅልፉ ነቃ። ባትሪ ሲያበሩበት በማይገባ ሁኔታ መሬት ላይ ወድቆ ያጓራ ነበር። በዐይኖቹ ውስጥም ጋኔናዊ ሁኔታ ይታይ ነበር። ጸጥ እንዲል ሊያደርጉት ሞከሩ ነገር ግን አልተሳካላቸውም። ሌሊቱን በሙሉ ሲንፈራገጥና ሲለፈልፍ ዐደረ።

በቀጣዩ ቀን ጠዋት ላይ ሁሉም ከእንቅልፉ ነቅቶ ንጉሤ ጸሎቱን መምራት ጀመረ። የኢየሱስ ስም እንደ ተጠራ ወዲያውኑ ሌሊቱን በሙሉ ሲለፈልፍ ያደረው ልጅ መሬት ላይ እየተንቀጠቀጠ ወደቀ። ንጉሤ ወዲያውኑ በአጠገቡ ሆኖ ይጸልይለት ጀመር። እየጸለይን ሳለ አንድ ያልተለመደ ነገርን ተመለከትን። የራሱን ድምፅ በማይመስል ወፍራም ድምፅና በማይጨበጥ መልክ ለንጉሤ ጥያቄዎች መልስ ሰጠ። ጋኔን እንደሚቁጣጠረው ሲጠየቅ አፆ ብሎ መሰሰ። በመጀመሪያ ሰባት ናቸው አለ፤ ከዚያም አርባ፣ መጨረሻ ላይ ደግሞ ሰማንያ ሰባት አጋንንት አለ።

አጋንንቱ እንዲወጡ ሲታዘዙ፣ በዚያ ወፍራም ድምፅ የመቁየት ፍላጎት እንዳለው ተናገረ። አንግዳና አስፈሪ የሆነው ድምፅ «የእኔ ነው። ለብዙ ዓመታት በዚህ ኖሬአለሁ» ሲል ሰማን። ጭዱ ላይ እየተንቀጠቀጠ የሚያቃስተውን ልጅ ለማየት ሰዎች ወደ ስብሰባ ተመሙ። ነገሩን የማወቅ ፍላጎታቸው ተመልሶ ከመሄድ ገታቸው።

በከፍተኛ ሁኔታ ሲሠቃይ የነበረው ልጅ ከመንዝ በስተ ሰሜን በኩል ከሚገኘው ከትግራይ እንደ መጣ ተረዳን። ወደ ፀሐይ ሲና ለመምጣት የመረጠው በጣም የታወቀ የዲቁና ትምህርት ቤት ስላለ

ነው። አብዛኛውን ጊዜ ወጣት ወንዶች በሙሉ ጊዜአቸው ለመማር ከፈለጉ ቤታቸውን ጥለው ይሄዳሉ።

ጓደኞቻችን ጋኔን ከሰው ወጥቶ ሲሄድ የሚያውቁበት ጊዜ በጣም ትንሽ እንደ ሆነ ነገሩን። በመንዝ ያሉ ሰዎች መጀመሪያውኑ አጋንንት የሚያወጡት ጠንቋዮችና ውፋዎች ማለት የሚርት ጥንቁላ ዐዋቂዎች እንደ ሆኑ ያውቃሉ። ስለዚህ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ አጋንንቱን ለማውጣት የሚችሉት እነርሱ ብቻ ነበሩ። እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን በአጋንንት ለተያዘ ሰው አንድ ነገር ለማድረግ ብትሞክር ሰውየው እንደሚሞት ይታመን ነበር።

በዚያ ጊዜ የሚካሄደውን ነገር ይመለከቱ ከነበሩት አብዛኛዎቹ እየሆነ ያለውን ነገር በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የሚካሄድ ጦርነት እንደ ነበር አስተዋሉ። የእግዚአብሔርን ኀይል የተለማመዱ ሰዎች ከልብ የሚያቀርቡት ጸሎት በየጊዜው ይቀርቡ ከነበሩ ጸሎቶች ይበልጥ ነበር። ልጁ በአካባቢው ዘመድ ስለሌለው ማንም ስለ እርሱ ኀላፊነት አልወሰደም። ለእርሱ በመጸለያችን የተሰነዘረ ተቃውሞም አልነበረም።

በመንዝ ሁሉም የቤተ ሰብ አባላት በአንድ ክፍል ውስጥ ስለሚኖሩ ለጸሎት የሚያመች ገለል ያለ ቦታ ለማግኘት አይቻልም። ገብተው ሊጸልዩ የሚችሉበት የግል ስፍራ የላቸውም። ይሁን እንጂ ለብቻቸው መሆን የሚያስችላቸው አንድ መንገድ አግኝተዋል። ሲጸልዩ በጉልበታቸው ተንበርክከው ግንባራቸው መሬቱን እስኪነካ ድረስ ያጐነብሳሉ። በእንደዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ጭንቅላታቸውን ሁልጊዜ በሚሰብሱት ትልቅ ሻርፐ ይሸፍኑና በዙሪያቸው በሚገኘው ነገር ሁሉ ይከለላሉ። በዚያን ቀን ጠዋት መሬቱ ሁሉ ወለል ላይ ልጥፍ ብለው ባጐነበሱ ሰዎች ተሞልቶ ነበር። እያንዳንዱ ሰው በሰይጣን ኀይል ላይ የኢየሱስን የመሥዋዕትነት ደም አሸናፊነት ያውጅ ነበር።

አጋንንቱ ከልጁ ወጥተው በሰባት ዕጥፍ ሊመለሱ ወይም ሌላ ሰውን ሊይዙ እንደሚችሉ እናውቅ ነበር። ስለዚህ ሁሉም ራሳቸውን ይፈትኑ ዘንድ አንድ ጊዜ ወደ ውጭ አወጣናቸው። እግዚአብሔር ለዚህ እንዲጠቀምብን ንጹሕ ሆነን መገኘት ፈለግን። የእግዚአብሔርን ይቅርታ በመቀበልና ከኀጢአት ነጻ በመሆን ትክክለኛ ሥራን እንሠራለን ብለን ዐሰብን።

በትንንሽ የጸሎት ቡድች ተከፋፈልን። ጥቂቶቹ ንስሐ ገቡ፤ ጥቂቶቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ ተቀበሉ፤ ሌሎች ደግሞ ጸሎቱን በጸጥታ ሰሙ። ከአንድ ሰዓት የጸሎትና የውይይት ጊዜ በኋላ ወደ አዳራሹ በድጋሚ ገባን። ጦርነቱ በዚያን ጊዜ በጎይለኛ ሁኔታ እንደ ቀጠለ ነበር። ለመጸለይ በድጋሚ ስንበረከክ ሰይጣናዊው ድምፅ እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ ለመቄየት እንደሚፈልግ ሲናገር አደመጥን። በመቀጠል ደግሞ ጋኔኑ በቅድስት ማርያም ወይም በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም እንድናስወጣው ሐሳብ አቀረበ። የኢየሱስን ስም

በፍጹም አልጠቀሰም ነበር። ከጦርነቱ ከፍተኛነት የተነሣ የጊዜውን መሄድ አላስተዋልንም። ሰዓታችንን ስንመለከት አንድ ሰዓት መሆኑ በጣም አስገረመን። ከጠዋት ጀምሮ ወጣቱ ልጅ አንድን ሐሳብ ተናግሮ ለመጨረስ አይችልም ነበር። ነገር ግን የተባለው ሰዓት እንዳለፈ የሕመሙ ስሜት በረደለት። በመጨረሻ ላይም በተረጋጋ ድምፅ በኢየሱስ ስም መሸነፉን ለመግለጽ ቻለ።

ሰዎች ሁሉ ልጁ በርግጥ ከአጋንንት ነጻ እንደ ሆነ ሲያምኑ በደስታ ተዋጡ። በቀሪው ጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋና ስናቀርብ ቈየን። በዚያን ጊዜ ተሳታፊዎቹ ብዙ መዝሙሮችን ማወቅ ችለው ነበርና በስብሰባው ላይ የተዘመረው መዝሙር መግለጽ በማይቻል መልክ እጅግ ማራኪ ነበር። እያንዳንዱ ሰው በሙሉ ልብ ይዘምር ነበርና በድምፃቸው ውሕደት እኛም የዚያ ዝግጅትና ክሥተት አካል እንደ መሆናችን፣ ልባችን በሐሤት ተጥለቀለቀ።

በዚያ ምሽት በድጋሚ ጭድ ላይ ተቀምጠን ሳለ ጌታ ውይይቱን በዐዲስ መልስ መራው። አንድ ዲያቆን እናቱ ለሰይጣን ባሪያ እንደ ሆነች ስለሚያውቅ እንድንጸልይለት ጠየቀን። ብዙዎች ከእርሱ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ለመጸለይ ሲስማሙ እኛም ወዲያውኑ መጸለይ ጀመርን። ከዚያም አንድ ሌላ ዲያቆን ከዘመዶቹ የአንዱን ስም በመጥቀስ እንዲጸለይለት ጠየቀ። ዲያቆናቱ እነዚህ ችግሮች በራሳቸው ቤት ውስጥ መኖራቸውን ሲያምኑ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። በዚያ ቀን ያገኙት ልምድ በአእምሮአቸው ዐዲስ ሆኖ በሚኖሩበት ስፍራ ሰይጣንን በእግዚአብሔር ኀይል ይቃወሙት ጀመር።

ለረጅም ጊዜ አጋንንት ዐድረውበት የኖረው ልጅ ኢየሱስ እንደሚያስፈልገው በጽናት አመነ። የራሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖረው ያስፈልግ ነበር። ንጉሤ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ እንድንሰጠው ሐሳብ አቀረበልን። ሌሎቹ መጽሐፍ ቅዱስ ያገኙት ፈተና ተፈትነው ስለ ነበር አመነታን። ቄይተን እርሱም ፈተና መውሰድ እንዳለበት ተሰማን።

ሁሉም በቅርቡ በሰይጣን ቊጥጥር ሥር የነበረውን ልጅ ብቃት ለመመልከት ተሰበሰበ። ፈተናው ከባድ ስለ ነበረ ብዙዎቹ የመጀመሪያ ጦቹን ፈተናዎች ማለፍ አልቻሉም። ጌታ ብሩህ አእምሮ እንዲሰጠው ጸለይንለት። ልጁ በሚያስደስት ሁኔታ የተነገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዐወቀ፤ እንዲያውም ከፈተና በኋላ ሁሉ ያለውን ዐውቆት ነበር። በትልቅ ስኬት ፈተናውን ዐለፈ። ከአንድ ቀን በፊት በልዩ ሁኔታ የተመለከትነው ልጅ እንደ ሆነ ለማመን ያስቸግር ነበር።

እግዚአብሔር ከዲያብሎስ የበለጠ ኀይለኛ እንደ ሆነ ብዙ ጊዜ ለሰዎች እንናገር ነበር፤ ሆኖም በመንዝ ያሉ ጓደኞቻችን የሰይጣንን ኀይል በተገቢው መንገድ እንዳልተረዳን አድርገው ያስቡ ነበር። ስለምንናገረው ነገር እንደምናውቅ ይጠራጠሩ ነበር። በኋላ ግን እግዚአብሔር ፈጽሞ በማይረቱት መልኩ ኀይሉን አሳያቸው። ጌታ በአሸናፊነት ወጣቱን ልጅ ከሰይጣን ባርነት ነጻ አወጣው።

ነገር ግን ጠላት መሸነፉን በቀላሉ መቀበል አልወደደም። ለረጅም ጊዜ ይዞት የነበረውን ለመልቀቅ አልፈለገም። መንዝ የእርሱ ግዛት ነበር ማለት ይቻላል። አሁንም ዲያብሎስ በዚያ አገር ውስጥ በእንደዚህ ዐይነት ሁኔታ እንዲቀጥል ይፈልጋል።